CENTRE for INFORMATION RESILIENCE

# በኢትዮጲያ ቲክቶክና ዩትዩብ መድረክ ላይ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ዙሪያ የተደረገ ምርመራ

# በኢትዮጲያ ቲክቶክና ዩትዩብ መድረክ ላይ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ዙሪያ የተደረገ ምርመራ

እ.ኤ.አ መጋቢት 2025

---

## ማውጫ


1. አጠቃላይ ሀሳብ 3
2. መግቢያ 5
   - **2.1** በቴክኖሎጂ የታገዙ ፆታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች ዙሪያ ጥናቶችን ማስቀጠል ለምን አስፈለገ? **5**
   - **2.2** የፕሮጀክቱ አላማዎች **7**
   - 2.3 የጥናቱ ጥያቄዎች 7
   - 2.4 የጥናቱ ወሰን 7
3. የጥናቱ ዘዴ 7
   - 3.1 ሃሳባዊ ማዕቀፍ 8
   - 3.2 የቃላት መረጣ 9
   - **3.3** የማህበራዊ ሚዲያ አካውንት መረጣ **10**
   - **3.4** የመረጃ አሰባሰብና ዝግጅት **11**
     - 3.4.1 መረጃ አሰባበሰብ 11
     - 3.4.2 የመረጃ ቅድመ ዝግጅት 11
     - 3.4.3 ለትንታኔ የሚሆኑ የመረጃ ናሙናዎችን መምረጥ 12
     - 3.4.4 መረጃዎችን ሚስጥራዊ ማድረግ 12
     - 3.4.5 ተመጣጣኝ መረጃ 12
   - 3.5 መረጃዎችን ጥላቻ ብሎ መመደብ 12
     - 3.5.1 መረጃ ትርጓሜ 12
   - 3.6 አውደ ጥናቶች 13
   - 3.7 ውስንነቶች 13
4. ውጤቶችና ማብራሪያዎች 15
   - 4.1 መድረኮቹ 15
     - 4.1.1 ቲክቶክ 15
     - 4.1.2 ዩትዩብ 16
     - 4.1.3 የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ተጠቃሚነት 16
     - 4.1.4 የይዘት ቁጥጥር 16
   - 4.2 ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረገ ፆታን መሰረት ያደረገ የጥላቻ ንግግር 18
     - 4.2.1 ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረገ የጥላቻ ንግግር አይነት 18
     - 4.2.2 የጥላቻ አውድ 19
     - **4.2.3** የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ልዩ አዝማሚያ (የጥላቻ አይነት እና አውድ) **21**
     - **4.2.4** ማብራሪያዎች **24**
   - 4.3 ሴቶችና ልጃገረዶች ከወንድ ጋር ሲነጻጸሩ 39
     - 4.3.1 የጥላቻ አይነቶች ንፅፅር 40

4.3.2 የጥላቻ ንግግር አውዶች ንፅፅር 40
4.3.3 ማብራሪያ 41
4.4 ተደራራቢ ጥቃቶች 46
4.4.1 ማብራሪያ 47
4.5 ከሌሎች በማንነት ላይ የተመሰረቱ የጥላቻ ንግግሮች ጋር የተደረገ ንፅፅር 52
4.5.1 የጥላቻ ንግግር አይነት ከሌሎች የማንነት ቡድኖች ጋር ማወዳደር 53
4.5.2 የጥላቻ ንግግር አውድ ከሌሎች የማንነት ቡድኖች ጋር ሲወዳደር 54
4.5.3 ማብራሪያ 55
4.6 በተለያዩ የይዘት ዘውጎች ላይ የሚሰነዘሩ የጥላቻ ንግግሮች ንፅፅር በፆታ 59
4.6.1 የተለያዩ ዘውግ ያላቸው ይዘቶችን የሚያዘጋጁ ወንዶችና ሴቶች 60
4.7 የኢንተርኔት ላይ ጥቃት የሚያደርሱ እና/ወይም የሚደርስባቸው የይዘት ፈጣሪዎች 64
5. ማጠቃለያ 64
6. ምክረ ሀሳብ 68
7. አባሪ 68

***ማስጠንቀቂያ፡*** *ይህ ሪፖርት የጥላቻ ንግግርን፣ የስድብ ቋንቋዎችንና ጎጂ ንግግሮችን የያዘ ነው። እነዚህ ሃሳቦች ሲ.አይ.አርን የማይወክሉና ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ የተጋሩ ሲሆኑ በኢትዮጲያ ውስጥ ያለውን ፆታዊ ጥላቻ ንግግሮች ለማጥናት የተካተቱ ናቸው። ይህ ሪፖርት የጥናቱን ግኝቶች ስሜት በማይነካ መልኩ ለማቅረብ ቢሞክርም አንዳንድ አንባቢዎችን ሊረብሽ የሚችል መረጃዎችን ይዟል። ፆታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች ዙሪያ መረጃ ካስፈለግዎ የ"*NO MORE*"ን የእርዳታ ሰጪ አካላትን የያዘ ስበስብ ይመልከቱ።*

# 1. አጠቃላይ ሀሳብ

ሴንተር ፎር ኢንፎርሜሽን ሪዚሊያንስ (ሲ.አ.ይ.አር) ኢትዮጲያ ውስጥ በቴክኖሎጂ የታገዙ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ላይ ያደረገው ምርመራው እንደሚያሳየው እነዚህ ጥቃቶች ጎጂና የተስፋፉ ሲሆኑ ሴቶች በተደጋጋሚ ትኩረት እነዲነፈጋቸውና ዝቅ ተደርገው እንዲታዩ ምክንያት ሆኗል ። በቴክኖሎጂ የታገዙ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ድሮም  ከነበሩ የተሳሳቱ የስነ-ፆታ እሴቶችና ሴት ጠል ከሆኑ አመለካከቶች ጋር በጥብቅ የተቆራኙ ናቸው። የኢንተርኔት ላይ ጥቃቶች ማን በዲጂታል መድረኮች ላይ ሀሳብ ማጋራት ፣መምራትና ያለ ስጋት መንቀሳቀስ እንደሚችል ይወስናሉ። ሴቶችና ልጃገረዶች በዲጂታል መድረኮች ላይ በነጻነትና ደህንነታቸው ተፀብቆ እንዲሳተፉ ማስቻል የኢንተርኔት ላይ ደህንነት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ሴቶች በአጠቃላይ ማህበራዊ ህይወታቸው ላይ በነፃነት እንዲሳተፉ የማገዝ ጉዳይ ነው ።

ሲ.አይ.አር ከዚህ ቀደም በፌስቡክ ፣ በቴሌግራም እና ኤክስ ( በቀድሞ ስሙ ትዊተር ) ላይ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶችና የጥላቻ ንግግሮች ዙሪያ ያደረገውን ጥናት በማስፋት በቲክቶክና በዩትዩብ ላይ ጥናቱን አድርጉአል። ይህ ሪፖርት በጉዳዩ ላይ ያለውን መረጃ በማጠናከር ባለድርሻ አካላት ትርጉም ያለው ፖሊሲ ለውጥ ለማምጣት የሚያደርጉትን ጥረትና የማንቃት ተግባሮቻቸውን ያግዛል።

የፕሮጀክቱ አላማዎች

- ኢትዮጵያ ውስጥ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች ዙሪያ ያለውን ማስረጃ ማጠናከር
- የመንግስት ተቋማት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የማህበራዊ ሚዲያ ኩባንያዎችና ማህበረሰቡ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ስላደረጉ ጥቃቶች ያላቸውን ግንዛቤ ማጠናከር
- በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን በመከላከል ዙሪያ ለሚሰሩ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና የመንግስት ተቋማት ተግባራዊ ምክረ ሀሳቦችን ማቅረብ

ይህ ጥናት መረጃን መሰረት ባደረገ ትንተናና በባለሙያ የተደረጉ አውደ ጥናቶችን በመጠቀም አዳዲስ ምልከታዎችን አቅርቧል። ሲ.አይ.አር በሌሎች አጥኚዎች የተገመገመና ተቀባይነትን ያገኘ የጥናት ዘዴን በመጠቀም በዩቱዩብና በቲክቶክ ላይ ያሉ የጥላቻ ንግግሮችን ከመረመረ በኋላ ውጤቶቹን ሲ.አይ.አር በፌስቡክ፣ በቴሌግራምና ኤክስ ላይ ከሰራው ጋር አወዳድሯል። ሲ.አይ.አር  የማህበራዊ ሚዲያ ልጥፍ ናሙናዎችን ለመምረጥ የናቹራል ላንግዌች ፕሮሰሲንግ (Natural Language Processing) ዘዴን የተጠቀመ ሲሆን አጥኚዎች የተመረጡትን 17,082 የማህበራዊ ሚዲያ አስተያየቶች በአራት ቋንቋዎች (አማርኛ፣ አፋን ኦሮሞ፣ ትግርኛና ኢንግሊዘኛ) የጥላቻ ንግግር ኢላማዎችን ፣የጥላቻ ንግግር አይነቶችን እና የንግግሮቹን አውዶች መርምረዋል። በመጨረሻም ሲ.አይ.አር በተንቀሳቃሽ ምስል ዘውጎች እና ፆታን መሰረት ባደረገ ጥቃት መሃከል ያለውን ግንኙነት  አጥንቷል።

ቁልፍ ግኝቶች

ኢትዮጲያ ውስጥ ሴቶችና ልጃገረዶች ድምጻቸውን የሚያፍኑና ተሳትፏቸውን የሚገድቡ ስድቦች ፣በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የተሳሳቱ መረጃዎችን የያዙ ንግግሮች ፣የፌዝ ንግግሮችና አሳናሽ የሆኑ አገላለፆች ይደርስባቸዋል። በአመራር ላይ ያሉ ሴቶች ፣ ስፖርተኛ ሴቶች ወይም ፌሚኒዝምን የሚሰብኩና ስለ ሴቶች መብት በመታገል የተለመደውን የስርዓተ-ፆታ ስርዓት የሚሟገቱ ሴቶች በተለየ ሁኔታ ጠንከር ያሉ ስድቦች፣ ወሲባዊ የሆኑ አስተያየቶች ፣ ስም ማጥፋቶችና መገለሎች ይደርስባቸዋል።. ለምሳሌ ፌሚኒዝም ባህላዊ እሴቶችን የሚሸረሽር እንደሆነና ፌሚኒስቶችም ለገንዘብ ጥቅምና ግብረ-ሰዶማዊነትን ለማስፋፋት እየሰሩ እንደሆነ ይታሰባል። እነዚህ አስተሳሰቦች ከዲጂታል መብት ጥሰቶች ጋር በመጣመር ሴቶችን ዝም የሚያሰኝ የዲጂታል መድረክ ለመፈጠሩ ምክንያት ሆኗል።

ወንዶችም በፆታዊ ሚናቸው ዙሪያ ያጠነጠኑ፣ ደካማነትን ፣ ወንድ አለመሆንን የሚገልፁና የፆታ እኩልነት ድጋፍን የሚቃወሙ የጥላቻ ንግግሮች ይደርሱባቸዋል። ሴትና ወንድ የፖለቲካ አመራሮች የኢንተርኔት ላይ ጥቃት ቢደርስባቸውም ወንዶች በፖሊሲና ፖለቲካ አመለካከታቸው ዙሪያ ጥቃት ሲደርስባቸው ሴቶች ግን በመልካቸው ወይም ባላቸው ማህበራዊ ሚና ዙሪያ ጥቃት ይደርስባቸዋል። በተጨማሪም ወንዶች ላይ ያነጣጠሩ ጥቃቶች ሴትነትን እንደማጥቂያና ማሸማቀቂያ አድርገው ይጠቀማሉ። በመሆኑም ሴቶች በቀጥታ ከሚደርስባቸው ጥቃት በተጨማሪ ወንዶችን ኢላማ ላደረጉ ጥቃቶች መሳሪያ ይሆናሉ።

ፆታን መሰረት ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች ብቻቸውን የሚገኙ ሳይሆኑ ከብሔር፣ ሀይማኖትና፣ ፖለቲካዊ አመለካከት ጋር የተገናኙ፣ ውስብስብና የተለያዩ ገጽታ ያላቸውን ጥቃቶች የሚያስከትሉ አልፎም ቀደም ብለው የነበሩ ውጥረቶችን የሚያባብሱ ናቸው። የቆዳ ቀለምና ጥቁርነት ላይ ያነጣጠሩ ጥቃቶች ያልተጠኑ ግን በሰፊው የሚታዩ ናቸው። የፖለቲካ ሁነቶችና አመለካከቶች ብሄር ተኮር ለሆኑ ፆታዊ የጥላቻ ንግግሮች በር ሲከፍቱ ሃይማኖታዊ ተፅዕኖዎች ደግሞ ሴቶችን ለሚያጣጥሉና ዝቅ ለሚያደርጉ ጥላቻ ንግግሮች በር ይከፍታሉ። እነዚህ ግኝቶች እንደሚያሳዩት ጉዳቱ ከሴቶችና ልጃገረዶች አልፎ በትግራይ ጦርነት ወቅት እንደታየው ፅብ ጫሪ የሆኑ ፖለቲካዊ ንግግሮች ፣ የተሳሳቱ ትርክቶች እና እንደ "ባንዳ" ፣ "ከሃዲ" እና "ሰይጣን " የመሳሰሉት ቃላት በገሀዱ አለም ብጥብጥ ለመፍጠር መንስኤ ይሆናሉ።

ወንድና ሴት የኢንተርኔት ዝግጅት አቅራቢዎች የተለያየ ይዘት ያላቸውና ከማህበራዊ አመለካከቶች ጋር የተገናኙ ጥቃት ይደርስባቸዋል። በፖለቲካ ዙሪያ ውይይት የሚያደርጉ ሴቶችና ልጃገረዶች ሌሎች ዘውጎች ላይ ከሚሳተፉ ሴቶች በበለጠ ጥቃት ይደርስባቸዋል። ይህም ችግሩን ለመፍታት የስርዓተ ፆታንና ባህላዊ ሁኔታዎችን ያማከለ አቀራረብ እንደሚያስፈልግ ያሳያል።

ሴቶችና ልጃገረዶች በኢንተርኔት ላይ ለጥቃት ኢላማ የሚሆኑበት መንገድ ከመድረክ መድረክ መለያየቱና በሰፊው መታየቱ፣ ችግሩን ለመፍታት የቴክኖሎጂ መፍትሔና የማህበራዊ አመለካከት ለውጦች አስፈላጊ መሆናቸውን ያሳያል። ይህ ጥናት በማህበራዊ ሚዲያ ይዘት ቁጥጥር ሂደት ላይ ያለውን ድክመትና ሰዎች በማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ ጥቃትን በመከላከል ዙሪያ ማህበራዊ ሚዲያ ኩባንያዎች ላይ እምነት እንደሌላቸው ያሳያል። የተሻለ የይዘት ቁጥጥር፣ ጠንከር ያለ የደንብ ትግበራዎችና የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ተጠያቂነትን ማስፈን በተለይም የቋንቋ ስብጥር ባላቸው ሃገራት አስፈላጊ ነው። የተለያዩ የማህበራዊ መድረኮች የተለያየ አይነት የጥላቻ ንግግሮችን ስለሚያስተናግዱ መፍትሔዎች መድረክ ተኮርና ሰፊ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ለምሳሌ በቲክቶክ ላይ ባሉ ይዘቶችና በዩትዩብ ላይ የሚገኙት ረዘም ያሉ የፖለቲካ ይዘቶች መካከል ያለው ልዩነት የጥላቻ ንግግርን በመዋጋት ረገድ ልዩ ፈተናዎችን ይፈጥራል።

በመጨረሻም ኢንተርኔት ላይ ያለው ዓለም ከእውነተኛው ዓለም የተለየ ነው የሚለው የተሳሳተ አስተሳሰብ መቀየር አለበት። ኢንተርኔት ላይና ከኢንተርኔት ውጪ ያለው አለም በጥብቅ የሚገናኙ ናቸው። ከኢንተርኔት ውጪ ያሉ ሁነቶች ኢንተርኔት ላይ ያለውን እንቅስቃሴ ሲወስኑ የኢንተርኔት ላይ ጥቃቶች በእውነተኛው ዓለም ላይ የስነ ልቦናዊና አካላዊ ጉዳት ያስከትላሉ።

---

# 2. መግቢያ

ማህበራዊ ሚዲያ እና ዲጂታል ቴክኖሎጂዎች ሰዎች የሚገናኙበትን፣ የሚግባቡበትን እና ከአለም ጋር የሚገናኙበትን መንገድ እየቀረፀ ነው። አብዛኞቹ ግላዊና ሙያዊ መስተጋብሮች በኢንተርኔት ላይ እንደመሆናቸው መጠን በቴክኖሎጂ የታገዙ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች እየጨመሩ መጥተዋል። በቴክኖሎጂ የታገዙ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች በኢትዮጲያ ውስጥ ጥላቻ ንግግር፣ ትንኮሳ፣ የበቀል ፖርኖግራፊ፣ ጎጂ የስርዓተ ፆታ ልምዶችን ማስቀጠልና የሴቶችን ድምፅ ማፈንን ጨምሮ የተለያዩ መልኮች አላቸው። ተፅዕኖዎቹ ከግለሰባዊ ጉዳት አልፈው የሴቶችን አጠቃላይ ማህበራዊ ተሳትፎ የሚያቀዛቅዙ ናቸው።

የኢንተርኔት ላይ ጥቃቶች ማን መናገር፣ መምራትና በዲጂታል መድረኮች ላይ በደህንነት መንቀሳቀስ እንደሚችል ይወስናሉ። ሴቶችና ልጃገረዶች በዲጂታል መድረኮች ላይ በደህንነትና በነጻነት እንዲሳተፉ ማስቻል የኢንተርኔት ላይ ደህንነት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በማህበራዊ ህይወት ላይ ያላቸውን ተሳትፎ የማረጋገጥም ጉዳይ ነው። ሲ.አይ.አር እነዚህን ጉዳዮች ለመረዳት እና ችግሮችን ለመፍታት በሚደረገው ጥረት ላይ አዲስ አበባ ውስጥ ጥናቶች፣ አውደ ጥናቶችን እና ኮንፍረንሶችን በማዘጋጀት ግንባር ቀደም ተሳታፊ ሆኗል።

በፌስቡክ ፣በቴሌግራምና ኤክስ ላይ ስላለው ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ሲ.አይ.አር እ.ኤ.አ በ2024 የሰራው ጥናት ወሳኝ ጉዳዮችን አንስቶ ተጨማሪ ምርመራ እንደሚያስፈልግ አመላክቷል። በእነዚህ ግኝቶች ላይ በመመስረት፣ ይህ ጥናት ወሰኑን ዩቱዩብና ቲክቶክ ላይ ወዳሉ የጥላቻ ንግግሮች በማስፋት በኢትዮጲያ ዲጂታል መድረክ ውስጥ ስላለው በቴክኖሎጂ የታገዘ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት አዳዲስ ግንዛቤዎችን ይሰጣል። ይህ ዘገባ ኢንተርኔት ላይ ባሉ ጥቃቶች አይነት ፣አስተሳሰብና ግንኙነቶች ዙሪያ ጥናት በማድረግ ጠቃሚ የፖሊሲ ለውጦችን ለመጠቆም፣ የማንቃት ስራዎችን ለማጎልበትና ደህንነቱ የተጠበቀ የኢንተርኔት መድረክን ለመፍጠር ያለመ ነው።

## 2.1 በቴክኖሎጂ የታገዙ ፆታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች ዙሪያ ጥናቶችን ማስቀጠል ለምን አስፈለገ?

በቴክኖሎጂ የታገዘ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት የዘመናት ችግር የሆነው ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት አዲሱ መገለጫ ነው። የተሳሳቱ ስነ-ፆታዊ አመለካከቶችና ባህላዊ አድሎዎች የመሳሰሉ የተሳሳቱ ማህበራዊ አመለካከቶችን የሚያንፀባርቁ አስተሳሰቦች ከጥቃቅን ጥቃቶች ተነስተው ወደ አካላዊ ጉዳት የሚደርሱ ናቸው። ይህም ሴቶች ኢንተርኔት ላይም ሆነ ከኢንተርኔት ውጪ ባለው ዓለም ዝም የማስባል፣ ከማህበራዊ ኑሮ የመገለልና በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ የመስጠትን መብት በመገደብ መገለልን ያስቀጥላሉ።

ሲ.አይ.አር በኢትዮጲያ ውስጥ ያሉ በቴክኖሎጂ የታገዙ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ባህሪያትን በመፈተሽ እና ፆታን መሰረት ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች እንደ አንድ በቴክኖሎጂ የታገዘ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት አድርጎ በመቁጠር ሰፊ ጥናት አድርጓል። የሲ. አይ.አር ምርመራ ጥቃቱ ከደረሰባቸው ሰዎች ጋር በተደረጉ ቃለ ምልልሶች፣ ከማህበራዊ ሚዲያ ይዘቶችን በመተንተን እና በተለለያዩ ቋንቋዎች ፀብ ጫሪ የሆኑ የቁልፍ ቃላትን ስብስብ በማዘጋጀት ጠቃሚ ግንባዛቤዎችን ፈጥሯል። ሲ.አይ.አር በሀገር በቀል የአፍሪካ ቋንቋዎች የተፃፉ የጥላቻ ንግግሮችን እንዴት ማጥናት እንደሚቻል ባዘጋጀው ዘዴ ላይ ያተኮረ ጥናትም አሳትሟል። እነዚህ ጥረቶች አዲስ አበባ ውስጥ ከተደረጉት ውይይቶችና ጋር በመሆን በስልጠናዎችና የግንዛቤ ፈጠራ ስራዎች ላይ በጎ ተጽዕኖ ፈጥረዋል። ለምሳሌ በርካታ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የሲ.አይ.አርን ግኝቶች በፕሮግራሞቻቸውና የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራዎቻቸው ውስጥ አካተዋል።

> ማናቸውንም መሻሻሎች ብናመጣም ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች በአዲስ መልኩ መምጣት መቀጠላቸው አስፈሪ ነው።
>
> የአውደ ጥናት ተሳታፊ፣ እ.ኤ.አ 2025

በሌሎች ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ ያለውን ግንዛቤ ለማስፋት ተጨማሪ ጥናቶች እንዲደረግ ጥሪዎች ሲቀርቡ ቆይተዋል። ለምሳሌ ከተለያዩ ኢትዮጲያዊ ባለድርሻ አካላት ጋር በተደረጉ ውይይቶች ቲክቶክና ዩትዩብ በመሳሰሉና ተጽዕኖ ፈጣሪ ሆነው ነገር ግን ብዙም ጥናት ባልተሰራባቸው የማህበራዊ መድረኮች ዙሪያ ጥናት እንደሚያስፈልግ ታይቷል። ይህ ፕሮጀክት ይህንን የመረጃ ክፍተት ለመሙላት እና በኢትዮጲያ ውስጥ ያሉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን እና ፖሊሲ አውጪዎችን ለማብቃት ያለመ ነው። ግኝቶቹ በተለይም ብዙም ተናጋሪ በሌላቸው ቋንቋዎች የሚለጠፉ ይዘቶችን ለመቆጣጠር ማሻሻያ ፖሊሲዎች እንደማያስፈልጉ አሳይተዋል። ሲ.አይ.አር ምርምሩን በመቀጠልና በኢትዮጲያ ባለድርሻ አካላት መካከል ትብብር በማጎልበት፣ በቴክኖሎጂ ድጋፍ በሚቃጡ ፆታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች ዙሪያ ግንዛቤን በማስቀጠልና ተግባራዊ ለውጦችን በማምጣት ለሴቶችና ልጃገረዶች ደህንነቱ የተጠበቀ የዲጂታል መድረክን ለመፍጠር ይሰራል።

> “ቴክኖሎጂ አሁንም ሆነ ወደፊት ተፅዕኖ ፈጣሪ ነው። ሰዎች እነዲጠቀሙት ደህንነቱ የተጠበቀ መድረክ መፍጠር አለብን።”
>
> የአውደ ጥናት ተሳታፊ፣ እ.ኤ.አ 2025

## 2.2 የፕሮጀክቱ አላማዎች

- ኢትዮጵያ ውስጥ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች ዙሪያ ያለውን ማስረጃ ማጠናከር
- የመንግስት ተቋማት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የማህበራዊ ሚዲያ ኩባንያዎችና ማህበረሰቡ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ስላደረጉ ጥቃቶች ያላቸውን ግንዛቤ ማጠናከር
- በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን በመከላከል ዙሪያ ለሚሰሩ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና የመንግስት ተቋማት ተግባራዊ ምክረ ሀሳቦችን ማቅረብ

## 2.3 የጥናቱ ጥያቄዎች

ከኢትዮጲያ ባለድርሻ አካላት ጋር የተደረገው ውይይትን ተከትሎ ሲ.አይ.አር በፌስቡክ ፣በቴሌግራም እና ኤክስ ላይ ያካሄደውን ቁጥራዊ ጥናት ወደ ሁለት መድረኮች ማለትም ዩትዩብ እና ቲክቶክ አሳድጓል። ይህ ጥናት ከእነዚህ ማህበራዊ መድረኮች ጋር በተያያዘ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ይሞክራል፡

1. መልክ (አይነት አውድ)፡ የትኞቹ የጥላቻ ንግግር አይነቶችና አውዶች በሰፊው ይታያሉ?
2. ተያያዥነት፡ በተያያዥነት ሌሎች ከለላ የተሰጣቸው ማንነቶች ኢላማ ሲሆኑ የጥላቻ ንግግር እንዴት ይለያል?
3. የማህበራዊ ሚዲያ መድረክ ልዩነት፡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥላቻ ንግግሮች በማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች መሃከል ልዩነት አላቸው?
4. ከይዘት ጋር ያለው ግንኙነት፡ የጥላቻ ንግግር ከተንቀሳቃሽ ምስሉ ይዘት ጋር ይገናኛል?

### 2.4 የጥናቱ ወሰን

በነባሩ ጥናት ላይ በመመርኮዝና ከዚህ በፊት ካደረገው ጥናት ጋር ተመሳሳይ የጥናት ዘዴና መዝገበ ቃላትን ዩቱዩብ እና ቲክቶክ ላይ ተግባራዊ በማድረግ ሲ.አይ.አር በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች መሃከል ንፅፅሮችን አድርጓል። በማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች መሃከል ባለው የይዘት ልዩነት (ተንቀሳቃሽ ምስልና አስተያየት መስተጋብር) ምክንያት ሲ.አይ.አር በተንቀሳቃሽ ምስል ይዘቶችና አስተያየቶች መሃከል ያለውን ግንኙነት የሚዳስስ ተጨማሪ ጥያቄዎችን አካቷል።

ይህ ጥናት፣ የጥላቻ ንግግርን [የኢትዮጲያ መንግስት](#) "የጥላቻ ንግግርንና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከታተልና ለመቆጣጠር" ባወጣው አዋጅ መሰረት መተርጎሙ ለኢትዮጲያ ሁኔታ የተመቸ እንዲሆን ያደርገዋል። በግብዓትና በጊዜ ጥበት ምክንያት በማህበራዊ ሚዲያ በሰፊው የሚታዩ አራት ቋንቋዎች ማለትም አማርኛ፣ አፋን ኦሮሞ፣ ትግርኛና እንግሊዘኛ ተመርጠዋል። ቀጣይ ጥናቶች ተጨማሪ ቋንቋዎችን ሊያካትቱ ይችላሉ።

ፆታን መሰረት ያደረገ የጥላቻ ንግግር ብዙ አይነት በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃት አይነቶችን የያዘ ነው። ወደፊት የሚደረጉ ጥናቶች በምስል የታገዙ የጥላቻ ንግግሮችን፣ የበቀል ፖርኖግራፊንና በታዋቂ ግለሰቦች ላይ በሚደርሱ ጥቃቶች ዙሪያ ሊያጠነጥኑ ይችላሉ።

---

# 3. የጥናቱ ዘዴ

ሲ.አይ.አር እ.ኤ.አ በ2004 በኢትዮጲያ የኢንተርኔት መድረክ ላይ ስላለው ፆታን መሰረት ያደረገ የጥላቻ ንግግር (ፌስቡክ፣ቴሌግራምና ኤክስ) ላይ የሰራውን ጥናት ወደ ሁለት ተጨማሪ መድረኮች ማለትም ዩቱዩብና ቲክቶክ አስፍቷል። ተመሳሳይና በባለሙያዎች የተገመገመ የጥናት ዘዴ ተግባራዊ መሆኑ በተለያዩ ማህበራዊ መድረኮች መሃከል የተገኙትን ግኝቶች ለማወዳደር ያግዛል።

ሲ.አይ.አር ከዩቱዩብና ቲክቶክ ናሙና ልጥፎችን ለመምረጥ ቁልፍ ቃላትን የሚያዘምዱና የጥላቻ ንግግርን የሚለዩ ሞዴሎችን ተጠቅሟል። የማህበራዊ ሚዲያ ጣቢያው ከተፈጠረ ጀምሮ ያሉ ልጥፎች በሙሉ ቢካተቱም የመረጃ ስብስቡ ግን የተካሄደው እ.ኤ.አ ከመስከረም እስከ ታህሳስ 2004 ነበር። አንድ የአጥኚዎች ቡድን የተሰበሰቡትን የልጥፍ አስተያየቶች በሶስት አቅጣጫዎች ማለትም በጥላቻ ንግግር ኢላማ ፣አይነትና አውድ ከፋፍሏል። ( አባሪ 7.3፣ ትርጓሜ ፕሮቶኮል ወይም ክፍል 3.1 እና ሃሳባዊ ማዕቀፍ ይመልከቱ )

ናቹራል ላንጉች ፕሮሰሲንግ (Natural Language Processing) ቴክኒኮች ከማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ የጽሁፍ መረጃን ለመተንተንና ለመተርጎም ቁልፍ አካል ነበሩ። ይህም የቃላት ስብስብን መፍጠር፣ ከማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ መረጃን መሰብሰብ እና የተደጋገሙ መረጃዎችን ማስወገድና ከልጥፎች ላይ ማንነትን የሚገልፁ መረጃዎችን ማንሳት ያካተተ የቅድመ ዝግጅት ሂደትን ያካትታል። በተጨማሪም ሲ.አይ.አር ናቹራል ላንጉች ፕሮሰሲነግን (Natural Language Processing) ከእንግሊዘኛ መረጃ ስብስብ ውስጥ የጥላቻ ንግግሮችን ለመለየትና በሰው እጅ ለሚደረገው ትርጓሜ መረጃዎችን ለማጥራት ተጠቅሟል። በመጨረሻም ናቹራል ላንጉች ፕሮሰሲንግ (Natural Language Processing) ቴክኒክ በባለሙያ እጅ በተሰራው የመረጃ መከፋፈል ሂደት ወቅት የመለያ ንድፍን በማዘጋጀት ረገድ ጥቅም ላይ ውሏል። የሚከተሉት ክፍሎች እያንዳንዱ ሂደት በዝርዝር ያሳያሉ።


### 3.1 ሃሳባዊ ማዕቀፍ

ሲ.አይ.አር የጥላቻ ንግግርን ኢላማ ፣አይነትና አውድን ለመገምገም ከዚህ በፊት የነበረውን ሃሳባዊ ማዕቀፍ ተጠቅሟል። ግልፅ የሆነ "ኢላማ" እና "የጥላቻ አይነት" መኖሩ አንድን ይዘት የጥላቻ ንግግር ብሎ ለመመደብ አስፈላጊ ነው። የሲ.አይ.አር አጥኚዎች አንድን ይዘት "የጥላቻ ንግግር " ብለው የመደቡት የጥላቻ ንግግሩ ኢላማ (እንደ ፆታ ያለ ህጋዊ ከለላ የሚደረግለት ማንነት) እና የጥላቻ ንግግሩ አይነት በግልፅ የሚታወቅ ከሆነ ብቻ ነው። በተጨማሪም ሲ.አይ.አር ለተጨማሪ ትንተና የጥላቻ ንግግሮችን "አውድ" በጥናቱ አካቷል።

በዚህ ጥናት ውስጥ የተካተቱ የጥላቻ ንግግር ኢላማዎች [የኢትዮጲያ መንግስት] የጥላቻ ንግግርና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከታተልና ለመቆጣጠር ባወጣው አዋጅ ውስጥ ከለላ ያገኙ ማንነቶች ናቸው። ምንም እንኳን ጥናቱ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ላይ ያተኮረ ቢሆንም ለንፅፅር እንዲመች ሌሎች ህጋዊ ከለላ ያገኙ ኢላማዎችም በጥናቱ ውስጥ ተካትተዋል (ብዙ ኢላማዎች ያላቸው የጥላቻ ንግግሮች አሉ ለምሳሌ ፆታ እና ብሄር)።

በማዕቀፉ ውስጥ፣ "የጥላቻ ንግግር አይነት" የጥቃቱን ዘዴ (እንደ "ዛቻ" ያለ) ሲወክል አውድ ደግሞ የጥቃቱን ስሜትና የቋንቋ ባህሪ ይገልፃል (እንደ "ስላቅ " ወይም "አሳናሽ")። ለምሳሌ፣ ጥላቻ እንደ ስላቅ፣ ምፀት ወይም ፌዝ ባሉ የንግግር ዘይቤዎች ሊተላለፍ ይችላሉ። የእያንዳንዱ ምድብ ከዚህ በታች በምስል 1 ላይ ተያይዟል።

ይህ ሃሳባዊ ማዕቀፍ ለመረጃ ትርጓሜው ድጋፍ ከመስጠቱም በላይ የምርምሩን ግኝቶች ለመተርጎም አስፈላጊ ነው። ስለሃሳባዊ ማዕቀፉ የበለጠ ለመረዳት [የሲ.አይ.አር 2024 ሪፖርትን] ይመልከቱ። ይህ ሃሳባዊ ማዕቀፍ በምሁራን ተገምግሞ ተቀባይነት ያገኘና [በሪሶርስስ ፎር አፍሪካ ጆርናል (Resources for African Journal)] ላይ የታተመ ነው።




*ምስል 1: የሲ.አይ.አር ሃሳባዊ መዕቀፍ፡ ይህም ለጥናቱ ቀረፃና በክፍል 7.3 ለሚታየው የትርጓሜ ፕሮቶኮል መሰረት ነው*

## 3.2 የቃላት መረጣ

ሲ.አይ.አር በአራት ቋንቋዎች (አማርኛ፣ አፋን ኦሮሞ፣ ትግርኛ እና እንግሊዘኛ) 2058 ፀብ ጫሪ ቃላትን የያዘ የቃላት ስብስብ አዘጋጅቷል። እነዚህ ቃላቶች ፆታን፣ ብሄርን እና ሀይማኖትን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች ናቸው። ሲ.አይ.አር ይህ የቃላት ስብስብ በአሁናዊ የኢትዮጲያ ሁኔታ ሁሉን አቀፍ የቃላት ስብስብ ነው ብሎ ያምናል።

የቃላት ስብስቡ የተዘጋጀው በዴስክ ጥናት ማለትም ከዚህ በፊት የነበሩ የጥላቻ ንግግር ስብስቦችን በመለየትና በማሻሻል፣ ሲ.አይ.አር ባዘጋጀው ቃለ መጠይቆች ወቅትና እ.ኤ.አ በሐምሌ 2023 በተደረገው የባለሙያዎች ውይይት ወቅት የተነሱ ቃላትን በማሰባሰብ ነበር። ሙሉ የመረጃው ዝርዝር በጥናቱ መጨረሻ ላይ ተካቷል። ሲ.አይ.አር በፌስቡክ ፣ በቴሌግራም እና ኤክስ ላይ ባደረገው ጥናት ተመሳሳይ የቃላት ስብስብ ተጠቅሟል። ከእነዚህ

ቁልፍ ቃላቶች ውስጥ አንዱ መኖሩ ብቻ ፅሁፉን የጥላቻ ንግግር አያስብለውም። ይልቁንም፣ የጥላቻ ንግግር ሊሆኑ የሚችሉ ልጥፎች በባለሙያ እጅ እንዲለዩ ያግዛል።


### 3.3 የማህበራዊ ሚዲያ አካውንት መረጣ

ሲ.አይ.አር በኢትዮጲያ ውስጥ በስፋት ታዋቂ እና ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆኑ የዩትዩብ እና የቲክቶክ ቻናሎች ዝርዝር ለማዘጋጀት የኢትዮጲያ የማህበራዊ ሚዲያ ባለሙያዎችን አሳትፏል። በእነዚህ ቻናሎችና አካውንቶች ላይ ባሉ ተንቀሳቃሽ ምስሎች ላይ የተሰጡ አስተያየቶች ለትንተና ተመርጠዋል።

#### የአካውንት ክፍፍል

የሲ.አይ.አር ማህበራዊ ሚዲያ ባለሙያዎች የተመረጡትን ቻናሎችና አካውንቶች በዘውግ ከፋፍለዋል። ይህም በተንቀሳቃሽ ምስል ዘውጎችና የሚሰጡ አስተያየቶች መካከል ያለውን ግንኙነት ለመመርመር አስችሏል።የቻናል ክፍፍሉ ከታች በምስል 2 ላይ ይታያል። ኢንተርኔት ላይ በሚለጠፉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዓት ያላቸው ይዘቶች ምክንያት ቡድኑ እያንዳንዱን ተንቀሳቃሽ ምስል መመልከት አልቻለም። በምትኩ ከእያንዳንዱ ቻናል ወይም አካውንት ይዘት ላይ ናሙናዎች ተመልክቶ አጠቃላይ ግምገማ አድርጓል።

በተጨማሪም የጥናት ቡድኑ አባላት የዩትዩብ ቻናሉ ወይም አካውንቱ ከዚህ በፊት የታወቀ ጥቃት ፈጻሚ ወይም የጥቃት ሰለባ መሆኑንና የቻናሉን ባለቤት ፆታ ለይተዋል። ይህ የተደረገው በጥላቻ ንግግር ላይ የሚሳተፉ ቻናሎች ራሳቸው የተለየ አይነት የጥላቻ ንግግር እንደሚደርስባቸው ለመለየት ነው። ሲ.አይ.አር ቻናሉ ላይ የተገለፀው ፆታ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ተጨማሪ ምርመራ አላደረገም።




*ምስል 2: በሲ.አይ.አር የተሰራው የአካውንቶችና ቻናሎች ክፍፍል*

## 3.4 የመረጃ አሰባሰብና ዝግጅት

ሲ.አይ.አር ከዩቱዩብ እና ከቲክቶክ ላይ የልጥፎችን ናሙና ለመምረጥ ቁልፍ ቃላትን የሚያዛምዱና የጥላቻ ንግግርን የሚለዩ ሞዴሎች ተጠቅሟል። የመረጃ ስብስቡ እ.ኤ.አ ከመስከረም እስከ ታህሳስ 2024 የተካሄደ ቢሆንም የማህበራዊ ሚዲያ አካውንቱ ከተፈጠረ ጀምሮ የነበሩ ልጥፎች መረጃ ቋት ውስጥ ተካተዋል።

### 3.4.1 መረጃ አሰባበሰብ

ዩትዩብ

ሲ.አይ.አር ከ160 ዩቱዩብ ቻናሎች ላይ የተሰጡ አስተያየቶችን ለመሰብሰብ ፋይተን ላይብረሪ (Phyton library) የተባለ መተግበሪያ ተጠቅሟል። ይህም በተመረጠው ቻናል ላይ ያሉ ተንቀሳቃሽ ምስሎች ላይ ከተሰጡ አስተያየቶች ከ60–80% የሚሆኑትን ለመለየት አስችሏል። ይህንን አካሄድ በመጠቀም ሲ.አይ.አር 7,810,908 የዩቱዩብ አስተያየቶችን ሰብስቧል።

ቲክቶክ

ሲ.አይ.አር ኦፕን ሜዠርስ “Open Measures” የተባለ የኢንተርኔት ላይ መሳሪያ በመጠቀም ከ364 የቲክቶክ አካውንቶች ላይ አስተያየቶችን ሰብስቧል። በዚህ አካሄድ 1,515,932 የቲክቶክ አስተያየቶች መሰብሰብ ተችሏል። ኦፕን ሜዠርስ ”Open Measures” ቅርብ ከሆኑት 1000 የቲክቶክ ቪዲዮዎች ላይ አስተያየቶችን ሲሰበስብ በአንድ ቪዲዮ ላይ ከ 10,000 በላይ አስተያየቶችን አይሰበስብም። በስብስብ ውስጥ ካሉት ተንቀሳቃሽ ምስሎች ማናቸውም ከ 10,000 በላይ አስተያየት ስለሌላቸው ይህ ገደብ ጥናቱ ላይ ተጽዕኖ እንደማይፈጥር ሲ.አይ.አር ያምናል።

አስተያየቶቹ የተሰበሰቡት ከተለጠፉ ቆይቶ ስለሆነ በሁለቱም የማህበራዊ መድረኮች ላይ የመድረኮቹን ህግ የሚጥሱ አስተያየቶች ተወግደው ሊሆን ይችላል። ይህም ማለት አንዳንድ ጎጂ የሆኑ የኢንተርኔት ላይ አስተያየቶች በናሙና ውስጥ ላይካተቱ ይችላሉ።

### 3.4.2 የመረጃ ቅድመ ዝግጅት

ሲ.አይ.አር ቅድመ መረጃውን ለትንተና ወደሚመች የመረጃ አይነት ለመለወጥ የማፅዳት፣ የመለወጥና የማስተካል ቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ሰርቷል። ይህም የቋንቋ ሞዴሎችን ጥራትና አስተማማኝነትን ለማሻሻል እና ከፅሁፋዊ መረጃዎች ትርጉም ያለው ግንዛቤን ለማግኘት አስፈላጊ ነበር። ዋናዎቹ ተግባራት ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡

የፅሁፍ ፅዳት

ከማህበራዊ ሚዲያ የሚሰበሰቡ የጽሁፍ መረጃዎች ብዙን ጊዜ ትንታኔ ወይም አተረጓጎምን የሚያወሳስቡ፣ ተዛማጅነት የሌላቸው ወይም የተሳሳቱ መረጃዎችን ይይዛሉ። መረጃ ማፅዳት ስራው የሚከተሉትን ያካተተ ነበር፡

- Hypertext markup language (HTML) መለያዎችንና የተለያዩ ፊደላትን ማስወገድ፡ HTML መለያዎች የኢንተርኔት ገጾች መረጃን እንዴት ማሳየት እንዳለባቸው የሚነግሩ መለያዎች ናቸው።
- HTML መለያዎች ድህረገፆችን ለመቅረፅና ፅሑፎችን ምስላዊ ውክልና ለመስጠት ጠቃሚ ሲሆኑ ፅሁፎችን በምናዘጋጅበት ወቅት ግን ጥቅም የላቸውም።
- ሁሉንም ፅሁፎች ወደ እንግሊዘኛ ንዑስ ሆሄ (Small letter) መለወጥ፡ ቃላት ወጥ በሆነ ሁኔታ እንዲታዩ ያደርጋል። ለምሳሌ “apple”  “APPLE” እና “Apple” ከ “apple” ጋር በተመሳሳይነት ይታያሉ።
- ስርዓተ ነጥብን ማሰወገድ ወይም መተካት

- ስሜት ገላጭ ምስሎች (Emoji) አፅንኦት ለመስጠት ወይም ስሜትን ለመግለፅ ጥቅም ላይ ስለሚውሉ በእነዚህ ሂደቶች ወቅት አልተወገዱም።

የሚከተሉት የመረጃ ማፅዳት ስራዎች የተከናወኑት ለእንግሊዘኛና አማርኛ ቋንቋ የመረጃ ስብስቦች ብቻ ነው።

- የቁጥር ፊደላትን፣ ቁጥሮችን እና ሌሎች ፅሁፋዊ ያልሆኑ መረጃዎችን ማስወገድ
- በእንግሊዘኛ እንደ “And “፣ “The” እና “In” የመሳሰሉና ትርጉም የሌላቸውን አያያዥ ቃላትን ማስወገድ
- ምህጻረ ቃላትን መተንተን፡ ምህጻረ ቃላት ብዙን ጊዜ ጎጂ ይዘትን ለመደበቅ ያገለግላሉ።በመሆኑም ሁሉንም አይነት ፅሁፎች ወደ ተመሳሳይ ቅጽ መለወጥ የጥላቻ ንግግር የሚለዩ ሞዴሎችን አሰራር ለማሻሻል ይረዳል።

### 3.4.3 ለትንታኔ የሚሆኑ የመረጃ ናሙናዎችን መምረጥ

ሲ.አይ.አር ከተሰበሰቡት አጠቃለይ የአስተያየት ጥርቅም ውስጥ ናሙናዎችን በእጣ መርጦ ወስዷል፤ ይህም የተመረጡት ናሙናዎች አጠቃላይ የመረጃ ቋት ወካይ መሆናቸውን ያረጋግጣል። ይህንንም ለማረጋገጥ በሁሉም ቋንቋዎች ተመጣጣኝ ቁጥር ያላቸው አስተያየቶች ተመርጠዋል።

### 3.4.4 መረጃዎችን ሚስጥራዊ ማድረግ

ሲ.አይ.አር መረጃቸው ለምርምር እና ለጥናት ጥቅም እንዲውል የተመረጡ ግለሰቦችን ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ ከስነምግባር መርሆች ጋር በተጣጣመ መልኩ የተመረጡ ልጥፎችን ስም አልባ አድርጓል።
ይህ የተደረገው ሁሉንም የተጠቃሚ ስሞች (ማለትም ከ”@” ምልክት በኋላ ያለውን ማንኛውንም ቃል) “user name” በሚል ቃል በመተካት ነው።

### 3.4.5 ተመጣጣኝ መረጃ

ከናሙና መረጣ በኋላ የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተርጉመውና ተከፋፍለው መጠናቸው ከመቶኛ ተቀምጧል። ምንም እንኳን በመረጃ ቋቱ ውስጥ የተለያዩ የጥላቻ ንግግር ቁጥሮች ቢኖሩም ይህ አካሄድ የጥላቻ ንግግር አይነቶችና አውዶችን ለማነጻጸር ያስችላል።

## 3.5 መረጃዎችን ጥላቻ ብሎ መመደብ

ሲ.አይ.አር መረጃዎች በእጅ ከመተርጎማቸው በፊት አውቶማቲክ የሆነ የመመደቢያ ዘዴ ተጠቅሟል። ሲ.አይ.አር በጥሩ ሁኔታ የተሰራ የማሽን ለርኒንግ ሞዴልን (Machine learning model) ፅሁፎች የጥላቻ ንግግር እንደሚይዙ ለመለየት ተጠቅሟል። በመቀጠልም የጥላቻ ንግግር ያልያዙ ፅሁፎች ከመረጃ ስብስብ ውስጥ ተወግደዋል።

ሲ.አይ.አር እነዚህ ሞዴሎች በትግርኛና አፋን ኦሮሞ ቋንቋ ባለመኖራቸው ምክንያት ይህንን ሂደት በአማርኛ እና እንግሊዘኛ በተጻፉ መረጃዎች ላይ ብቻ ተጠቅሟል። በዚህም ምክንያት በአማርኛና እንግሊዘኛ ቋንቋ የተጻፉ የጥላቻ ንግግሮችን መለየት ቀላል ሆኖ ሊሆን ይችላል።

### 3.5.1 መረጃ ትርጓሜ

የትርጓሜ ፕሮቶኮሉን በመጠቀም ልምድ ያላቸው የሲ.አይ.አር ተርጓሚዎች 17,082 አስተያየቶች ተርጉመዋል (አባሪ 7.3 ይመልከቱ)። የቡድኑ አባላት የቋንቋ እውቀት በጥናቱ ውስጥ የተካተቱትን አራቱንም ቋንቋዎች ያካተተ ነበር፣ አፋን ኦሮሞ፣ አማርኛ፣ ትግርኛ እና እንግሊዘኛ። የተለያዩ ቋንቋዎች በሚናገሩ የቡድኑ አባላት መሃከል ወጥነትን ማረጋገጥ ቁልፍ ነበር። ይህንን ለማረጋገጥ የሲ.አይ.አር ሃሳባዊ ማዕቀፍ የጥላቻ ንግግርን ፣ኢላማዎቹን

፣አይነቶቹንና አውዶቹን ለመለየት ግልጽ መግለጫዎችን ይሰጣል ( ክፍል 3.1 ይመልከቱ)። ፕሮቶኮሉ ሃሳባዊ ማዕቀፉ እንዴት እንደሚተረጎም የሚያሳዩ ምሳሌዎችንም ይዟል።

ደካኖ የተባለ መተግበሪያን በመጠቀም ተርጓሚዎች አስተያየቶችን በኢላማ (ፆታ፣ሀይማኖት፣ዘር ፣አካል ጉዳተኝነት)፣ በአይነትና እና በአውድ (ክፍል 3.1 ይመልከቱ) ከፋፈሉ ። ምድቦቹ ሙሉ ለሙሉ የተለያዩ አልነበሩም ማለትም አንድ የጥላቻ ንግግር ለምሳሌ በፆዝ እና ፀብጫሪ ምድብ ውስጥ ሊመደብ ይችላል።

## 3.6 አውደ ጥናቶች

ሲ.አይ.አር ኢ.ኤ.አ በነሀሴ እና ህዳር 2024 እና በጥር 2025 ከባለድርሻ አካላት ጋር በኢንተርኔትም በአካልም ተከታታይ አውደ ጥናቶችና ስብሰባዎች በአዲስ አበባ አካሂዷል። ስብሰባዎቹ መነሻ ግኝቶችን እና ሀሳቦችን ለማጋራትና ለመወያየት ያስቻሉ ሲሆን ጠቃሚ የሆኑ ምክረ ሀሳቦችን ለመዳሰስም መድረክ ሰጥተዋል። የአውደ ጥናቶቹ ተሳታፊዎች 60% ሴቶችና 40% ወንዶች ሲሆኑ ግለሰቦቹ የሴቶችና ልጃገረዶችን መብቶች ፣ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች (ኢንተርኔት ላይና ከኢንተርኔት ውጪ) እና የኢንተርኔት ላይ ደህንነትን ጨምሮ በርካታ የሠብዓዊ መብት ጉዳዮችን አንስተዋል።

ሲ.አይ.አር በርዕሠ ጉዳዩ ላይ እውቀት ካላቸው ባለሙያዎች ጋር ለመወያየት እና በጉዳዩ ላይ በኢትዮጲያ ውስጥ እንዴት ምርምር ማድረግና ምላሽ መስጠት እንሚቻል ለማወቅ ፈልጎ ነበር። በአውደ ጥናቱ ላይ የተሳተፉትን ግለሰቦች ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ስማቸው እንዳይገለፅ ተደርጓል።

## 3.7 ውስንነቶች

በተቻለ መጠን ሲ.አይ.አር የአሰራር ሂደቱንና የግኝቶቹን ውስንነት ለመቀነስ እርምጃዎች ወስዷል። ሆኖም ከዚህ በታች የተዘረዘሩ በርካታ የግብዓት፣ የዓውድና የውጤት ውስንነቶችን መገንዘብ ያስፈልጋል።

*ቋንቋዎች*

ኢትዮጲያ ውስጥ ከ80 በላይ ቋንቋዎች ይነገራሉ። እነዚህ ሁሉ ቋንቋዎች በማህበራዊ ድህረ-ገጾች ላይ ባይወከሉም ለዚህ ጥናት አራት ቋንቋዎችን መምረጥ ያስፈለገው በግብዓት እና ጊዜ ውስንነት ብቻ ነበር። በዚህም ምክንያት በማህበራዊ ድህረ-ገጾች ላይ በሰፊው ጥቅም ላይ የሚውሉ አራት ቋንቋዎች ማለትም አማርኛ ፣ አፋን ኦሮሞ፣ ትግርኛ እና እንግሊዘኛ ቋንቋዎች ተመርጠዋል። ስለዚህም እነዚህ ግኝቶች በማህበራዊ ሚዲያ ላይ የአራቱን ቋንቋዎች ናሙና ይወክላሉ። ይህ ሆኖ ሳለ ጥናቱን በአራት ቋንቋዎች ለማካሄድ ቋንቋዎቹን፣ ዐውደ ፅሁፉን እና የማህበራዊ ሚዲያ ትንታኔዎችን ጠንቅቀው የሚያውቁ ተመራማሪዎች አስፈልጓል። የወደፊት ጥናቶች በተለያዩ ቋንቋዎች ላይ ተመሳሳይ ምርምሮችን ለማካሄድ የሲ.አይ.አርን የጥናት ዘዴ ሊከተሉ ይችላሉ።

*የመረጃ አሰባሰብ*

ሲ.አይ.አር የእያንዳንዱ ማህበራዊ ሚዲያ መድረክ ደንቦችና ሁኔታዎች ለማክበር ለሁሉም ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች የተለየ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ተጠቅሟል። ይህ አስፈላጊ የነበረ ቢሆንም ከእያንዳንዱ መድረክ ላይ የተለያየ መጠን ያላቸው መረጃዎች እንዲሰበሰብ አድርጓል። በዚህም ምክንያት ሲ.አይ.አር በዩቱዩብና በቲክቶክ ላይ ያለውን የጥላቻ ንግግር መጠን ማወዳደር አልቻለም። ይልቁንም በእያንዳንዱ መድረክ ያለውን የጥላቻ ንግግር አይነትና አውድ በመቶኛ ማወዳደር ተችሏል።

በመጀመሪያ የቲክቶክ መረጃ ማሰባሰብ ሂደት ወቅት በትግርኛ ቋንቋ ከሌሎች ሶስት ቋንቃዎች ያነሱ አስተያየቶች ተሰብስቧል። ሲ.አይ.አር ትግርኛ ተናጋሪ የሆኑ የቲክቶክ አካውንቶች በበቂ ሁኔታ አልተወከሉ እንደሆነ ለማየት ተጨማሪ አካውንቶችን በንቃት አስሷል። ነገር ግን ይህ መረጃ ቋቱ ውስጥ ያለውን የትግርኛ ቋንቋ መጠን

አልጨመረውም። ሲ.አይ.አር ከሁሉም ቋንቋዎች ላይ እኩል ናሙናዎችን ስለወሰደ ይህ የትግርኛ ቋንቋ ውክልና ላይ ተፅዕኖ አላሳደረም። የትግርኛ ቋንቋ ቲክቶክ አስተያየቶች አለመብዛታቸው ምናልባት በቲክቶክ ላይ ያለውን ወቅታዊ ይዘት ሊያንፀባርቅ ይችላል። ምክንያቱም በዩቱዩብ መረጃ ስብስብ ውስጥ ይህ አልተስተዋለም። የአውደ ጥናት ተሳታፊዎች ይህ የሆነበት ምክንያት በትግራይ ክልል ያለው ውስን የኢንተርኔት ግንኙነት፣ ያነሰ የመሰረተ ልማት እውታርና ቲክቶክ ጠንካራ የሆነ የኢንተርኔት ግንኙነት መፈለጉ ሊሆን እንደሚችል ገልጸዋል።

ግኝቶቹን ከቀዳሚው ጥናት ጋር ለማወዳደር በቲክቶክና በዩቱዩብ ተንቀሳቃሽ ምስሎች ላይ በተሰጡ አስተያየቶች ዙሪያ ፅሁፋዊ ትንታኔ ተካሄዷል። ሲ.አይ.አር የማህበራዊ ሚዲያ ተተቃሚዎች የሚያጋሯቸውን የይዘት አይነቶች ለመወሰን እያንዳንዱን ቻናል ገምግሟል፤ ነገር ግን እያንዳንዱን ተንቀሳቃሽ ምስል ለመተንተን በቂ ጊዜ ባለመኖሩ ሙሉ የተንቀሳቃሽ ምስል ትንተና ማድረግ አልተቻለም። ወደ ፊት የሚደረጉ ጥናቶች በተንቀሳቃሽ ምስሎቹ ውስጥ ያሉትን ይዘቶች በራሳቸው ሊያጠኑ ይችላሉ።

*የመረጃ ዝግጅት*

ከመረጃ ቋት ውስጥ ናሙና ከመወሰዱ በፊት ሲ.አይ.አር የሰለጠነ የማሽን ለርኒንግ ሞዴልን (Machine Learning Model) በመጠቀም "ጥላቻ አይደሉም" ተብለው የተፈረጁ ልጥፎችን አጣርቶ በማውጣት የጥላቻ ንግግሮችን የማግኘት እድልን አስፍቷል። በትግርኛና በአፋን ኦሮሞ እነዚህን የሚሰሩ የሰለጠኑ ሞዴሎች ባለመኖራቸው ምክንያት ይህ የቅድመ ዝግጅት ሂደት በአማርኛና እንግሊዘኛ ቋንቋዎች ላይ ብቻ ተደርጓል።
ሆኖም ግን በእነዚህ ቋንቋዎች የተተረጎሙት የሲ.አይ.አር መረጃ ስብስቦች የማሽን ለርኒግ ሞዴሎችን (Machine learning model) ለወደፊት ጥናቶች ለማሰልጠን ጥቅም ላይ ይውላሉ። በተጨማሪም እነዚህ ሞዴሎች በማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ የጥላቻ ንግግርን በራሳቸው የመለየት አቅም ስላላቸው ለማህበራዊ መድረክ ይዘት ቁጥጥር ሊያግዙና በእነዚህ ቋንቋዎች የጥላቻ ንግግር እንዲቀንስ ሊያደርግ ይችላል።

በተጨማሪ ተመራማሪዎች በኢትዮጲያ የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ ከፍተኛ መጠን ያለው የፖለቲካ የጥላቻ ንግግርን ተመልከተዋል። ሆኖም እነኚህ ንግግሮች ከኢትዮጲያ መንግስት የጥላቻ ንግግር ትርጓሜ ወጪ ስለሆኑ በጥናቱ ውስጥ አልተካተቱም። በተመሳሳይ "ኢሳት የኦሮሞ ህዝብ ቁጥር 1 ጠላት ነው" የሚሉና የመሳሰሉ የሚዲያ ድርጅቶችን ኢላማ ያደረጉ ፅሁፎች በብዛት ቢታዩም ኢላማቸው ግለሰብ ስላልሆነና የጥላቻ ንግግር መስፈርትን ስለማያሚሉ በጥናቱ ውስጥ አልተካከቱም።

*የቋንቋ ድርብነት*

የቃላት ድርብ ትርጉም መያዝ ሌላ የጥላቻ ንግግር ለመተርጎም የሚደረርገውን ጥረት ያወሳሰበ ሁነት ነው። ለምሳሌ በእንግሊዘኛ "Bitch" የሚለው ቃል ዖታዊ ስድብ እንደሆነ ቢታወቅም አንዳንድ ጊዜ እንደ "Go Bitch" ባሉ ሀረጎች ውስጥ በአዎንታዊ መልኩ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። እነዚህ ነገሮች የአውድን አስፈላጊነትና የመረጃ ተርጓሚዎች እውቀትን ጠቃሚነት ያሳዩ ናቸው።

*ጠቃሚ መረጃዎችን መለየትና የዲያስፖራው ተፅዕኖ*

የቲክቶክ መረጃ ስብሰብ የመጣው ከኢትዮጲያን አካውንቶች ብቻ ነው። ይሁን እንጂ እነዚህ አካውንቶች "ኢትዮጲያዊያን "ተብለው ቢገለፁም ፣ የዲያስፖራ ኢትዮጲያዊያን ሊሆኑ ይችላል። ሲ.አይ.አር መረጃዎችን አጥንቶ የዲያስፖራ አካውንቶችን ከመረጃ ስብስብ ውስጥ አስወግዷል። ይህ በተለይ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ይዘቶች ላይ ጎልቶ ይታይ ነበር። መረጃው እንደሚያመለክተው አብዛኞቹ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች በአሜሪካ፣ በካናዳ እና በፈረንሳይ ውስጥ ይገኛሉ ። ምክንያቱም አብዛኞቹ በእነዚህ ሀገራት ውስጥ ስላለው የፖለቲካ ሁኔታ አስተያየት ይሰጣሉ። ለምሳሌ ብዙ አስተያቶች አሜሪካዊቷ ኮሚዲያን ካቲ ግሪፊን ከተመራጭ ፕሬዝዳንት ዶናልድ ትራንፕ ጋር ተመሳስሎ ከተሰራ ጭንቅላት ጋር ስለተነሳችው ፎቶ አስተያየቶች ሲሰጡ ነበር። በተመሳሳይ ብዙዎቹ

አስተያየቶች ታዋቂውን የአሜሪካ ፖለቲካ ተፅዕኖ ፈጣሪ ሃሪ ሲሠንን ማንሳታቸው በኢትዮጲያና አሜሪካ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች መካከል ተቀራራቢ መድረክ መኖሩን ያሳያል። ሲ.አይ.አር የመረጃ ስብስቡን በማጥራት የሚከተሉትን ቃላት አስወግዷል። ትራምፕ ፣ዋልዝ፣ ሃሪ፣ ጄዲ፣ ቨንስ፣ ቪቪክ፣ ዴሞክራቶች እና "demontats"። የመረጃ ስብስቡን ጠቃሚነት ለማሻሻል ሲባል እነዚህ ቃላት የያዙ ልጥፎች ተወግደዋል።

---

# 4. ውጤቶችና ማብራሪያዎች

ይህ ጥናት ሲ.አይ.አር ከዚህ በፊት የሰራውን ጥናት ወደ ሁለት ተጨማሪ ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ማለትም ዩቱዩብና ቲክቶክ በማስፋት በኢትዮጲያ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ዙሪያ ያለውን ግንዛቤ ለማጠናከር ያለመ ነው። በሲ.አይ.አር ቀደምት ጥናት ላይ በመመርኮዝ ይህ ጥናት ሴቶችና ልጃገረዶች ላይ የሚሰነዘረውን የጥላቻ ንግግር **አይነትና ዓውድ** ያጠናል። ለምሳሌ **አፀያፊ፣ በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የተሳሳቱ አመለካከቶችን የያዙ፣ ፀብጫሪ ወይም ፌዝ**። በተጨማሪ ሲ.አይ.አር በሴቶችና ልጃገረዶች ላይ የሚደርሰውን በደል በወንዶች ላይ ካነጣጠሩ ጥቃቶች ጋር አወዳድሯል።

ሲ.አይ.አር በተጨማሪም ሴቶችና ልጃገረዶች በፆታቸው ላይ ብቻ ሳይሆን እንደ ብሄር ወይም ሀይማኖት ባሉ ሌሎች ጥበቃ ያገኙ ማንነቶቻቸው ላይ ጥቃት ሲነዘር ያለውን ልዩነት መርምሯል (ክፍል 4.4 ይመልከቱ)። መረጃው ውስጥ ሌሎች **የጥላቻ ኢላማዎችን** በማካተት፣ ሲ.አይ.አር ጥቃቶች በሴቶችና በልጃገረዶች ላይ ሲደርስ ወይም በግለሰቦች ብሔር፣ ሀይማኖት ወይም ዘር ሲደርስ እንዴት እንደሚገለፅ ማወዳደር ችሏል (ክፍል 45)።

በተጨማሪ ሲ.አር.አይ በተለያዩ **ይዘት ዘውጎች** ላይ ባደረገው ጥናት (ክፍል 4.6) ሴቶችና ልጃገረዶች የተለየ ጥቃት እንደሚደርስባቸው ተመልክቷል።

በአውድ ጥናቱ ወቅት ተሳታፊዎች በቲክቶክና ዩቱዩብ ዙሪያ ያላቸውን ልምድና መድረኮቹ ለጥላቻ ንግግር በር የሚከፍቱበትን ልዩ ባህሪ አብራርተዋል። የጥናቶቹን ውጤቶች ከመግለፅ በፊት ስለእነዚህ ልዩ ባህሪያት እንደሚከተለው ማብራሪያ ተሰጥቷል (ክፍል 4.1)። ከሲ.አይ.አር ቀደምት ጥናት ላይ የተገኙ ግንዛቤዎች፣እንዲሁም በቃለ መጠይቆች፣ በውይይቶችና በዓውደ ጥናቶች የተገኙ ግኝቶች ለትንታኔው ጥልቀት ጨምረዋል። የሚከተለው መረጃ በጥላቻ ንግግር አይነቶች ላይ ለማተኮር እንዲመች መጠኖችን ከመቶኛ ይገልጻል።

## 4.1 መድረኮቹ

የተደረጉ አውደ ጥናቶች ቲክቶክና ዩቱዩብ ላይ በሚደርሱ ጥቃቶች መሃከል ልዩነት መኖራቸውን አሳይተው ለእነዚህ ልዩነቶች ምክንያት ጠቁመዋል። እንደሚከተለው የቀረቡት ሀሳቦች የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች ሲሆን በግል ሲ.አይ.አር ያረጋገጣቸው አይደሉም።

ተሳታፊዎቹ እንደገለፁት ቲክቶክ ተቃርኖን የሚያባብስ ስራት ሲኖረው ዩቱዩብ ደግሞ ፖለቲካዊ የሆኑ፣ ብሄርና ፆታን የሚነኩ ጥቃቶችን እንደሚያስተናግድ ገልፀዋል። በይዘት ቁጥጥር ሂደት ላይ ያለው እምነት ማጣት፣ በቅርብ የተደረጉ የቁጥጥር ፖሊሲ ለውጦችና በመድረኮች መሃከል ያለው የይዘት ሽግግር ጥቃቶችን ለማስቆምና ለሴቶችና ሌሎች የተገለሉ ቡድኖች ደህንነቱ የተጠበቀ የኢንተርኔት መድረክ ለመፍጠር፣ አጠቃላይና መድረክ-ተኮር እርምጃዎች እንደሚያስፈልጉ ማሳያ ናቸው። የጥላቻ ንግግርን ለመከላከል የወጡ መመሪያዎች ቢኖሩም አፈጻጸማቸው ግን ደካማ ነው። ከማህበራዊ ሚዲያ ኩባንያዎች ጠንከር ያለ እርምጃ ይጠበቃል።

### 4.1.1 ቲክቶክ

የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች በቲክቶክ ላይ የጥላቻ ንግግር እና ጎጂ ይዘት መስፋፋት ላይ ከፍተኛ ስጋት እንዳላቸው ገልጸዋል። ቲክቶክ ከሁሉም ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች በበለጠ ከፍተኛ የሆነ የጥላቻ ንግግር እና ማስፈራሪያዎችን እንደሚያስተናግድ አስረድተዋል። ቲክቶክ በሴቶች እና ሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ዘንድ ያለውን ታዋቂነት ግምት ውስጥ በማስገባት ተሳታፊዎች በዚህ የማህበራዊ ሚዲያ መድረክ ላይ የሚደረጉ ጥቃቶች ከሌሎች የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ጋር ሲነፃፀሩ ግለሰብን በቀጥታ የሚያጠቁ መሆናቸውን አስተውለዋል።

የቲክቶክ ስሪት በተቃራኒ ሀሳቦች መካከል ያለውን ውጥረት ይጨምራል

ቲክቶክ በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ ተቃራኒነት ያላቸው ሀሳቦችን የሚያስተናግድ መድረክ ነው። በባለሙያ እጅ በተከናወነው መረጃ ትርጓሜ ወቅት ሲ.አይ.አር እንደ "አንቺ ንግሥት!" እና "ጎበዝ በርቺ!" ያሉ ብዙ አዎንታዊ የወዳጅነት እና የጓደኝነት መስተጋብሮችን አስተውሏል። በተቃራኒው በዚሁ መድረክ ጉልህ የጥላቻ ንግግር ይታያል። የአውደ ጥናት ተሳታፊዎችም የቲክቶክ መድረክ እነኚህን ከፍተኛ ተቃራኒነት ያላቸው ሀሳቦች የሚያስተናግደው ተከታዮችን ለመሳብ እንደሆነ ይገልፃሉ። ብዙ የቲክቶክ ተንቀሳቃሽ ምስል ሰሪዎች የተመልካች ቁጥራቸውን ለማሳደግ፣ ትኩረትን የሚስብ እና አወዛጋቢ ይዘትን ይመርጣሉ:: ይህ ደግሞ የማህበራዊ ሚዲያ መድረኩን አሉታዊ ተፈጥሮ ያባብሰዋል። በመሆኑም የጥናቱ ተሳታፊዎች የቲክቶክ ይዘት ፈጣሪዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍተኛ ተቃራኒነት ያላቸው እና አፀያፊ ሀሳቦችን እየጨመሩ፣ ይዘቶቹ እና አስተያየቶቹም በሰፊው ተቀባይነት እያገኙ እንደሆነ ተሰምቷቸዋል። ለምሳሌ ይዘቶቹ ብዙውን ጊዜ ወንዶች እና ሴቶችን በማወዳደር ያልተገባ ንፅፅርን ያጠናክራሉ። በተጨማሪም፣ የቀልድ ይዘት ያላቸው ቪድዮዎች ብዙውን ጊዜ የጥላቻ ንግግርን እና አድሎአዊ አመለካከቶችን እያስለመዱ መጥተዋል። በአጠቃላይ ተሳታፊዎች የቲክቶክን የይዘት ስነ-ምህዳር መከፋፈልንም አንድነትንም የሚያበረታታ አድርገው ይመለከቱታል። ይህም ግለሰብ ላይ የሚደረግ ጥቃትን እና የኢንተርኔት የጥላቻ ንግግርን ያባብሳል።

### 4.1.2 ዩትዩብ

የአውደ ጥናት ተሳታፊዎች ዩትዩብ በበለጠ በታዋቂ ግለሰቦች ላይ የተሳሳቱ፣ ሀሰተኛ መረጃዎችን እና የስም ማጥፋት ዘመቻዎችን እንደሚያስተናግድ ገልፀዋል:: የዩትዩብ ይዘት ብዙ ጊዜ በታዋቂ ግለሰቦች ዙርያ ፖለቲካዊ ንግግሮችን በማቀጣጠቃል የሚደርስባቸውን ጥቃት እንደሚጨምር ጠቁመዋል።

ዩትዩብ በይበልጥ ፖለቲካዊ፣ ብሄር ተኮር እና ፆታዊ ጥላቻን ያስተናግዳል

በአጠቃላይ፣ ሲ.አይ.አር በዩትዩብ ላይ ፖለቲካዊ፣ ጎሳዊ እና ፆታዊ ጥላቻን አስተውሏል። ጥላቻውም ከሌሎች የማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፅ በበለጠ ዛቻ ያለውና እና ፀብ ጫሪ ነው። የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎቹ የዩትዩብ ረጅም ተንቀሳቃሽ ምስሎችን የማስተናገድ አቅም ጠለቅ ያሉ ሀሳቦች እንዲነሱና፣ ሰፊ ውይይት ለማድረግ ቢያስችልም ለከፋ እና አደገኛ ጥቃት እንደሚያጋልጥ ግን ጠቅሰዋል። የፖለቲካ ይዘት ያላቸው ውይይቶች መብዛት ጥልቅና ሥር የሰደዱ የዘር ወይም የፆታ አስተሳሰቦች ተመልሰው እንዲመጡ ያደርጋል። ለምሳሌ፣ ሲ.አይ.አር ፖለቲካን ያማከለ የብሄር ወይም የፆታ ጥቃት እንደ አብይ አህመድ፣ ሽመልስ አብዲሳ፣ እንዲሁም ቤቲ 'ቤቲ ሾው' እና አዳነች አቤቤ በመሳሰሉት ታዋቂ ግለሰቦች ላይ አግኝቷል።

ለምን ከፍ ያለ የጥቃት ደረጃ ዩትዩብ እንደሚያስተናግድ የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ ዩትዩብ ላይ የሚቀርቡት ቀስቃሽ እና የተሳሳቱ መረጃዎች ስሜትን የሚነኩ ስለሆኑ ሊሆን እንደሚችል አስረድተዋል::

### 4.1.3 የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ተጠቃሚነት

የማህበራዊ ሚዲያ ተደራሽነት ሁሉም አካባቢዎች ላይ እኩል አይደለም። ይህም በገጠር እና በከተማ መካከል ያለው የተደራሽነት ልዩነት በበለጠ በቲኪቶክ እና ዩትዩብ አጠቃቀም ላይ ጎልቶ ይታያል:: ምክንያቱም የቲክቶክ እና ዩትዩብ ከፍተኛ የኢንተርኔት ፍጆታ አስተዋፅዖ እንዳለው የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች አመላክተዋል:: በተጨማሪም፣ አንዳንድ የአገሪቱ አካባቢዎች በተለይም ከግጭት የሚያገግሙ አካባቢዎች ላይ የኢንተርኔት አገልግሎት መቋረጥ እና የኢንተርኔት መሠረተ ልማት ብልሽት የማህበራዊ ሚዲያ ተደራሽነትን የበለጠ ይገድባል።

### 4.1.4 የይዘት ቁጥጥር

ምንም እንኳን 93% የቲክቶክ እና 87% የዩትዩብ ተጠቃሚዎች በአውደ ጥናቱ ወቅት የስርዓተ-ፆታ የጥላቻ ንግግሮችን ማየታቸውን ቢዘግቡም ከመካከላቸው ሪፖርት ያደረጉት 47 እና 40 ፐርሰንቶቹ ብቻ ናቸው:: የተቀሩት ምንም እርምጃ እንዳልወሰዱ ወይም ለጓደኞቻቸው እንደነገሯቸው ገልፀዋል። በቅሬታ ማቅረቢያ መንገዶች እና የይዘት ቁጥጥርን በማሻሻል ዙሪያ የተደረጉ ውይይቶች የሚከተሉትን ጭብጦች አንስተዋል፡ ውጤታማ ያልሆነ የይዘት ቁጥጥር፣ እምነት ማጣት፣ በኢትዮጵያ ያለው የሲቪክ ምህዳር እየቀነሰ መምጣት እና ከአንድ የማህበራዊ ሚዲያ መድረክ ወደሌላኛው የሚካሄድ የይዘት ስርጭት ተጽእኖ።

ውጤታማ ያልሆነ የይዘት ቁጥጥር እምነትን ማሳጣቱ

በአውደ ጥናቱ ውስጥ በተደጋጋሚ ሲነሳ የነበረው ስጋት በቲክቶክ እና በዩትዩብ ላይ ያለው የይዘት ቁጥጥር ውጤታማ አለመሆን ነው። ብዙ ተሳታፊዎች ሪፖርት ያደረጓቸው ቪድዮዎች ከኢንተርኔት እንደማይወገዱ እና አንዳንድ ተሳታፊዎችም በማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች እርምጃ አለመውሰድ በመበሳጨታቸው በአጠቃላይ ሪፖርት ማድረግ እንዳቆሙ ገልፀዋል። ጎጂ የሆኑ ይዘቶችን ሪፖርት ማድረጋቸውን የቀጠሉትም እንኳን ተስፋ እየቆረጡ መጥተዋል። አንድ ተሳታፊ ለሲ.አይ.አር እንደተናገሩት የቲክቶክ አካውንታቸውን ሌላ ተጠቃሚ አስመስሎ በመክፈቱ ለቲክቶክ ሪፖርት ቢያደርጉም መመሪያ አልተጣሰም የሚል መልዕክት ደርሷቸዋል። የአስመሳዩ አካውንትም ይህ አውደ ጥናት እስከተደረገበት እ.ኤ.አ መስከረም 2025 ድረስ አልታገደም::

በርካታ ተሳታፊዎች በቲክቶክ ላይ የጥቃት ወይም ወሲባዊ ይዘትን ሪፖርት ቢያደርጉም የተሰጣቸው ምላሽ ግን ሪፖርት የተደረገው ይዘት የቲክቶክን መመሪያዎች የሚጥስ እንዳልሆነ ነው። ተሳታፊዎችም ይህ በቂ ምላሽ እንዳልሆነ እና በፖሊሲ ወይም ይዘት ግምገማ ዘዴ ላይ ከፍተኛ ክፍተት እንዳለ ይጠቁማሉ። የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች እነዚህ የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች የተለያዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን የያዙ ቪድዬዎችን ለመገምገም ተገቢው መሳርያ ወይም የሰው ሀይል እንደሌላቸው ገልጸዋል። ይህም በይዘት ግምገማው ላይ ላይ እምነት ማጣትን አስከትሏል።

ከአንድ የማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፅ ወደሌላኛው የሚካሄድ የይዘት ስርጭት ተጽእኖ

በተለያየ አሰራራቸው ምክንያት እያንዳንዱን የማህበራዊ ሚዲያ መድረክ ነጣጥሎ ማየት አስፈላጊ ቢሆንም፣ የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች ግን ከአንዱ የማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፅ ወደሌላኛው እየተሰራጨ የመጣው ጥላቻ በተመለከተ ስጋታቸውን ገልጸዋል። ከቲክቶክ እና ዩትዩብ የሚመጡ ጎጂ ይዘቶች እንደ ኤክስ፣ ኢንስታግራም፣ ፌስቡክ እና ቴሌግራም ባሉ የማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ላይ በቀላሉ ሊጋሩ ይችላሉ። ይህም የተናጠል የማህበራዊ ሚዲያ መድረክ ይዘት ግምገማ ውጤማነትን ይቀንሳል:: ይህም ሁሉን አቀፍ የሆነ ጎጂ ይዘቶችን የሚቆጣጠር አሰራር መዘርጋት እንዳለበት ያመላክታል::

የጥላቻ ንግግርን የሚቆጣጠሩ የማህበራዊ ሚዲያ መድረክ መመሪያዎች ቢኖሩም ተፈፃሚነታቸው በቂ አይደለም። ስለዚህ የማህበራዊ ሚዲያ ኩባንያዎች ተጠቃሚዎችን በተለይም ሴቶችን እና የተገለሉ ማህበረሰቦችን ለመጠበቅ ጠንከር ያሉ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው።

የይዘት ቁጥጥር ለውጦች

በኤክስ እና ሜታ የይዘት ግምገማ ፖሊሲዎች ላይ የተደረጉ ለውጦች የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎችን ስለወደፊቱ ሁኔታ ስጋት እንዲኖራቸው አድርጓቸዋል። ለምሳሌ፣ ኤክስ እ.ኤ.አ በጥቅምት 2022 ከተሸጠ በኋላ የይዘት ግምገማ ቅነሳና እና በነጻነት የመናገር መብት ላይ ያተኮሩ ስራዎችን ሰርቷል:: እንዲሁም እ.ኤ.አ ሜታ በመስከረም 2025 የሶስተኛ ወገን እውነት አረጋጋጭነትን አስወግዷል። ይህ ማለት ድረ-ገጾቹ አውቶማቲክ የይዘት መቆጣጠርያን ይጠቀማሉ፣ ይህም ሀገር በቀል በሆኑ እንደ አማርኛ፣ አፋን ኦሮሞ እና ትግርኛ ባሉ ቋንቋዎች የሚለጠፉ ይዘቶችን ለመቆጣጠር ውጤታማነቱ አነስተኛ ነው። የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎችንም ቲክቶክ እና ዩትዩብ የኤክስን እና ሜታን ዘዴ እንዳይከተሉ ፍራቻቸውን ገልፀዋል:: ይህ ከአንድ የማህበራዊ ሚዲያ መድረክ ወደ ሌላ የማህበራዊ ሚዲያ መድረክ የይዘት ዝውውር ባይኖር እንኳን በትንሹም ቢሆን በዩትዩብ እና በቲክቶክ ላይ ተጽዕኖዎች ሊኖሩ ይችላሉ።

ይህ ለውጥ መሰረቱ የመናገር መብትን የሚያበረታታ ነው ቢባልም፣ የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች ግን ይህ ለውጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ የሀሳብ ተቃራኒነትን መጨመርና የተሳሳቱ መረጃዎች መስፋፋትን እንደሚያመጣ ገልፀዋል። እነዚህ ስጋቶች ያደሩት በአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች ብቻ ሳይሆን በአለምአቀፍ ደረጃም ብዙ አስተያየት ሰጪዎችን ተመሳሳይ ሀሳቦችን ያንፀባርቃሉ። ይህ ጥናት በተናጠል የሚያሳየው አሁን ያለው የይዘት ቁጥጥር በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሴቶችን እና ልጃገረዶችን እንዲሁም ሌሎች ቡድኖችን ደህንነት መጠበቅ አለመቻሉን ነው።

## 4.2 ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረገ ፆታን መሰረት ያደረገ የጥላቻ ንግግር

ይህ ጥናት በማህበራዊ ሚዲያ መድረክ እንዲሁም በአጠቃላይ ኢንተርኔት ላይ ሴቶች እና ልጃገረዶች እንዴት የጥላቻ ንግግር አላማ እነደሚሆኑ ያሳያል። ክብራቸውንና እና ሰብአዊነታቸውን የሚነኩ እንዲሁም አስተሳሰባቸውን፣ በማህበረሰብ ውስጥ ያላቸውን ቦታ ወይም የአካላዊ ጥንካሬያቸውን ዝቅ በሚያደርጉ መልዕክቶች ጥቃት ገጥሟቸዋል። ጥቃት አድራሺዎችም ስላቅ እና ፌዝን በመጠቀም ሴቶችን ዝቅ ለማድረግ ይሞክራሉ። ዛቻ አዘል እና ሀይለቃል ንግግሮች ብዙ ባይሆኑም በሴቶች ኢንተርኔትም ሆነ በአካል ደህንነት ላይ ከባድ ተፅዕኖ ይፈጥራሉ።

በዩትዩብ እና በቲክቶክ ላይ የሚታዩት 'የጥላቻ አይነቶች' ተመሳሳይነት ያላቸው ቢሆኑም፣ የጥላቻ ንግግሮቹ አውድ ላይ ግን ጉልህ ልዩነቶች ነበሩ። በተጨማሪም፣ ከሲ.አይ.አር ቀደምት ጥናት ጋር ሲነፃፀር የጥላቻ አይነቶቹ በፌስቡክ፣ በቴሌግራም፣ በኤክስ ፣ በዩትዩብ እና በቲክቶክ ላይ ልዩነት አላቸው:: ይህም የሚያሳየው ለሴቶች እና ልጃገረዶች ደህንነቱ የተጠበቀ የኢንተርኔት መንደር ለመፍጠር ሰፋ ያሉ ስልቶች እና እያንዳንዱን የማህበራዊ ሚዲያ መድረክ ያማከለ እቅድ መነደፍ እንዳለበት ነው።

ሲ.አይ.አር በፆታዊ ሚና ዙሪያ ያሉ የተሳሳቱ አስተሳሰቦች እና ከሴቶች ማህበረሰባዊ ሚና ጋር የተያያዙ ትችቶችን ጨምሮ በሚደርሱት ጥቃቶች ውስጥ ቁልፍ የሆኑ አስተሳሰቦችን ለይቷል። በአመራር ውስጥ ወይም ስፖርት ውስጥ ያሉ ሴቶችን ጨምሮ የተሳሳቱ ማህበራዊ ልማዶችን የሚቃወሙ ሴቶች በወሲባዊ መንገድ መታየት፣ ክብር መነፈግ፣ መገለልና እና ስድብም ገጥሟቸዋል። ፌሚኒዝም ተደጋግሞ የተነሳ ሀሳብ ሲሆን ባህላዊ እሴቶችን የሚቃረን ሆኖ ተወክሏል፣ ፌሚኒስቶችም ስማቸው ጠፍቷል።

ይህ የጥናት ክፍል ጎጂ ይዘቶችን የሚያባብሱ አስተሳሰቦችን ከማሰሱ በፊት በመጀመሪያ የመረጃ ውጤቶችን በጥልቀት በማጥናት የጥላቻ አይነቶች እና አውዶችን ይዳስሳል።

### 4.2.1 ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረገ የጥላቻ ንግግር አይነት

ይህ ጥናታዊ ምርመራ ልዩ የሆኑ ሴቶችን እና ልጃገረዶች ላይ ያነጣጠሩ የጥላቻ ንግግር ዓይነቶችን በጥልቀት አጥንቷል:: ይህ የመረጃ ማህደር ከስድብ እና ማስፈራራት እስከ የበታችነት ስሜትን መፍጠር ወይም ሴትነትን

ከመጥፎ ባህሪያት ጋር ማያያዝን ጨምሮ የተለያዩ ጥቃቶችን አጋልጧል (ከዚህ በታች ያለውን ምስል 3 እና 4 ይመልከቱ)። እነዚህ ምድቦች የኢንተርኔት ላይ የስርዓተ-ፆታ የጥላቻ ንግግርን ዘርፈ ብዙ መልክ አጉልተው ያሳያሉ።

| TYPE OF HATE SPEECH | | | | |
|---|---|---|---|---|
| CATEGORY | INSULT | THREAT | PRESUMED ASSOCIATION | ALLEGED INFERIORITY |
| DEFINITION | Offensive remarks or denigrating expressions. | Intimidation, incitement to hatred, violence, or a violation of rights. | with harmful personality traits, such as laziness or greed. | of social position, cognitive or physical ability. |


*ምስል 3፡ የእያንዳንዱን የጥላቻ ንግግር አይነት ምንነት የሚያብራራ ከሃሳባዊ ማዕቀፉና ትርጓሜ ፕሮቶኮሉ ላይ የተወሰደ ምስል*

ከተተነተነው ይዘት 44.9% የሚሆነው የተለያዩ ማንነትን የሚነኩ ንግግሮችን ያካተቱ **ስድቦች** ናቸው። ይህ ምድብ የሴቶችን ክብር እና ዋጋ ዝቅ ለማድረግ የታቀዱ የቃላት ጥቃቶችን ያጠቃልላል። ብዙውን ጊዜም ድምፃቸውን ለመቀማት ወይም ለማዋረድ በሚፈልጉ ክፉ እና አስጸያፊ መንገዶች ይቀርባሉ።

ሁለተኛ ደረጃ በመያዝ 25.8% የሚይዘው የይዘት አይነት **አሳናሽ** ንግግር ነው። ይህ ምድብ ሴቶችን እና ልጃገረዶችን የበታችነት ስሜት እንዲሰማቸው ለማድረግ በመሞከር ማህበራዊ ሚናቸው፣ የግንዛቤ ወይም የአካላዊ ችሎታቸው ላይ ያነጣጠረ ንግግርን ያካትታል። እነዚህ አስተያየቶች ጎጂ የሆኑ አስተሳሰቦችን ከማስቀጠል ባለፈ ያለውን የፆታ እኩልነት ችግር አጠናክረው፣ ሴቶች በሁሉም የሕይወት ዘርፍ ውስጥ ያነሱ እንደሆኑ የሚያመላክቱ ሃሳቦችን ያስቀጥላሉ።

19.8% የሆኑት የጥላቻ ንግግሮች ደግሞ **ባልተረጋገጠ መረጃ ሴቶችን ከስግብግብነት ወይም ስንፍና ጋር ያያይዛሉ**። እነዚህ አስተያየቶች ሴቶችን ከማይፈለጉ ባህሪያት ጋር በማያያዝ እና ክብራቸውን ለማጣጣል በተዛባ አመለካከት ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ይህም በግልፅም ሆነ በተዘዋዋሪ የሴቶችን እና ልጃገረዶችን ስም እና ተአማኒነት (በጋራም ሆነ በግል) ሊሸረሽር ይችላል።

ከሌሎቹ አነስተኛ ቢሆንም፣ 9.6% የሆኑት የጥላቻ ንግግሮች አይነት **ዛቻዎች** ናቸው። ይህ ምድብ ማስፈራራትን፣ ጥቃት ማነሳሳት እና የግለሰቦችን መብት ለመጣስ የሚደረግ ዛቻን ያጠቃልላል። ብዙ የተለመደ ባይሆንም፣ የዚህ አይነት የዛቻ ይዘት መኖሩ ከኢንተርኔት ወደ ገሃዱ ዓለም የመሸጋገር አቅም ስላለው ከፍተኛ ስጋትን ይፈጥራል። በብዙ ምክንያቶች፣ ሲ.አይ.አር አስተያየቶች ብቻ መተንተናቸው (በቪዲዮው ይዘት ውስጥ ያለው ጥላቻ ሳያጠቃልል), ይዘት ቁጥጥር መኖሩ እና አደገኛ የሚባሉ አስተያየቶች መወገዳቸው በቲክቶክ ላይ ያለውን ከፍተኛ የዛቻ መጠን በበቂ ሁኔታ እንዳይወከል ምክንያት ነው ብሎ ያመናል።




*ምስል 4: በሲ.አይ.አር የመረጃ ስብስብ ውስጥ የተካተቱ ሴቶችና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግር አይነቶች*

### 4.2.2 የጥላቻ አውድ

ሲ.አይ.አር በሴቶች እና ልጃገረዶች ላይ ያነጣጠሩ የተለያዩ የጥላቻ ንግግር **አውዶችን** መርምሯል። እነዚህ የጥናት ውጤቶች ግልጽ በሆነ ሁኔታ ጥቃት እንዴት እንደሆነ እና ስለሚያስከትላቸው ጉዳዮች በበለጠ ግንዛቤን በመስጠት ሴቶች በኢንተርኔት የሚያጋጥሟቸውን የተለያዩ እና የተደራረቡ የጥላቻ ንግግር ዓይነቶች ያሳያሉ። ተመራማሪዎች የማህበራዊ ሚዲያ መድረክ ይዘቶችን **ፀብ ጫሪ** እና **አፀያፊ ቋንቋ፣ ፌዝ** ወይም **በስርአተ-ፆታ ዙርያ የተሳሳቱ አመለካከቶችን የያዙ ንግግሮች** በማለት ከፋፍለዋል። (ከዚህ በታች ያለውን ምስል 5 እና 6 ይመልከቱ)

| | SENTIMENT OF HATE SPEECH | | | |
|---|---|---|---|---|
| CATEGORY | OFFENSIVE | STEREOTYPICAL | MOCKERY | AGGRESSIVE |
| DEFINITION | Offensive remarks, demeaning or denigrating language. Associating the target with harmful or false personal traits, or suggesting the target's inferiority. | Text includes implicit or explicit references to stereotypical beliefs or prejudices about an individual/group with protected characteristics. | Mockery, satire or sarcastic messaging which targets a protected characteristic of the recipient and could be harmful. | Strong language that: physically intimidates, threatens or incites physical violence; or, which requests, suggests or promotes a violation of rights. |


*ምስል 5: የእያንዳንዱን የጥላቻ ንግግር አውድ ምንነት የሚያብራራ ከሃሳባዊ ማዕቀፉና ትርጓሜ ፕሮቶኮሉ ላይ የተወሰደ ምስል*

በመረጃ ማህደሩ ውስጥ በጣም ከፍተኛ ቦታ የያዙት አውዶች **አፀያፊ እና በስርአተ-ፆታ ዙርያ የተሳሳቱ አመለካከቶች** ሲሆኑ በቅደም ተከተል 35.7% እና 32.6% ይይዛሉ። አፀያፊ ንግግር ሰፋ ያለ የጥላቻ ንግግር

አይነቶችን ያጠቃልላል። ከቀጥተኛ ስድብ እና ክብርን ዝቅ የሚያደርጉ አስተያየቶች እስከ የተጠቂው ለራስ የሚሰጠውን ዋጋ የሚያሳንሱ እና የበታችነት ስሜትን የሚያጠናክሩ ንግግሮችን ያካትታል። አንድ ይዘት በስርአተ-ፆታ ዙርያ የተሳሳቱ አመለካከት ይዟል ብሎ ለመመደብ ጽሑፉ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጭፍን ጥላቻዎችን መያዝ አለበት። ይህም በሴቶች እና ልጃገረዶች ላይ የማህበራዊ መድሎ ጫና ይፈጥራል።

በሦስተኛ ደረጃ ላይ የተቀመጠው አውድ፣ **ፌዝ** ሲሆን ከጥላቻ ንግግሮቹ ውስጥ 20% ይይዛል። ይህም ብዙውን ጊዜ ቀልድ እና አሽሙር መልክ በመያዝ ሴቶች ላይ ለመሳለቅና ዝቅ ለማድረግ ሲውል ይታያል።

11.7% ብቻ የያዘው ፣ **ፁብ ጫሪ ንግግር** ከሁሉም በበለጠ ቀጥተኛ የሆነውን ጎጂ አውድ ይወክላል። እነዚህ አስተያየቶች ማስፈራሪያ፣ ዛቻ እና የጥቃት መገፋፋትንን የሚያጠቃልሉ ሲሆን ሴቶችን በዲጂታሉ አለም ዝም ለማሰኘት እና ለጥቃት ለማጋለጥ ኢላማ ያደረጉ ናቸው።




*ምስል 6: በሲ.አይ.አር የመረጃ ስብስብ ውስጥ የተካተቱ ሴቶችና ልጃገረዶችን አላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግር አውዶች*

### 4.2.3 የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ልዩ አዝማሚያ (የጥላቻ አይነት እና አውድ)

ዩትዩብ እና ቲክቶክ


የሲ.አይ.አር ጥናት ትንተና በቲክቶክ እና በዩትዩብ ላይ ያሉ ሴቶች እና ልጃገረዶችን ያነጣጠሩ የጥላቻ ንግግሮች መካከል ያለውን ያልጎላ ልዩነት አሳይቷል። አንዳንድ የጥላቻ አይነቶች እና አውዶች በተመሳሳይ መልኩ ሲሰራጩ፣ ሌሎች ደግሞ በተለያዩ ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ልዩነት አሳይተዋል። የአውደ ጥናት ተሳታፊዎች እነዚህ ልዩነቶች የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮችን የተለያዩ ልማዶችና እና የተጠቃሚ ባህሪያትን እንደሚያንጸባርቁ ተረድተዋል።

ቲክቶክ (39.5%) ከዩትዩብ (47.4%) ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ የ**ስድብ** ይዘት ያስተናግዳል። እንዲሁም ቲክቶክ(36.1%) ከዩትዩብ(24.2%) ይልቅ በስርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረቱ ጭፍን እና የተለመዱ ጥላቻን የሚያራምዱና **የተሳሳቱ አመለካከቶች ላይ የተመሰረቱ የጥላቻ ንግግሮችን** በከፍተኛ ደረጃ ያስተናግዳል። አንድ የአውደ ጥናት ተሳታፊ የቲክቶክ አሳታፊ እና አስተያየት ተኮር መሆን በቀላሉ ክብርን የሚነኩ ንግግሮችን

መስፋፋት ሲያባብስ በትንሽ ጊዜ ብዙ ይዘት ማሳየት መቻሉ ደግሞ ችኩል አስተያየቶች እና በስርአተ-ፆታ ዙርያ የተሳሳቱ አመለካከቶችን የያዙ መልዕክቶችን ያበረታታል።

ዩትዩብ (31.6%) ከቲኪቶክ (23.1%) ጋር ሲወዳደር ባልተረጋገጠ ሁኔታ **ሌሎችን ዝቅ ማድረግን ያማከለ የጥላቻ ንግግር** ነበረው። በተመሳሳይ ዩትዩብ(16.4%) ከቲክቶክ(9.8%) በላይ **ዛቻን፣ ማስፈራራትን ወይም ጥቃትን የሚቀሰቅሱ የጥላቻ ንግግሮችን** ያስተናግዳል። የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች ዩትዩብ ረዘም ላይ ያለ ቪድዮ ማሳየት መቻሉ እና በአስተያየት የተሞላ ይዘት መያዙ ተጠቃሚዎች አድሎአዊ ንግግር ውስጥ እንዲሳተፉ የበለጠ የሚገፋፋ እንደሚችል ጠቁመዋል። ይህም ለፀብ የሚገፋፋ መድረክን በመፍጠር የጥላቻ ንግግርን ሊያባብስ ይችላል።

ትኩረት በሳበ ሁኔታ **የዛቻ ፣ ባልተረጋገጠ ሁኔታ ነገሮችን ማዛመድ፣ ፌዝ እና አፀያፊ ንግግሮች** በሁለቱም የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ በአንፃራዊነት ተመሳሳይነት ነበራቸው። ይህም፣ በሁለቱም የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ ተመሳሳይ የሆኑ በስርአተ-ፆታ ዙርያ የተሳሳቱ አመለካከቶች፣ ፌዝ፣ የማሳነስ ንግግሮች እና ማስፈራራት አዝማሚያ እንዳለ ይጠቁማል። እነዚህ ተመሳሳይነት ያላቸው ሁኔታዎች የሚያሳዩት በተለያዩ የማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች መካከል በተደጋጋሚ የጥላቻ ይዘት ያላቸው ንግግሮች ልውውጥ መኖሩን ነው። በተጨማሪም እነዚህ የጥናት ውጤቶች የሚያመላክቱት እያንዳንዱ የማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፅ የራሱ የሆነ መፍትሄ እንደሚያስፈልገው ነው። ይህም ለሴቶች እና ልጃገረዶች ደህንነቱ የተጠበቀ የኢንተርኔት መድረክን ይፈጥራል።





*ምስል 7፡ ሴቶችን ኢላማ የሚያደርጉ የጥላቻ ንግግሮች አይነትና አውድ የሚያሳይ ምስል*

ፌስቡክ፣ ቴሌግራም፣ ቲክቶክ፣ ዩቱይብ እና ኤክስ


ሲ.አይ.አር በዚህ ጥናት ላይም ቀደም ሲል ባደረገው ጥናት ላይ የተጠቀመውን ዘዴን ስለተጠቀመ፣ የጥናት ውጤቶቹን በአምስት ዋና ዋና መደቦች ማለትም ፌስቡክ፣ ቴሌግራም፣ ቲክቶክ፣ ዩትዩብ እና ኤክስ ከፋፍሎ አወዳድሯል። ይህም የተወሰኑ ሁኔታዎች ተመሳሳይነት ያላቸው ቢሆንም፣ እያንዳንዱ የማህበራዊ ሚዲያ መድረክ ላይ በሴቶች እና ልጃገረዶች ላይ የሚፈጸመው ጥቃቶች እንዴት እንደሚለያዩ አሳይቷል።

የማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፅ ልዩነቶች

- በሁሉም የተጠኑት የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ፣ **አፀያፊ ንግግር** ቀዳሚ የሆነው የጥላቻ ንግግር አውድ ነበር። በዚህም መሰረት ፌስቡክ (55.7%) ቀዳሚነቱን ሲይዝ ቲክቶክ (34.7%) ደግሞ የመጨረሻውን ቦታ ይዟል።
- ቴሌግራም(15.6%) ቲክቶክን (9.2%) በእጥፍ በመብለጥ **ዛቻን** ያዘለ የጥላቻ ንግግርን በማስተናገድ ከፍተኛውን ውጤት አስመዝግቧል። ይህ ልዩነትም የተፈጠረው በቴሌግራም ላይ የይዘት ቁጥጥር የሚያካሂዱት የቻናሉ ባለቤቶች መሆናቸውና እና በመድረኩ ዝግ ተፈጥሮ ሊሆን ይችላል።
- ቴሌግራም (29.1%) ከፍተኛውን **የፌዝ** ይዘት ሲይስተናግድ ኤክስ (9.3%) ደግሞ የመጨረሻውን ደረጃ ይዟል።
- ከቴሌግራም (5.9%) በሦስት እጥፍ የሚበልጠው ዩትዩብ (16.4%) **የፀብ ጫሪ** ንግግርን በማስተናገድ ትልቁን ቦታ ይዟል ።
- በተጨማሪም ዩትዩብ (31.6%) **ከአሳናሽ** የጥላቻ ንግግር ጋር ስሙ ጎልቶ ታይቷል።
- ኤክስ (48%) **ስድብን** መሰረት ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮችን በመያዝ ቲክቶክን (47.4%) በመጠኑ ሲበልጥ ፌስቡክ (25%) የመጨረሻውን ደረጃ ይይዛል።
- ፌስቡክ (31.7%) ሴቶችን **ከመጥፎ ባህሪያት ጋር በሚያያይዝ** የጥላቻ ንግግር ከፍተኛውን ቦታ ይዟል።
- ቲክቶክ ከፍተኛውን **በስርአተ-ፆታ ዙርያ የተሳሳቱ አመለካከቶችን** የሚሰብኩ የጥላቻ ንግግሮች ቦታ (36%) ሲያስተናግድ ፌስቡክ (12.5%) በአንፃራዊነት ዝቅተኛ ድርሻ ነበረው።




*ምስል 8: በሁለቱ የሲ.አይ.አር ጥናቶች ውስጥ በተካተቱት ማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ ሴቶችና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግር አይነቶች የሚያሳይ ምስል*




*ምስል 9: በሁለቱ የሲ.አይ.አር ጥናቶች ውስጥ በተካተቱት ማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ ሴቶችና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግር አውዶችን የሚያሳይ ምስል*

### 4.2.4 ማብራሪያዎች

በትርጓሜ ሂደት ውስጥ፣ በስርዓተ-ፆታ የጥላቻ ንግግር ውስጥ ያሉ ቁልፍ ሃሳቦች ተለይተው ተመዝግበዋል። እነዚህ ሃሳቦች በአውደ ጥናቱ ተገምግመው ስለትርጉማቸው እና ስለተፅዕኖቻቸው ጥልቅ ግንዛቤን ለመስጠት አስችለዋል (በአውደ ጥናቱ ላይ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ ክፍል 3.6 ይመልከቱ)። ይህ የጥናቱ ክፍል በኢንተርኔት ላይ ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ኢላማ ለማድረግ ጥቅም ላይ የሚውሉትን ዋና ዋና ጭብጦችን ያሳያል፣ ይህም ጎጂ ትርክቶች እንዴት እነደሚፀነሱና እና እንደሚቀጥሉ ያሳያል።

በማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ፣ ሲ.አይ.አር የፆታ ጥቃትን ጨምሮ ሌሎች ተደጋጋሚ እና የህብረተሰቡን አኗኗር ዘይቤ የሚያንፀባርቁ ሃሳቦችን ተመልክቷል። የሴቶች ሚና እና መልካቸው ተደጋግመው በወሲባዊ እና ንቀታዊ ቋንቋ ይነሳሉ ። ይህም ስኬታማ የሆኑ በተለይም ፖለቲካ እና ስፖርት ውስጥ ያሉ ሴቶችን በመናቅ ፣ በማግለል እና ወሲባዊ አስተያየቶችን በመስጠት ጎልቶ ይታይ ነበር። በተመሳሳይ፣ የ'ነፃነት' እሳቤዎች ከባህላዊ የሥርዓተ-ፆታ ሚናዎች ጋር የሚጋጩ ተደርገው ይታያሉ ። የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች ባህላዊ እና ሀይማኖታዊ እሴቶች ብዙውን ጊዜ ጥቃትን አቅልለው እንደሚያዩ እና ሴቶችን 'በሴቶች ሚና' እና በስርአተ-ፆታ ዙርያ በተሳሳቱ አመለካከቶች እንደሚጨቁኑ ያስባሉ ።

በስልጣን ላይ ያሉ ሴቶች ላይ ወሲባዊ አስtያየቶች መስጠትና እና ማሸማቀቅ


ሴቶች ፖለቲካ ወይም ሌሎች እንደ አመራር ያሉና እንደ የወንድ ስራ የሚታሰቡ ስራዎችን ለመስራት እንደ ደካማ ወይም ብቁ እንዳልሆኑ ተደርገው በተደጋጋሚ ፆታዊ ጥቃት ይደርስባቸዋል። ይህ በስልጣን ላይ ያሉ ሴቶችን በሚተቹ አስተያየቶች ላይ በግልጽ ታይቷል። ለምሳሌ አዳነች አቤቤ (ታዋቂዋ የፖለቲካ ሰው እና የአዲስ አበባ ከንቲባ) ሚናዋን የተቀዳጀችው ከብቃቷ ይልቅ በግላዊ ግንኙነቶች ነው የሚሉ ተደጋጋሚ ሀሳቦችን ሲ.አይ.አር ለይቷል፣ ይህም የፆታ መገለልና እና የወንድ የበላይነትን የሚሰብኩ አስተያየቶችን መጣመር አሳይቷል።

> “
>
> አዳነች በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዴት ብዙ
> ስልጣን አገኘች? የአብይ ቀምጥ ነች?
>
> ”
>
> ከጥላቻ ንግግር ስብስብ የተወሰደ

ይህም ቀደም ባሉት ጥናቶቻችን ላይ ከታየው የሴቶችን ስኬት ከማሳነስ አዝማሚያዎች ጋር ይዛመዳል። ይህ ሀሳብ በአውደ ጥናቶቹ ላይ ሲነሳ፣ አዳነች እንደ “አነጋጋሪ ግለሰብ” በመቆጠር ጠቅላይ አቃቤ ህግ ሆና መስራት ከጀመረችበት ጊዜ ጀምሮ ስትተች ቆይታለች። በአዲስ አበባ ከንቲባነቷ ከጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ ጎን በዝግጅቶች እና የመክፈቻ ስነ ስርዓቶች ላይ ብዙ ጊዜ መታየቷ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ቅርበት እንዳላት ለማሳያ እንደ መረጃ ሲነገር ይታያል።

የአውደ ጥናት ተሳታፊዎች እንደገለፁት የማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎች ብዙውን ጊዜ ከፍተኛ ስልጣን ላይ ያሉ ሴቶችን የሚያዋርዱት ከፍተና ብልሀት ወይም እውነተኛ ማስረጃ የማያስፈልገው መንገድ ስለሆነ ነው። ሌሎች በአመራርነት ሚና ላይ ያሉ እንደኢትዮ ቴሌኮም ዋና ስራ አስፈፃሚ ፍሬህይወት ታምሩ ያሉ ሴቶችም የፆታዊ

ጥቃት እና ትችት እንደሚደርስባቸው ተሳታፊዎቹ ተናግረዋል። በተመሳሳይ፣ የሲ.አይ.አር መረጃ የዩትዩብ «ቤቲ ሾው»ፕሮግራም  አቅራቢ ቤቲም ኢላማ እንደተደረገች ይገልፃል። በአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎቹ ይህ ዓይነቱ ጥቃት በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ ስልጣን ላይ ያለች ፣ በኢንተርኔት ላይ ታዋቂ የሆነች እና ለውጥን የምትሰብክ ሴት ከመሆን ጋር ተያይዞ የሚመጣ እንደሆነ ያምናሉ።




*ምስል 10: የቤቲ ሾው ዩትዩብ ገፅ፣ በሲ.አይ.አር የተወሰደ*

ነፃ የሆኑና ልጆቻውን ለብቻ የሚያሳድጉ ሴቶች

[የሲ.አይ.አር ጥናት] እንደሚያሳየው የፖለቲካ ሰዎች፣ ጋዜጠኞች፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች መሪዎች፣የማህበራዊ ሚዲያ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች እና የቴሌቪዥን ፕሮግራም አቅራቢዎች የመሳሰሉ፣ በመሪነት ሚና ላይ ያሉና በማህበራዊ ሕይወት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉ ሴቶች ተደጋጋሚ የኢንተርኔት ላይ ጥቃት ይደርስባቸዋል። የአውደ ጥናት ተሳታፊዎች የእነዚህን ሴቶች ነጻነት ለዚህ ችግር እንደመንስኤ ተጠቅሰዋል። ይህም ባህላዊ የስርዓተ ፆታ ስርዓትን የሚቃወሙ ሴቶች ጥላቻ እንደሚደርስባቸው ከሚያሳየው የቀድሞ የሲ.አይ.አር ጥናት ጋር ይደጋገፋል። የአውደ ጥናት ተሳታፊዎች ያላገቡ ሴቶች በተደጋጋሚ በተመሳሳይ ምክንያቶች የጥቃት ኢላማ እንደሚሆኑ ጠቅሰዋል።

በሴቶች ጥቃት ዙሪያ በተደረገው አውደ ጥናት ላይ በተሰበሰበው መረጃ ውስጥ በተደጋጋሚ ስለታየው “ሴት ያሳደገው” በሚለው ሀረግ ዙሪያ ክርክር ተነስቷል። ይህ ሀረግ ነፃነትን የሚያሳይ ቢሆንም እንደ ንቀት ማሳያም ያገለግላል። እንደ አውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች ይህ ሀረግ ሴቶችን ለማሸማቀቅ እና ለመናቅ የተለመደና ከኢንተርኔት ዓለም ውጪ እውነተኛው ዓለም ላይም ጥቅም ላይ እንደሚውል ተናግረዋል።

> ሊክዱሽ ይገባል፣ በዛ ላይ ልጅሽን ብቻሽን ነው የምታሳድጊው🤣🤣🤣
>
> ከጥላቻ ንግግር ስብስብ የተወሰደ

ይህ ስድብ በኢትዮጲያ ውስጥ የሞራል ወይም የማህበራዊ የበታችነት ስሜትን በመፍጠር ግለሰቦችን ለማንቋሸሽ አገልግሎት ላይ ይውላል። ይህም ልጆቻቸውን ያለ አባት በሚያሳድጉ እናቶች ዙሪያ ላለው መገለል እና ኢንተርኔት ላይ ላሉ ጥላቻዎች መጠቀሚያነት መዋሉን ያሳያል። በህብረተሰቡ ውስጥ የወንድ አርዓያነትንና አስፈላጊነትም ያሳያል። እንደ ተሳታፊዎች ዘገባ ወጣት ሆነው ልጆቻቸውን ለብቻ የሚያሳድጉ እናቶች ጥቃቱ እንደሚበረታባቸው ገልፀው የቤተሰብ ግዴታቸውን እንዳልተወጡና ነፃነትና ፌሚኒዚም የመሳሰሉ ከሀይማኖትና ማህበረሰባዊ እሴቶች ጋር የተቃረኑ ሀሳቦችን እያራመዱ እንደሆነ ይታሰባል።

ትኩረትን በሚስብ መልኩ አንድ ልጅ በእናቱ ብቻ ካደገ ልጁ በአግባቡ እንዳላደገ ሲታሰብ ከአባቱ ጋር ብቻ ካደገ ግን አሳዳጊው አባት ለጥረቱ "የአመቱ ምርጥ አባት" ተብሎ ይወደሳል። ይህ በቤተሰብ ውስጥ በወንዶች ሚና ዙሪያ ትኩረት ሳቢ ክርክር አስነስቷል። አንድ ተሳታፊ እናቶች ልጆቻቸውን ለብቻ ማሳደጋቸው "የወንዱ ውድቀት" እንጂ የሴቶቹ ችግር እንዳልሆነ በመግለጽ ጥቃቱን ተችተዋል።

**ፌሚኒዝም እንደ ኢንተርኔት ላይ ጥቃት ኢላማ**

ሲ.አይ.አር ከዚህ በፊት ከሰራው ጥናት ጋር በተመሳሳይ መልኩ ፌሚኒዝም ሴቶችንና የሴቶችን መብት ለማስከበር የሚታገሉ አባላትን ለማሸማቀቅ እንደ መሳሪያ የሚያገለግል ርዕስ ሆኖ ተገኝቷል።

ለዚህም ምክንያቱ ምን እንደሆነ የተጠየቁት ተሳታፊዎቹ የወንድን የበላይነት የሚያጎሉ የአኗኗር ዘይቤዎች ከሀይማኖትና ማህበረሰባዊ እሴቶች ጋር በመሆን የኢትዮጲያ ማህበራዊ ኑሮ ምህዳርን ተቆጣጥረዋል ብለዋል። የተሰበሰበውም መረጃ ይህን የሚያጠናክር ነበር። ለምሳሌ አስተያየቶች ብዙውን ጊዜ ፌሚኒዝምን እንደ አጥፊ ሀይል በመቁጠር በኢትዮጲያ ማህበረሰብ ውስጥ ያለውን ባህላዊ እሴቶች የሚያዳክም ነው ይላሉ።

> ፌሚኒዝም ጥብቅ የሆኑ ባህላዊና ሃይማኖታዊ አስተሳሰቦችን ስለሚሞግት እንደፅንፈኛ ሀሳብ ነው የሚታየው
>
> የአውደ ጥናት ተሳታፊ፣ እ.ኤ.አ 2025

በፌሚዝም ዙሪያ ያሉ ሀሳቦች የተቃረኑ ናቸው። ለምሳሌ አንድ አስተያየት ሰጪ የሚከተለውን በማለት ሌላ ማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚ ላይ ተሳልቋል፡

> ፌሚኒዝም ማለት ይሄ አይደለም የኔ ቆንጆ። ሴቶች የመስራት ወይም ቤት ተቀምጦ ልጅ የማሳደግ ምርጫ አላቸው። የፌሚኒዝም ሀሳብሽን ሰው ላይ እየጫንሽ ነው

ከጥላቻ ንግግር ስብስብ የተወሰደ

ፌሚኒስቶች በኢንተርኔት መድረክ ላይ የጥቃት ኢላማ ተደርገዋል፣ ተንቀዋል እና ተገልለዋል። የሚደረጉ ውይይቶች በተደጋጋሚ አደገኛ እና የተሳሳቱ እንደሆኑ አድርገው ይስሏቸዋል። ለምሳሌ ፌሚኒዝምን ለገንዘብ ጥቅም ማግኚያ መሳሪያ እንደሆነ አድርገው ይገልፁታል። እንደዚህ ያሉ አስተያየቶች ፌሚኒስቶች የሴቶችን መብት ለማስከበር ከእውነተኛ ተሟጋቻችነት ይልቅ ራሳቸውን ለማበልፀግ እየሰሩ እንደሆነ ይሰብካሉ። ይህ ትርክት የሴቶችን እንቅስቃሴ ተዓማኒነት የሚጎዳና ሴቶች ከግል ጥቅማቸው ውጪ ከራስ ወዳድነት ነፃ በሆነ መንገድ መንቀሳቀስ አይችሉም የሚለውን የተሳሳተ አመለካከት የሚያስቀጥል ነው።

> የኢትዮጲያ ፌሚኒዝም ገንዘብ ለማካበት ነው። እባካቹ ምንም የማያውቁ ሴቶችን ለግል ኪሳቹ መሙያ አትጠቀሟቸው።

ከጥላቻ ንግግር ስብስብ የተወሰደ

ለዚህ ሪፖርት በተደረጉ እውደ ጥናቶች ወቅት ፣ፌሚኒስቶች ብዙውን ጊዜ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጊቶች እና የውጪ ሀገራት ክፍያ እየተከፈላቸው እንደሚሰሩና "ከሀዲ "እንደሆኑ የሚገልፁ አስተያየቶች እንደሚደርሳቸው ተሳታፊዎች ገልፀዋል። ይህ ከመጀመሪያው ጥናት ግኝት ጋር ተመሳሳይና ፌሚኒዝም የምዕራባውያን ፅንሰ ሀሳብ እንደሆነና የኢትዮጲያ አኗኗር ዘይቤን የሚሸረሽር ተደርጎ እንደሚታይ ያሳያል። በመሆኑም ጥቃት አድራሾች የሴቶች መብት ደጋፊ የሆኑ ወይም ፌሚኒስት ሴቶችን በምዕራባውያን ጫና ውስጥ እንደወደቁ አድርገው ሊሰድቧቸው ወይም ሊቀልዱባቸው ይችላሉ።

ሌላ አሳሳቢ የነበረው ግኝት ፌሚኒዝምን በኢትዮጲያ ውስጥ ህገ-ወጥ ከሆነው ግብረ ሰዶማዊነት ሀሳቦች ጋር መገናኘቱ ነው። ይህ አስተሳሰብ ፌሚኒዝምን በኢትዮጲያ ማህበረሰብ ውስጥ ተቀባይነት ከሌላቸው ሀሳቦች ጋር በማዛመድ የእንቅስቃሴውን ህጋዊነት ለማሳጣትና ለሴቶች መብት የሚታገሉ ሰዎች ላይ ጥላቻን ለመፍጠር ያለመ ነው። እንደዚህ አይነት ወንጀላዎች እንደ ስድብ ብቻ ሳይሆን ግብረሰዶማዊነት ህገ-ወጥ በመሆኑ ምክንያት እንደ ማስፈራሪያና ዝም ማሰባያ ሊያገለግሉ ይችላሉ። ይህም በኢንተርኔት ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች ምን ያህል በእውነተኛው ዓለም የግልና ሙያዊ ህይወት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ በማሳደር መዘዞችን ሊያስከትል እንደሚችል አጉልቶ ያሳያል።

ሲ.አይ.አር "የገንዘብ ጥቅም" እና "ፌሚኒዝምና ግብረሰዶማዊነት" ግንኙነት ዙሪያ ለአውደ ጥናት ተሳታፊዎች ሀሳብ ሲያቀርብ ፣ ብዙ ተሳታፊዎች እነዚህ ትርክቶች የሚጠበቁና የተለመዱ መሆናቸውንና የፌሚኒዝምን እንቅስቃሴ ህገ-ወጥ ለማድረግ ያለሙ እንደሆነ ተናግረዋል።

የጥላቻ ንግግር በሴቶች ስፖርት ውስጥ

ሌላ ተለይቶ ሊታይ የሚችል ሀሳብ በሴቶች ስፖርቶች ላይ የሚደርሰው የጥላቻ ንግግር ነው። በጉዳዩ ላይ ያሉ ሀሳቦች የሴቶች ስፖርት ዝቅተኛ ቦታ እንዳለውና ህልውናው ወንዶች በሚያደርጉት ድጋፍ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ የሚያትቱ ናቸው። ይህ አነጋገር የሴቶችን አስተዋፅኦ ከማሳነስ ባለፈ ኋላቀር የሆኑ የስርዓተ ፆታ አመለካከቶችን የሚያጠናክሩ ናቸው። ይህም የሴቶችን አትሌቲክስ ስኬት ዝቅ የሚያደርግ ነው።

የአውደ ጥናት ተሳታፊዎች በእነዚህ ግኝቶች እንዳልተገረሙና የሴቶች ስፖርት በተለምዶ ዝቅ ተደርጎ እንደሚታይ ገልፅዋል። ጥናቱ የተካሄደው ኦሎምፒክ እየተካሄደበት በነበረበት ወቅት ስለነበር የሴቶች ስፖርት ማህበራዊ ሚዲያ ላይ መነጋገሪያ ርዕስ ሊሆን እንደሚችል ተሳታፊዎች ገልጽዋል። ይህም ኢትዮጲያን ወክለው የሚወዳደሩ ሴት አትሌቶች ስለሚደርስባቸው ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መነጋገሪያ መንስኤ ሆኖ ነበር።

በተጨማሪም በመረጃ ማሰባሰቡ ወቅት ሁለት ሴቶች በአዲስ አበባ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ውስጥ በዋና አመራርነት ቦታዎች ላይ ተመርጠው እንደነበር ተሳታፊዎች አንስተዋል። ማስተዋል ወንድወሰን እና ሀረገወይን አሰፋ እንደየቅደም ተከተላቸው ምክትል ፕሬዝዳንትና የፋይናንስ ኦፊሰር ሆነው ተመርጠው ነበር። እነዚህም ግለሰቦች ስለ እግር ኳስ ለማውራትም ሆነ በጉዳዩ ላይ ለመስራት ብቁ እንዳልሆኑ ተደርጎ መሳለቂያ ሆነው እንደነበር ተገልጿል (ምንጮች ግላዊነትን ለመጠበቅ ሲባል ማንነታቸው አልተገለፀም)።

**የጥላቻ ንግግር መለመድና ችላ መባል**

ሁሉም የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች ብዙ "ጭካኔ" ፣ "አመፅ" እና "አስጊ" የሆኑ የጥላቻ ንግሮች በሚታዩበት የቲክቶክ መድረክ ማስፈራሪያን የያዙ ወይም ፅብጫሪ የሆኑ የጥላቻ ንግግሮች ከሌሎች የጥላቻ ንግግር አይነቶች ባነሱ መልኩ መታየታቸው እንዳስገረማቸው ገልፀዋል። ይህ ግኝት ከሲ.አይ.አር ቀደምት ቁጥራዊ ጥናት ጋር የተመጣጠነ ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት ምናልባት በጣም ጎጂ የሆኑ ይዘቶች በማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ሊወገዱ ስለሚችሉ ይሆናል።

> ቲክቶክ ለሴቶች በጣም መርዛማና አስፈሪ የሆነ የማህበራዊ ሚዲያ መድረክ ነው። ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ታዋቂነትን ለማግኘት ሲሉ የማይሉት መጥፎ ነገር የለም

የአውደ ጥናት ተሳታፊ፣ እ.ኤ.አ 2025

የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች ቲክቶክ ያለው ግልጽ ዛቻ በመረጃው ላይ ከተገኘው በላይ እንደሆነ እንዲያውም ቲክቶክ "በጥቃት ላይ የተመሰረተ ማህበራዊ ሚዲያ" እንደሆነ ተሳታፊዎች ገልፀዋል። ይህ ልዩነት የመጣው ምን አልባት ከመረጃ አሰባሰብ ሂደቱ በፊት ፅንፍ የያዙ አስተያየቶች ተወግደው ስለሆነ ይሆናል። በሌላ በኩል የሲ.አይ.አር የቀድሞ ጥናቶች እንዳመለከቱት ሌሎች አይነቶች ፆታን መሰረት ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች ስለተለመዱ ሳይስተዋሉ ቀርተው ይሆናል። ቀደም ሲል የተሰሩ የሲ.አይ.አር ጥናቶች እንደሚያሳዩት የሴቶችን የበታችነት ስሜት የሚሰብኩ መልእክቶች ሳይስተዋሉ ሲቀሩ ስድብ፣ፌዝ እና ስነ-ፆታን መሰረት ያደረጉ የተሳሳቱ አመለካከቶች በጣም የተለመዱ ከመሆናቸው የተነሳ እንደ ጥላቻ ንግግር ላይታዩ ይችላሉ። ለምሳሌ የሲ.አይ.አር የቀድሞ ጥናት ፆታን መሰረት ያደረገ ጥላቻ መስፋፋቱ ማህበረሰቡ ትኩረት እንዳይሰጠው እንዳደረገው ደምድሟል።

በተጨማሪም ስርዓተ ፆታ ላይ ያተኮሩ ጥቃቶች በጣም እየተስፋፉ የመጣና ችላ እየተባለ መጥቶ የማይታዩበት ደረጃ ላይ መድረሱን የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች በአፅንኦት ገልፀዋል። በዚህም ምክንያት የጥላቻ ንግግሮች ማለትም ስላቅና በስነፆታ ዙሪያ የተሳሳተ መልዕክትን የያዙ የጥላቻ ንግግሮች ይታለፋሉ፣ ሪፖርት አይደረጉም አልፎም ጎጂ እንዳልሆኑ ይታሰባል።

ፖሊሲ አውጪዎች እና አንቂዎች እነዚህን ስውር የሆኑ ግን በእኩል ደረጃ ጎጂ የሆኑ ንግግሮችን ችላ ሊሏቸው አይገባም። ምክንያቱም እነሱን አለመቅረፍ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች እንዲቀጥሉ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።

### የዲጂታል መብቶች

የኢንተርኔት ላይ ዓለም ራሱን የቻለና መተዳደር የማይችል ነው ብለው የሚከራከሩ ወገኖች የዲጂታል መብቶች አስፈላጊ እንዳልሆነ ይገልፃሉ። ለዲጂታል መብቶች መታገል ችላ እንደሚባልና በኢንተርኔት ላይ ለመብታቸው የሚታገሉ ሴቶች እንግልት እንደሚደርስባቸውና ይልቁንም ላገኙት ኢንተርኔት የመጠቀም እድል አመስጋኝ እንደሆኑ እንደሚነገቸው የአውደ ጥናት ተሳታፊዎች ገልፀዋል። በተጨማሪም የኢንተርኔት አገልግሎት የመጠቀም እድል ያላቸው ሰዎች የበለፀጉና የከተማ ነዋሪዎችን ስለሚወክሉ ኢንተርኔት መጠቀም በራሱ መብትን መጠቀም እንደሆነ የሚያዩ አስተሳሰቦች እንዳሉ ተሳታፊዎች ገልፀዋል። ሆኖም ግን የአውደ ጥናቶቹ ተሳታፊዎች ይህንን አስተሳሰብ እንደሚቃወሙና የኢንተርኔት ተደራሽነት ማለት የመብት መከበር እንዳልሆነ ይገልፃሉ።

> በቴክኖሎጂ የታገዙ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ከመጀመሪያውም የተገደበውን የሴቶች ዲጂታል መድረክ የበለጠ ያጠቡታል
>
> የአውደ ጥናት ተሳታፊ፣ እ.ኤ.አ 2025

የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች እንደገለፁት በዲጂታል መድረኮች ላይ ያለው የአስተዳደር እጦትና በማህበራዊ መድረኮች ላይ የይዘት ቁጥጥር ውጤታማ አለመሆን የሴቶችን የኢንተርኔት ላይ ተሳትፎ ይገድባሉ። ተሳታፊዎች፣ ዲጂታል መድረኮች ያለተጠያቂነት መንቀሳቀስ እንደሌለባቸውና ኢንተርኔት ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች ሊቀጡ እንደሚገባ ገልፀዋል።

በቴክኖሎጂ የታገዙ ፆታን መሰረት ስላደረጉ ጥቃቶች ለመወያየትና ለማጥናት ቁልፍ እንቅፋት የሆነው "የኢንተርኔት ዓለም" እና "እውነተኛው ዓለም" በሚል የተፈጠረው ሰው ሰራሽ ልዩነት ነው። ከኢንተርኔት ውጪ ያለው ዓለም የኢንተርኔት ላይ ጉዳዮች ላይ ተጽዕኖ እንደሚፈጥር እና የኢንተርኔት ላይ ጥቃቶች የሰዎችን የዕለት ተዕለት ህይወት በሚጎዳ መልኩ ተፅዕኖ እንዳላቸው ግልጽ ነው። አንድ ተሳታፊ እንደገለፁት በኢንተርኔት መድረኮች ላይ የሚደርሱት ጉዳቶች "የእውነተኛው ዓለም ላይ ያሉ ጥቃቶችን የሚመስሉ" እና የገሀዱ ዓለም ላይ ጉዳቶችን የሚያባብሱ ናቸው ። የኢንተርኔትና ከኢንተርኔት ውጪ ያሉ መድረኮች በጥብቅ የተያያዙ ናቸው።

> ያለነው በዲጂታል ዘመን ላይ እንደመሆኑ መጠን ሴቶች በደህንነት የሚሳተፉበት፣ ሃሳባቸውን የሚገልፁበትና ድምፃቸውን የሚያሰሙበት መድረክ ያስፈልጋል
>
> የአውደ ጥናት ተሳታፊ፣ እ.ኤ.አ 2025

## 4.3 ሴቶችና ልጃገረዶች ከወንድ ጋር ሲነጻጸሩ

ይህ ጥናት በሴቶችና ልጃገረዶች ላይ የሚደርሰውን በቴክኖሎጂ የታገዘ ፆታን መሰረት ስላደረገ ጥቃት ቢያጠናም ወንዶችን ኢላማ ስለሚያደርጉ የጥላቻ ንግሮችም አጥንቷል። ይህም በፆታዎች መካከል ስላለው የጥላቻ ንግግር አይነትና አውድ ልዩነት ለማጥናት ያስችላል።


ምንም እንኳን የጥላቻ ንግግሮች በፆታ ረገድ መጠነኛ ልዩነት ቢያሳዩም ስድብ እንደአጠቃላይ በብዛት የታየው የጥላቻ ንግግር እንደሆነ ታይቷል። ነገር ግን የጥላቻ ንግግር አውዶችን ስንመለከት የኢንተርኔት ላይ ጥላቻ ንግግሮች በፆታ መሃከል ያለውን ልዩነት በሰፊው የሚያሳዩ መረጃዎችን እናገኛለን።

ይህ ጥናት በኢትዮጲያ ውስጥ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች እንዴት የማህበራዊ ስነፆታዊ አመለካከት ማንፀባረቂያ እንደሆኑ ያሳያል። ሴቶች ሲገለሉና መሳለቂያ ሲሆኑ ወንዶች ደግሞ የፆታ እኩልነትን በመደገፋቸው እንደ ደካማና ወንዳ ወንድ እንዳልሆኑ የሚገልፁ ጥቃቶች ይደርስባቸዋል። የሁለቱም ፆታዎች ፖለቲካ መሪዎች ጥቃት ቢደርስባቸውም በፖለቲካ ውስጥ ያሉ ሴቶች በመልካቸው ወይም በማህበረሰባዊ ሚናቸው ጥቃት ሲደርስባቸው ወንዶች ግን በፖሊሲ አመለካከታቸው ጥቃት ይደርስባቸዋል። በስርዓተ ፆታ፣ ፖለቲካና ብሔር መሃከል ያሉት ግንኙነቶች የኢንተርኔት ላይ ጥቃትን የሚያወሳስቡና የኢንተርኔት ላይ መድረክ የወንዶችን የበላይነት የሚያንፀባርቁና የፖለቲካ ክፍፍልን የሚያሳብሱ እንዲሆኑ ያደርጋሉ።

### 4.3.1 የጥላቻ አይነቶች ንፅፅር

በወንዶችና በሴቶች በመሃከል የሚደርሱትን ጥላቻ ንግግሮች የሚያወዳድረው ምስል በጥቃቶቹ "አይነቶች" መሃከል መጠነኛ ልዩነቶች እንዳሉ ያሳያል (ምስል 10 ይመልከቱ)። ለወንዶችም ሆነ ለሴቶችና ልጃገረዶች መጠኑ ቢለያዩም ስድብ በሰፊው የታየው የጥላቻ ንግግር "አይነት" ነበር። ወንዶች አጠቃላይ ከሚሰነዘርባቸው ጥቃት ውስጥ ከመቶኛ ከሴቶች የበለጠ ስድብን (56%) ሲያስተናግዱ በመጠኑ የበለጠ ዛቻንም ያስተናግዳሉ (ለወንዶች 10.2% ፣ ለሴቶች 9.6%)።

በተቃራኒው ሴቶች ከመቶኛ የእውቀት፣ የአካል ወይም በማህበራዊ ህይወታቸው የሚያሳንሱ የጥላቻ ንግግሮች ከወንዶች የበለጠ ይደርስባቸዋል (25.8% ለወንዶች ፣18.9 % ለወንዶች)። በተጨማሪ ሴቶች ፆታቸውን ከስንፍናና ስግብግብነት የመሳሰሉ መጥፎ ባህሪያት ጋር የሚያገኛኙ ንግግሮች (19.8%) ከወንዶች የበለጠ ያስናግዳሉ። ትኩረትን ሳቢ በሆነ መልኩ ይህ አይነቱ ጥላቻ ንግግር ከሌሎች ጥላቻ ንግግር አይነቶች ጋር ሲወዳደር ያለው ልዩነት አናሳ ነበር።





*ምስል11: በሲ.አይ.አር መረጃ ስብስብ ውስጥ ያሉ ነዑስ ቡድኖች የሚደርስባቸው የጥላቻ ንግግር አይነት የሚያሳይ ምስል*


### 4.3.2 የጥላቻ ንግግር አውዶች ንፅፅር

ሲ.አይ.አር በጥላቻ ንግግር አውዶች (ፀብ ጫሪ ፣ አፀያፊ፣ ፌዝ፣ ወይም በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የተሳሳቱ አመለካከቶች የያዘ የጥላቻ ንግግሮች ብሎ በመክፈል) ሲመለከት ከጥላቻ ንግግር አይነቶች በበለጠ መልኩ ልዩነቶችን አሳይተዋል። ለምሳሌ ወንዶች (57.2%) ከሴቶች (37.5%) በበለጠ አፀያፊ የጥላቻ ንግግሮች ያጋጥማቸዋል። ይህም የተሰላው እያንዳንዱ ፆታ ከሚደርስበት አጠቃላይ ጥቃት በመቶኛ ነው።

ሴቶችና ልጃገረዶች በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የተሳሳቱ አመለካከቶችን የያዙ ንግግሮች ከወንዶች በበለጠ ያስተናግዳሉ (32.6% ለሴቶች፣ 16.9% ለወንዶች ) ይህ የጥቃት አይነት ወንዶች ከሚደርስባቸው ጥቃት ውስጥም ሁለተኛ ደረጃን ይይዛል።

በተጨማሪም ሴቶች ከሚደርስባቸው የጥላቻ ንግግር 20% የፌዝ ሲሆን ይህ ቁጥር ወንዶች ላይ 10.3% ብቻ ነው። በተጨማሪም ወንዶች (15.5%) ከሴቶች (11.7%) በበለጠ ፀብ ጫሪ የሆኑ ጥላቻ ንግግሮች ቢደርስባቸውም ልዩነቱ ሰፊ አልነበረም።




*ምስል12: በሲ.አይ.አር መረጃ ስብስብ ውስጥ ያሉ ነውስ ቡድኖች የሚደርስባቸው የጥላቻ ንግግር አውድ የሚያሳይ ምስል*

### 4.3.3 ማብራሪያ

በኢትዮጲያ ኢንተርኔት መድረክ ላይ ያሉትን ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ማጥናት ሴቶችና ወንዶች ኢላማ ሲደረጉ ያለውን የጥቃት ልዩነቶች ለማየት ይረዳል። ወንዶች ወንድነታቸውን የሚያሳንሱ ጥቃቶች ሲደርሱባቸው ሴቶች አሳናሽና ከማህበራዊ መድረኮች አግላይ የሆኑ ጥቃቶች ይደርስባቸዋል። አንዳንድ ወንዶች የፆታ እኩልነትን በመደገፋቸው ምክንያት ጥቃት ሲደርስባቸው የፖለቲካና ብሔር ክፍፍሎች ፆታን መሰረት ካደረጉ ጥቃቶች ጋር በመጣመር የኢንተርኔት ላይ ጥላቻን ይቀርጻሉ።

በተመሳሳይ ሁሉም ተሳታፊዎች በሴቶችና ልጃገረዶች ላይ ብቻ በሚለው ክፍል (ክፍል 4.2) ስር የተቀመጠው የዛቻ እና ፀብ ጫሪ ንግግሮች በሁለቱም ፆታ ላይ በአነስተኛ መልኩ መገኘቱ እንዳስገረማቸው ተናግረዋል። እንደ ተሳታፊዎች ዘገባ እነዚህ ውጤቶች “ለዘብ ያሉ” ናቸው። ዛቻ ያዘሉና ፀብ ጫሪ የሆኑ ንግግሮች በብዛት የሚታዩት የጥላቻ ንግግር አውዶች እንደሆኑ እንደሚሰማቸው ተናግረዋል።

*ወንድነትና ሴቶችን ዝቅ አድርጎ መመልከት*

ወንዶች በተለምዶ ከሚጠበቅባቸው በታች ጥንካሬና የበላይነት ካሳዩ ጥቃት ይደርስባቸዋል። “ሴት መሆን ይሻልሀል” እና “ደፋር ሁን “ የሚሉ ስድቦች ወንድነታቸውን ለማጥቃት ጥቅም ላይ ሲውሉ ይህም ማህበረሰቡ ከእነሱ የሚፀብቀውን ጠንካራነትና ጉልበተኛነት ያሳያል።

> This guy should be wearing a dress,
> so weak
>
> HATE SPEECH DATASET

**“ይሄ ቀሚስ ቢለብስ ይሻለዋል፤ ደካማ“**

**ከጥላቻ ንግግር ስብስብ የተወሰደ**

# ይሄ ቀሚስ ቢለብስ ይሻለዋል፣ ደካማ

ከጥላቻ ንግግር ስብስብ የተወሰደ

ሴቶችና ሴትነት የብሄር እና የፆታ ስድቦች መሳሪያ ሆነው ያገለግላሉ። ለምሳሌ “ዲቃላ” የሚለው ቃል (በአብዛኛው የትግሬ ማህበረሰብን ለማጥቃት ጥቅም ላይ ይውላል) ወንዶችን በግልፅ ለማጥቃት ጥቅም ላይ ቢውልም ውስጣዊ ትርጉም ግን “የሴት ልጅ “ለማለት ነው። ይህም ትርጉሙ ከእንግሊዘኛው ሀረግ “son of a bitch“ ጋር ተመሳሳይ ነው። “ሴት ያሳደገው” ከሚለው ሀረግ ጋር በተመሳሳይ መልኩ የሴት ፆታን ወንዶችን ለማዋረድና ለማሸማቀቅ ሲውል በዚህ አውድ ደግሞ ፆታንና ብሄርን በማዋሀድ ጥቃት የሚፈፀምበት ቃል ሆኖ እናየዋለን።

የሲ.ይ.አር መረጃ ተርጓሚዎች እንደተመለከቱት ወንዶች ሌሎች ወንዶችንና ሴቶችን ለማጥቃት የሴቶችን የሰውነት አካላት እንደ መሳሪያ ይጠቀማሉ። በዚህም ምክንያት ሴቶች በቀጥታ ከሚደርስባቸው ጥቃት በተጨማሪ ለሌሎች ጥቃቶች መጠቀሚያና ምልክት ይሆናሉ። ለምሳሌ እንደ አውደ ጥናቶች ተሳታፊዎች ዘገባ የሴቶች የወር አበባ ወንዶችን ለማጥቃት በሰፊው ጥቅም ላይ እየዋለ እንደሆነ ዘግበዋል። እነዚህ ስድቦች ከሴትነት ጋር መያያዝ አሳፋሪ እንደሆነ በማሳየት የተሳሳቱ ፆታዊ አስተሳሰቦችን ያባብሳሉ።

> Abuse targeting men often says things like: *"where did you get your pad?", "do you have enough tampons?", or “you’re acting like you’re on your period!”*

WORKSHOP PARTICIPANT, 2025

**“ወንዶችን ኢላማ የሚያደርጉ ጥቃቶች የሚከተለውን ይመስላሉ፡ “ሞዴስህን ከየት ነወ ያመጣኸው?“ “በቂ ሞዴስ አለህ?“ “ፔሬድ ላይ እነዳለህ ነው እየሆንክ ያለኸው!““**

**የአውደጥናት ተሳታፊ፣ እ.ኤ.አ 2025**

> ወንዶችን ኢላማ የሚያደርጉ ጥቃቶች የሚከተለውን ይመስላሉ፡ “ሞዴስህን ከየት ነወ ያመጣኸው?“ “በቂ ሞዴስ አለህ?“ “ፔሬድ ላይ እነዳለህ ነው እየሆንክ ያለኸው!“

የአውደ ጥናት ተሳታፊ፣ እ.ኤ.አ 2025

አንድ የአውደ ጥናት ተሳታፊ “እሙሙ” የሚለው ቃል የሴቶችን የመራቢያ አካል እንዲወክል ተደርጎ ሴቶች ላይ ጥቃት ለመፈፀም መሳሪያ እየሆነ እንደሆነ ተናግረዋል። ይህ አዝማሚያ በኢትዮጲያ ብቻ የሚታይ ሳይሆን በእንግሊዝኛ ቋንቋም የሴትን መራቢያ አካልን የሚወክሉ ቃላትን እንደ አዋራጅ ስድብ ጥቅም ላይ ይውላሉ። በኢትዮጲያ አውድ የወንዶችን የወሲብ ፍላጎት ለመግለፅም ጥቅም ላይ ይውላሉ። ቃሉ በአጠቃላይ ወንዶችንም ሆነ ሴቶችን ኢላማ ላደረጉ ስድቦች መጠቀሚያ ሆኗል። እነደዚህ ያሉ ስድቦች ሴትነትን ከስድብና ከውርደት ጋር በማያያዝ የተሳሳቱ ፆታዊ አመለካከቶችን ያባብሳሉ።

የአውደ ጥናት ተሳታፊዎች እነዚህ ፆታን መሰረት ያደረጉ ስድቦች ለወንዶች የበላይነት አስተዋፅኦ እንደሚያበረክቱና ሴቶች ከዲጂታል ውይይቶች ላይ ራሳቸውን እንዲያገለግሉ ምክንያት እንደሚሆኑ ገልፀዋል። ሴቶች ድምጻቸውን በኢንተርኔት መድረክ ላይ እንዳያሰሙ የሚያደርገው ጫና በከፍተኛ ሁኔታ በማህበራዊ መድረክ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ የሚገድብ ነው።

**የወንድ የበላይነትን የሚሰብኩ ንግግሮች**

ሲ.አይ.አር በእንግሊዘኛ “simp“ የመሳሰሉትና ሌሎች የወንድ የበላይነትን የሚሰብኩና ሴት ጠል የሆኑ የቃላት አጠቃቀሞችን በኢንተርኔት ላይ ተመልክቷል። የቃሉ አጠቃቀም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተቀየረ ቢመጣም በአብዛኛው ለሴቶች ትኩረት የሚሰጡና ወንዳ ወንድ አይደሉም ተብለው የሚታሰቡ ወንዶችን ለመስደብ ጥቅም ላይ የሚውል ቃል ነው። የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች በእነዚህ ግኝቶች ያልተገረሙ ሲሆን ይህም የሆነው እንደ አንድሪው ቴት ባሉ በኢትዮጲያውያን ወጣቶች ዘንድ ተጽዕኖ እየፈጠሩ በመጡ ግለሰቦች መሆኑን አስረድተዋል። የቴት መልዕክቶች የወንዶችን የበላይነት የሚገልፁና በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት የሚደግፉ ናቸው። ይህ ግኝት ማህበራዊ ሚዲያ ጎጂ ሀሳቦችን በአለም አቀፍ ደረጃ ለማስፋፋት ሊውል እንደሚችል ማሳያ ነው።

> ሴት ልጅን ካከበርካትና ከተንከባከብካት “SIMP“ ነህ። ማንኛውም ሴት ደግሞ “SIMP“ አይመቻትም ይልቁንም በመጥፎ መንገድ የሚያናግራትን ወንድ ነው የምትፈልገው ምክንያቱም ብዙ ሴቶች አስተዳደጋቸው እንደዛ ስለሆነ።

ከጥላቻ ንግግር ስብስብ የተወሰደ

በተጨማሪም እንደ “ሞጣ ቀራንዮ” ያሉ በአሜሪካ የሚገኙ ተፅዕኖ ፈጣሪዎችና የተለያዩ ፖድካስትና ዩትዩብ ፕሮግራም አዘጋጆች ሴት ጠል የሆኑና አፀያፊ የሆኑ ፆታዊ ስድቦችን በቀልድ መልክ እንደሚያስተላልፉ ተገልጿል።እነዚህ አካሄዶች ሴቶችን ማሳነስ እንደ ተለመደ ተግባር እንዲቆጠርና በዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ ያሉ ሴት ጠል ንግግሮች ተቀባይ እንዲሆኑ ያደርጋል። አንድ ተሳታፊ በአንድ ተንቀሳቃሽ ምስል አንዲት ሴት የተገለፀችበትን መንገድ ስታስታውስ “ሌሎች የነዳጅ ቁፋሮ ሲኖራቸው አንቺ እሙሙሽን ታስቆፍሪያለሽ አዕምሮ የለሽም ፣የምታሲቢው በእሙሙሽ ነው” ብላለች (ምንጭ ይህንን የተናገረውን ግለሰብ ላለማጉላት ሲባል አልተገለፀም)

የፖለቲካ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች

ሁለቱም ፆታ የፖለቲካ መሪዎች በኢንተርኔት ላይ ጥቃት ቢደርስባቸውም ሴቶች ብዙውን ጊዜ በመልካቸው ወይም በማህበራዊ ሚናቸው ትችት ሲደርስባቸው፣ ወንዶች ግን በአመለካከታቸውና በተግባራቸው ዙሪያ ያጠነጠኑ ጥቃቶች ይደርስባቸዋል። የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ከወንዶች ይልቅ በሴቶች ላይ የተስፋፉ መሆናቸውን ገልፀዋል። ይህም ከሲ.አይ.አር ቀደምት ጥናት ግኝቶች ጋር የሚጣጣም ነው።

ለምሳሌ ጠ/ሚ/ር አብይ አህመድን የሚቃወሙ አስተያየቶች በኢንተርኔት ላይ ቢኖሩም አዳነች አበቤ ላይ ከሚደርሱት ጥቃቶች በተቃራኒ ኢላማቸው ፖሊሲዎቹና የፖለቲካ አመለካከቶቹ ስለሆኑና ይህ በኢትዮጲያ መንግስት ትርጓሜ መሰረት የጥላቻ ንግግር ስላልሆነ በጥናት ውስጥ አልተካከቱም። በጥቂት አጋጣሚዎች የተገኙ የኦሮሞ ማንነቱ ላይ ያነጣጠሩ የጥላቻ ንግግሮች በጥናቱ ውስጥ ተካተዋል። የእነዚህ ሁለት ታዋቂ ሰዎች ንፅፅር በራሱ በፆታዎች መካከል ያለውን የኢንተርኔት ላይ ጥቃት ልዩነት የሚያመለክት ሲሆን ይህም ሲ.አይ.አር ያነጋገራቸው የማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎችን ተሞክሮ ያጠናክራል።

ፌሚኒስት የሆኑ ወንዶች

ለስርዓተ ፆታ እኩልነት እንደሚሟገቱ ሴቶች ሁሉ ፌሚኒስት የሆኑ ወንዶችም ጥቃት ይደርስባቸዋል። በአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች መሰረት ኢትዮጲያ ውስጥ ወንድ ፌሚኒስት መሆን ሴት ፌሚኒስት የመሆንን ያህል አደገኛ መሆኑን ጠቁመው የሴቶችን መብት በሚደግፉ ወንዶች ላይ የሞት ዛቻ ሲሰነዘር እንዳዩ ገልፀዋል።

## 4.4 ተደራራቢ ጥቃቶች

ሲ.አይ.አር ተደራራቢ የጥላቻ ንግግሮች ላይ ያደረገው ጥናት ውስብስብና ተለዋዋጭ የሆኑ የኢንተርኔት ጥቃቶች መኖራቸው አሳይቷል፤ ይህም ሌሎች ማንነቶች ከፆታ ጋር ኢላማ ሲሆኑ ጥቃቶቹ እንዴት እንደሚለወጡ ያሳያል። ተደራራቢ ጥላቻ ብሎ ለመመደብ የተሰጠው አስተያየት ከአንድ ማንነት በላይን ኢላማ ማድረግ አለበት፡ አካል ጉዳተኝነት፣ ብሔር፣ ፆታ፣ ዘር ወይም ሃይማኖት።


የጥላቻ ንግግሮች ሴቶችና ልጃገረዶችን በባዶ ኢላማ የሚያደረጉ ሳይሆኑ ባሉት ተጨማሪ ማንነቶች ላይ ተመርኩዘው የሚለዋወጡ ናቸው። ሴቶችና ልጃገረዶች ከፆታቸው በተጨማሪ ሌሎች ማንነቶቻቸው (ለምሳሌ ብሔር ወይም ሐይማኖት ) ኢላማ ሲሆኑ የጥላቻ ንግግሩ መልክ ይለወጣል።

ሲ.አይ.አር እነዚህ ሁኔታዎችን በማጥናት በፆታ፣ ብሔር፣ ሀይማኖት እና ቆዳ ቀለም መሃከል ያሉት ግንኙነቶች ኢትዮጲያ ውስጥ ያለውን የኢንተርኔት ላይ ጥቃት እንዴት እንደሚለውጡ አሳይቷል። የፖለቲካ ሁነቶችና ግጭቶች ብሄር ተኮር የሆኑና ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን ሲያባብሱ ሀይማኖታዊ ተፅዕኖዎች ደግሞ ሴቶችን ለሚያጥላሉ መልዕክቶች በር ይከፍታሉ። ለምሳሌ ሙስሊም ሴቶች ከሂጃብ ጋር በተያያዘ የተለየ ጥቃት ይደርስባቸዋል። ሴቶችን ከሔዋን "የመጀመሪያው ሐጥያት" ጋር የሚያገናኙ ስር የሰደዱ ሀይማኖታዊ ትርክቶች ሴት ጠል የሆኑ አመለካከቶችን ለማስቀጠል ጥቅም ላይ ይውላሉ። በተጨማሪም የቆዳ ቀለምን ያማከሉና ፀረ-ጥቁር የሆኑ ጥቃቶች ትኩረት የማይሰጣቸው ግን የተንሰራፉ ናቸው። ግኝቶቹ የጥላቻ ንግግርን ውስብስብነትና ባለብዙ መልክነት ሲያሳዩ ሴቶች ማንነቶቻቸው ለጥቃት መፈጸሚያ መሳሪያ ምክንያት እየሆኑ እንደሆነ ያስረዳሉ።

ከዚህ በታች ባለው ትንተና ውስጥ "ሴቶች እና ሌሎች " የሚለው ምድብ በሲ.አይ.አር ተለይተው ከተዘረዘሩ ቡድኖች ወጪ ያሉትን ያጠቃልላል። ለምሳሌ ከሀይማኖት ጎን ለጎን ፆታ ሲጠቃ ነገር ግን የተጠቃው ሃይማኖት በግልፅ ሳይታወቅ ሲቀር አጥኚዎች ይህንን መደብ ተጠቅመዋል።

ሴቶችን ብቻ ኢላማ ካደረጉ የጥላቻ ንግግሮች ጋር ሲነጻጸር ይህ ትንታኔ ትኩረት የሚስቡ ልዩነቶችን አሳይቷል። (ከዚህ በታች ምስል 13ን ይመልከቱ)

- ያነሰ ስድብ እና አጸያፊ የጥላቻ ንግግሮች፡ ብዙ ኢላማዎች ሲኖራቸው የስድብ እና አፀያፊ ይዘት ያላቸው ንግግሮች እንደሚቀንሱ ሲ.አይ.አር ተረድቷል። ይህ የሚያሳየው ብዙ ማንነቶች እንደ ጥቃት ኢላማነት ሲጣመሩ የጥላቻ ንግግሩ አንቋሻሽ እና ቀጥተኛ ስድብን የያዘ ከመሆን ይልቅ ሌሎች መልኮችን የያዘ ይሆናል።
- የበታችነትን የሚሰብኩ ንግግሮች መብዛት፡ "ሴቶችና ኦሮሞ" ፣"ሴቶችና ሙስሊም" እና "ሴቶችና ሌሎች" የሚባሉት ምድቦች ሴቶች በፆታቸው ብቻ ከሚደርስባቸው ጥቃቶች በበለጠ መልኩ የበታች እንደሆኑ የሚያጎሉ ጥቃቶች ይደርስባቸዋል። ይህም ፆታና ሌሎች ማንነቶች በአንድነት ኢላማ ሲደረጉ ግልፅ ያልሆኑ ነገር ግን ጎጂ የሆኑ ጥቃቶች መኖራቸውን ያሳያል።
- ሴቶችን ከመጥፎ ባህሪያት ጋር የሚያያይዙ ንግግሮች መብዛት፡ ፆታንና ብሄርን ኢላማ ያደረጉ በተለይም "ሴቶችና ትግሬ" ወይም "ሴቶችና ሌሎች " የሚባሉትን ቡድኖች ኢላማ ያደረጉ ጥቃቶች እነዚህን ቡድኖች ከመጥፎ ባህሪያት ጋር አገናኝተዋል። ይህም ስለ ኢላማው ቡድን የተዛቡ አመለካከቶችን እና የተሳሳቱ እሴቶችን ያጠቃልላል። ለምሳሌ ከስግብግብነት፣ ከሴጣናዊ ስራ እና ከክህደት ጋር ማያያዝ።
- ፀብ ጫሪ ንግግሮች መብዛት፡ "ሴቶች እና ኦሮሞ" ፣ "ሴቶችና አማራ" እና "ሴቶችና ትግሬ" ቡድኖች ከሌሎች በበለጠ ፀብ ጫሪ የሆኑና ዛቻ ያለባቸው ንግግሮች ይደርስባቸዋል። በእነዚህ ክልሎች እየተከሰቱ ካሉትና በታሪክ ከነበሩት ግጭቶች አንጻር ውጤቱ አያስገርምም።
- በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የተሳሳቱ ሀሳቦችን የያዙ አስተያየቶች መብዛት፡ በሁሉም ተደራራቢ ጥቃቶች ወቅት ፆታ ብቻውን ከሚጠቃበት ጊዜ በላይ በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የተዛቡ አመለካከቶችን የያዙ ንግግሮች ተስተውለዋል። ይህም ከተወሰኑ ማንነቶች የመጡ ሴቶች ላይ የሚሰነዘሩት ጥቃቶች ሰፊና በጎጂ ባህላዊና ሀይማኖታዊ አመለካከቶች ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን ያሳያሉ።
- ፌዝና የሴጣናዊ ስራ ወንጀላዎች፡ ሌላ ትኩረት ሳቢው ጉዳይ "ሴቶችና ሌሎች" በሚለው ቡድን ላይ ሰፊ የፌዝ ጥላቻ ንግግሮች መታየታቸው ነው። በዚህ ቡድን ውስጥ ያሉ ብዙ ሴቶች ከሰይጣን ጋር መመሳሰልን ጨምሮ ጎጂ በሆኑ ቃላት መሳለቂያ ይሆናሉ። ካለፈው ጥናት ጋር ሲወዳደር ይህ ግኝት በዚህ ጥናት ላይ ጎልቶ ታይቷል።




*ምስል 13: በሲ.አይ.አር የመረጃ ስብስብ ውስጥ የተደራራቢ ጥቃት አላማዎችን የሚያሳይ ምስል*

### 4.4.1 ማብራሪያ

የጥላቻ ንግግር እንደ ብሔር እና ሀይማኖት ባሉ ማንነቶች ላይ በመመስረት ውስብስብና ተለዋዋጭ ይሆናል። የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች የኢትዮጲያ ማህበረሰብ ሃይማኖተኛና ወግ አጥባቂ መሆኑን ገልፀው ይህ በኢንተርኔት ላይም ሆነ ከኢንተርኔት ውጪ ባለው አለም እንደሚታይ አስረድተዋል። ይህ ሁነት በዚህ ጥናት ላይ የታየውን የተደራራቢ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት አዝማሚያ እንደሚያብራራ ገልፀዋል። በተጨማሪም ከተደራራቢ ጥቃቶች ጋር ተያይዘው የሚመጡ ተግዳሮቶች የዕለት ተዕለት አካል መሆናቸውን ገልፀዋል።

> ማንም ሴት ብቻ ሊሆን አይችልም። ብሄር እና ሃይማኖት የመሳሰሉ ሌሎች ማንነቶች አሉት። ተደራራቢ ጥቃቶች በእለት ተእለት ኑሯችን የሚገጥመን ነው።
>
> የአውደ ጥናት ተሳታፊ፣ እ.ኤ.አ 2025

የውስጥ ግጭቶች እና ፖለቲካ

ይህ ጥናት ነባራዊ ወቅታዊ ክስተቶች በኢንተርኔት ክርክር እና የጥላቻ ንግግር ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ያሳያል። የፖለቲካ ክስተቶች በኢንተርኔት ላይ በሚደረጉ የውይይት ርእሶች እና ንግግሮች ላይ ትልቅ ተፅእኖ አላቸው። ለምሳሌ በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች እየተከሰቱ ካሉ ግጭቶችና የውስጥ ፖለቲካ ጋር በተያያዘ በኦሮሞ፣ በአማራ እና በትግራይ ብሔር ተወላጅ ሴቶች እና ልጃገረዶች ላይ ያነጣጠረ ጥቃትን ማየት ይቻላል።

በአማራ፣ በኦሮሞ እና በትግራይ ተወላጆች ላይ ያነጣጠረው ተደራራቢ ጥላቻ ይበልጥ ጠንከር ያለ መሆኑ ለአብዛኞቹ የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች ያስገረመ አልነበረም። የፖለቲካ ጥላቻዎች ብዙውን ጊዜ የተወሰኑ ቡድኖችን ወዳነጣጠሩ ጠንከር ያሉ ንግሮች እና ብሄርን የሚያጠቁ ስድቦች ያመራሉ። የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች ለፖለቲካዊ ክስተቶች ምላሽ የሚሰጡ እና ቀስቃሽ ንግግሮችን የሚጠቀሙ የጥላቻ ንግግሮች በኢንተርኔት ላይ በሰፊው እንደሚታዩ ተናግረዋል።

ቀደም ሲል የተደረገው የሲ.አይ.አር ጥናት የአማራ ሴቶች ከኦሮሞ ሴቶች የበለጠ የስላቅ ንግግር ሰለባ እንደሆኑ ቢያሳይም በአሁኑ ጥናት ላይ ግን የኦሮሞ ሴቶች የበለጠ ፌዝ እና የበታችነትን የሚያመላክቱ ንግግሮችን አስተናግደዋል። ይህ ለምን ሊሆን እንደሚችል የተጠየቁት ተሳታፊዎች፣ የፖለቲካ ምኅዳሩ ለውጥ እና አገራዊ አጀንዳዎችን የሚዘውሩ የተለያዩ ክስተቶች ውጤት እንደሆነ ገልፀዋል።

በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሂጃብ እገዳዎች

ሙስሊም ሴቶችን ኢላማ ያደረጉ ጥቃቶች በመረጃ ስብስብ ውስጥ በሰፊው ታይተዋል። በተለይም በአክሱም ትግራይ ፀረ እስልምና ንግግሮች እየጨመሩ መምጣታቸውና በአራት ትምህርት ቤቶች ሂጃብ መከልከሉን በአውደ ጥናት ውይይቶች ላይ ተነስቷል። ይህም ክስተት ትምህርት ቤቶች ሃይማኖታዊ ወይስ ከሃይማኖታዊ ነፃ መሆን አለባቸው በሚለው ጉዳይ ላይ በኢንተርኔት ላይ እና በማህበረሰቡ ዘንድ ከባድ ክርክሮችን አስከትሏል። እ.ኤ.አ. ከህዳር 2024 ጀምሮ ውጥረቶቹ ተባብሰው ወደ ተቃውሞ፣ ሰላማዊ ሰልፍ እና ሂጃብ እንዲፈቀድ ወደሚጠይቁ ጥሪዎች አድገዋል። እንደ አውደ ጥናት ተሳታፊዎች ገለፃ ይህ ደግሞ ሙስሊም ሴቶች ላይ ያነጣጠሩ ምላሽ የተቃውሞ ሰልፎች እና የኢንተርኔት ላይ ዘመቻዎች እንዲካሄዱ አድርጓል።

ሙስሊም ሴቶች ከመልካቸውም ጋር የተያያዘ ጥቃት ደርሶባቸዋል። ለምሳሌ ሂጃባቸውን ካልለበሱ ወይም ጂንስ ከለበሱ "ጥሩ ሙስሊም አይደሉም" ተብለው በኢንተርኔት ላይ ጥቃት ደርሶባቸዋል።

የሰይጣንነት ውንጀላዎች

ሲ.አይ.አር ሴቶችን ከክፋት ጋር የሚያስተሳስሩ የማሸፍ ንግግሮችን እና አስተያየቶችን አስተውሏል። ንግግሮቹም በጥልቀት ሃይማኖታዊ እና ብዙ ጊዜ በቀጥታ ከሔዋን ጋር የተያያዙ ሃይማኖታዊ አንቀፆችን ይጠቅሱ ነበር። ሄዋን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጠቀሰው ከኃጢአት ጋር ያላት ግንኙነት ሴቶችን ሴጣናዊ አድርጎ ለመሳል በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ ውሏል።

> እየሱስ ሚስት አልነበረውም፣ እግዚአብሄር ሚስት አልነበረውም፣ ሴጣን ከሴቶች እነዳመለጡ ይናገራል። ስለዚህ ፆታማ ያልነገሩን ነገር አለ😂😂😂።

ከጥላቻ ንግግር ስብስብ የተወሰደ

የጥናቱ ውጤት ለአውደ ጥናት ተሳታፊዎች ሲቀርብላቸው፣ አብዛኛውን ጊዜ በመስማማት ጭንቅላታቸውን ነቅንቀዋል። በፆታዊ ጥቃት ውስጥ ሃይማኖታዊ ተጽእኖዎች መታየታቸው አላስገረማቸውም። ከኢንተርኔት ውጭ ሴቶችን ከሰይጣን እና ከሔዋን 'የመጀመሪያው ኃጢአት' ጋር በማወዳደር ሴቶችን ሴጣናዊ ማስመሰል የተለመደ

እንደሆነ እና ይህም ከትውልድ ወደ ትውልድ ተላልፎ የመጣ እንደሆነ ተሳታፊዎቹ ገልፀዋል። ይህ አዝማሚያ አሁንም በኢንተርኔት ላይ እየታየና እና እየተጠናከረ ነው።

በቆዳ ቀለም መገለልና እና ፀረ-ጥቁርነት

አንድ ተሳታፊ በጥናቱ ውስጥ የጎደለው ቁልፍ እና ሰፊ ትንታኔ በቆዳ ቀለም ላይ የተመሰረተ አድልዎ ወይም ፀረ-ጥቁርነት እንደሆነ ጠቁመዋል። ይህም በታሪካዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ እሴቶች ላይ የተመሠረተ እና በዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ጥቃቅን ጥቃቶች እና አድልዎችን የሚያስከትል ነው።

አስተያየት ሰጪዎች ኢትዮጵያ ለቀኝ ግዛት እጇን ባትሰጥም አሁንም በምዕራባውያን የውበት እሳቤ ተፅዕኖ እንዳደሚደርስባት እና ሚዲያው እነዚህን ሃሳቦች እና የውበት መለኪያዎችን እነደሚወስን ይናገራሉ። የአውደ ጥናቱ ተሳታፊ እንደገለፁት ነጣ ያለ ቆዳ አንዳንድ ጊዜ በበለጠ ቆንጆ እና ሀብታም ከመሆን ጋር የተያያዘ ነው። አክለውም ጠቆር ያለ ቆዳ ያላቸው ሰዎች ብዙ ጊዜ በደል እና መገለል እንደሚደርስባቸው ተናግረዋል።

የዩትዩብ ተጽእኖ ፈጣሪዋ ወይኒ ተስፋይ በኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው የቆዳ ቀለም አመለካከት መንስኤ አስተያየቷን ስትገልፅ የባርነት ትሩፋት ለ'ፀረ-ጥቁር' አውዶች አስተዋፅዖ እንዳበረከተ ጠቁማለች። በሚያስገርም ሁኔታ ብዙ ኢትዮጵያውያን ራሳቸውን 'ጥቁር' ብለው እንደማይጠሩ ገልጻለች። ነገር ግን፣ የባርነት ርዕስ ብዙ ጊዜ የማይነሳ ብቻ ሳይሆን በጣም አከራካሪ ነው፣ ይህም የዩትዩብ ቪድዮ በሬዲት ላይ የጥላቻ ንግግር እንዲደርስባት ምክንያት ሆኗል።


የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች አክለውም ሁልጊዜ ሁሉም ነገር ቀጥተኛ እንዳልሆነ አክለዋል። ለምሳሌ ግለሰቦች 'በጣም ነጭ' ተብለው ከተወሰዱ፣ ከኢትዮጵያዊ እንዳልሆኑ ወይም ከውጭ አገር እንደሆኑ ለሚጠቁሙ ሴቶችን ኢላማ ለሚያደርጉ ጥቃቶች ምክንያት ሊሆን ይችላል። እንደመጡበት አካባቢ ቢወሰንም አንዳንድ ጊዜ ጥቁር ቆዳ ከአሉታዊነት ይልቅ ኢትዮጵያዊነትንና አፍሪካንነትን እንደሚወክል ገልፀዋል።

እ.ኤ.አ. በ2023 በተደረጉት አውደ ጥናቶች እና የጠረጴዛ ዙሪያ ውይይቶች ፣ ሲ.አይ.አር በኢትዮጵያ ማህበረሰብ ውስጥ ግለሰቦች ላይ መድሎ የሚፈጥሩ ቁልፍ ቃላትን ሰብስቧል። ይህም ለዚህ ጥናት ለተዘጋጀውን የቃላት ስብስብ መሰረት የሆነ ሲሆን በቆዳ ቀለም ምክንያት ለማግለል የሚያገለግሉ ቃላትን ያጠቃልላል። ለምሳሌ፡- ባሪያ - ትርጉሙም ተገዥ ሰራተኛ ማለት ሲሆን በተለምዶ ጥቁር ቆዳ ያላቸው ኢትዮጵያውያንን ለማመልከት ያገለግላል። ሻንቅላ ደግሞ ግለሰብን የሚያንቋሽሽ ቃል ሲሆን፣ ብዙ ጊዜ ከጥቁር ቆዳ ጋር ይያያዛል።

የጥናት ውጤቶቹ የፆታ እና ማንነት ድምር ውጤት የሆኑና በሴቶች ላይ የሚደርሱትን ልዩ የጥቃት አይነቶች ያጎላሉ። ይህም ሴቶች እና ልጃገረዶች በኢንተርኔት ላይ መድልዎ የሚደርስባቸውን ዘርፈ ብዙ መንገዶች ያሳያል።

## 4.5 ከሌሎች በማንነት ላይ የተመሰረቱ የጥላቻ ንግግሮች ጋር የተደረገ ንፅፅር

የዚህ ጥናት ተቀዳሚ ትኩረት በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ላይ ቢሆንም፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የጥላቻ ንግግር መግለጫን መሠረት በማድረግ፣ ሲ.አይ.አር በተለያዩ ሌሎች ከለላ ያገኙ የማንነት ቡድኖች ላይ ያነጣጠረ የጥላቻ ንግግር ለይቷል። ይህ ክፍል የስርዓተ-ፆታ የጥላቻ ንግግሮችን ከብሄር፣ ሀይማኖት፣ ዘር እና አካል ጉዳተኝነት ጋር በማነፃፀር እና በመተንተን በኢትዮጵያ የኢንተርኔት ላይ የጥላቻ ንግግርን ውስብስብ ገጽታ ያሳያል። (ከዚህ በታች ስእል 14 ይመልከቱ)




*ምስል 14፡ በኢትዮጲያ መንግስት የጥላቻ ንግግርንና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከታተልና ለመቆጣጠር ባወጣው አዋጅ መሰረት የጥላቻ ንግግር ኢላማዎችን የሚያሳይ ከሃሳባዊ ማዕቀፉ ላይ የተወሰደ ቁንፅል*

የጥናት ውጤቱም የተለያዩ ቡድኖች በሚገጥሟቸው የጥላቻ ንግግር ዓይነቶች እና አውዶች ላይ ግልፅ ልዩነቶችን ያሳያል። ትንታኔውም ከሴቶች እና ልጃገረዶች ጋር በማነፃፀር በብሄረሰብ ላይ የሚሰነዘሩ የጥላቻ ንግግር ዓይነቶችን ያሳያል። ሴቶች እና ልጃገረዶች ከብሄር ብሄረሰቦች ይልቅ ለዛቻ ወይምፀብ ጫሪ ንግግሮች የመጋለጥ እድላቸው አናሳ ነው፣ ነገር ግን ባልተመጣጠነ መልኩ በስርአተ-ፆታ ዙርያ የተሳሳቱ አመለካከቶች እና ስላቅ ያለው ጥላቻ ይደርስባቸዋል። ለምሳሌ የብሄር እና ፖለቲካ ውህድ ቀስቃሽ ንግግሮችን በማቀጣጠል፣ ከተለያዩ ማንነት የመጡ ሰዎች ሀገራቸውን ከድተዋል ወይም ከውጭ ሃይሎች ጋር ተሰልፈዋል እንዲባሉ አድርጓል። እንደ "ባንዳ" እና "ከሀዲ" ያሉ የታሪክ ማጣቀሻዎች እና ቃላት በህወሐትና በመንግስት ሃይሎች መሃከል በተከሰተው ግጭት ወቅት (እ.ኤ.አ በህዳር 2020 የጀመረው) እንደታየው በገሃዱ ዓለም ብጥብጥ ለመቀስቀስ ጥቅም ላይ ይውላሉ። በተጨማሪም፣ ሃይማኖታዊ ንግግሮች ጥላቻን ለመሰንዘር በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ ይውላሉ፣ እንደ "ዲያብሎስ" እና "ከሀዲ" ያሉ ቃላቶች የብሄር እና የፖለቲካ መከፋፈልን የሚያጠናክሩ ናቸው። እነዚህ የጥናት ውጤቶች የኢትዮጵያን ቀጣይነት ያለው የፖለቲካ፣ የብሄር እና የሃይማኖት ውጥረቶችን በማንፀባረቅ እና በማጉላት የጥላቻ ንግግርን ጥልቅ ትስስር ባህሪ ያሳያሉ።


### 4.5.1 የጥላቻ ንግግር አይነት ከሌሎች የማንነት ቡድኖች ጋር ማወዳደር

በተለያዩ የማንነት ቡድኖች መሃከል የጥላቻ ንግግር እንዴት ሊገለፅ እንደሚችል ለመረዳት ሲ.አይ.አር በመረጃ ስብስቡ ውስጥ በሰፊው የሚገኙት ቡድኖች ማለትም ሴቶችና ልጃገረዶች፣ ወንዶች፣ ትግሬዎች፣ አማራዎች እና ኦሮሞዎች ያጋጠማቸውን የጥላቻ ንግግር አይነቶች አነጻጽሯል።(ምስል 15 ይመልከቱ)

የስድብ የጥላቻ ንግግር በሁሉም ቡድኖች በሰፊው የታየው የጥላቻ ንግግር አይነት ነበር። ሴቶችና ልጃገረዶች ከትግሬዎች (44.1%)፣ አማራዎች (33.7%) እና ኦሮሞዎች (31.7%) በጥቂቱ ከፍ ያለ ስድቦች አስተናግደዋል። ነገር ግን ስድቦች ወንዶች ላይ ከሚደርሱ የጥላቻ ንግግሮች 56% በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ።

ትግሬዎች፣ አማራዎችና ኦሮሞዎች ከፆታዊ ቡድኖች አንጻር በትንሹ ከፍ ያለ የዛቻ ንግግሮችን ያስተናግዳሉ። በተለይም የትግራይ ተወላጆች በዚህ ረገድ ሲጠቁ 20.4% የሚሆኑት እነሱን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች ዛቻን የያዙ ነበሩ ። በተቃራኒው ሴቶችና ልጃገረዶች በንፅፅር ከሚደርስባቸው ጥቃቶች ዛቻዎች አነስተኛውን (9.6%) መጠን ይይዛሉ።

ሴቶችና ልጃገረዶች እና ወንዶች ከብሄር ቡድኖቹ ጋር ሲነጻጸር ያነሱ ማንነታቸውን ከመጥፎ ባህሪያት ጋር የሚያገናኙ የጥላቻ ንግግሮች ይደርስባቸዋል።ሴቶችና ልጃገረዶች (25.8%) ከወንዶች 18.9%)፣ ከአማራ (23.7%)፣ እና ትግሬ (15.6%) ጋር ሲወዳደር በበለጠ የአስተሳሰብ፣ በማህበራዊ መስተጋብርና በአካላዊ ብቃት ያነሱ እንደሆኑ የሚገልፁ የጥላቻ ንግግሮች ይደርስባቸዋል። ሆኖም ግን የዚህን አይነት የጥላቻ ንግግር በሰፊው የሚያስተናግዱት ኦሮሞዎች (26.1%) ናቸው።




*ምስል 15: በሲ.አይ.አር የመረጃ ስብስብ ውስጥ ባሉ የማንነት ቡድኖች ላይ የደረሱ የጥላቻ ንግግሮች አይነቶችን የሚያሳይ ምስል*

### 4.5.2 የጥላቻ ንግግር አውድ ከሌሎች የማንነት ቡድኖች ጋር ሲወዳደር


የጥላቻ ንግግር **አይነቶች** በቡድኖች መካከል ልዩነት ቢያሳይም የጥቃት ፈጻሚውን ስሜት የሚገልፀው የጥላቻ ንግግር **አውድ** ንፅፅር ግን ግልፅ ያልሆኑና የተወሳሰቡ ውጤቶች አስገኝቷል።

**አፀያፊ** የጥላቻ ንግግር በሁሉም ንዑስ ቡድኖች በሰፊው ቢታይም ሴቶችና ልጃገረዶች በንፅፅር ከሚደርስባቸው ጥቃቶች ውስጥ (35.7%) በመያዝ ከአማራዎች (35.2%) እና ኦሮሞዎች (35.3%) የበለጠውን ድርሻ ይይዛሉ። ወንዶች (57.2%) እና ትግሬዎች (44.7%) የዚህ የጥላቻ ንግግር አውድ ኢላማ ነበሩ።

ሴቶችና ልጃገረዶች (32.6 %) ከወንዶችና (16.9%) እና ትግሬዎች (18.0%) በላይ **ከማንነታቸው ጋር የተያያዙ የተሳሳቱ አመለካከቶችን የያዙ ንግግሮችን** ያስተናግዳሉ። ነገር ግን አማራዎች (32.6%) እና ኦሮሞዎች (34.8%) በጉልህ የእነዚህን አይነት ንግግሮች ሲያስተናግዱ ይህ በብሄር ማንነት ዙሪያ ምን ያህል የተሳሳቱ አመለካከቶች እንዳሉ ያሳያል።

ሴቶችና ልጃገረዶች ፆታቸውንና መልካቸውን ኢላማ ያደረጉ **የፌዝ** የጥላቻ ንግግሮች በሰፊው ያስተናግዳሉ (20%) ይህም የዚህ የጥቃት አውድ በተለየ መልኩ ከፆታ ጋር ያለውን ግንኙነት ያሳያል።

የትግራይ ተወላጆች ከሌሎቹ ንዑሳን ቡድኖች በበለጠ ከፍተኛ **ፀብ ጫሪ** የሆኑ ንግሮች ደርሶባቸዋል(30%) ይህም የሚያሳየው በተለይም የፖለቲካ ሽኩቻ ባለበት ወቅት የብሄር ማንነትን ኢላማ ያደረጉ ፀብ ጫሪ የሆኑ ንግግሮች ሊብሱ እንደሚችሉ ነው።




*ምስል 15: በሲ.አይ.አር የመረጃ ስብስብ ውስጥ ባሉ የማንነት ቡድኖች ላይ የደረሱ የጥላቻ ንግግሮች አውዶችን የሚያሳይ ምስል*

### 4.5.3 ማብራሪያ

ሴቶችና ልጃገረዶችም ሆነ የተለያዩ የብሄር ቡድኖች በኢትዮጲያ ውስጥ ያለውን የህብረተሰብ አመለካከትና የፖለቲካ ምህዳር ውስብስብነትን በሚያሳይ መልኩ የጥላቻ ንግግር ሰለባ ይሆናሉ።

የዘር ክፍፍል እና ጥላቻ

መረጃው እንደሚያመለክተው ፆታን መሰረት ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች በስድብ፣ በፌዝና የተሳሳቱ አስተሳሰቦችን በመጠቀም ሴቶችና ልጃገረዶች በአብዛኛው ያጠቃሉ። እንደ ትግሬ ባሉ ብሔሮች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች ዛቻና ፀብጫሪነትን የያዙና ከፖለቲካ ሁነቶች ጋር የተያያዙ ናቸው። ይህም በአማራ ክልል ያሉት ግጭቶች አይነት የፖለቲካ ሁነቶች ኢንተርኔት ላይ ባለው መድረክ ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ የሚያሳየውን የሲ.አይ.አር የቀድሞ ጥናት ይደግፋል። በሂጃብ ክልከላ ወቅት እንደታየው በኢንተርኔት ላይ ያሉ ጥቃቶች በእውነተኛው ዓለም ላይም ተጽዕኖ ያሳድራሉ።

ብሔር በኢንተርኔት የጥላቻ ንግግር ላይ ያለውን ተጽዕኖ ለማየት አንድ ብሄር ከሌላ ብሄር ጋር የሚያጋጩና የሚያዋርዱ ቋንቋዎችን መመልከት ይችላል። "አህያ"፣ "ባንዳ" ወይም "ከሀዲ" የመሳሰሉት ንግግሮች ብሄር ተኮር የጥላቻ ንግግሮች በኢትዮጲያ ኢንተርኔት መድረክ ላይ የተስፋፉ መሆናቸውን ያሳያሉ።

በተለይም በትግራይ ጦርነት ወቅት "ባንዳ" የሚለው ቃል የትግራይ ተወላጆች ኢላማ ለማድረግ ጥቅም ላይ ሲውል የመኖሪያ አድራሻቸውም ተያይዞ በማህበራዊ መድረኮች ላይ ይለጠፍ ነበር። ከዚያም ሰዎች ያሳድዷቸዋል አንዳንድ ጊዜ አልፎም ይገድሏቸው ነበር። ለዚህም ምሳሌ በፌስቡክ እንዲገደል ቅስቀሳ ከተደረገበት በኋላ በአማራ ክልል ውስጥ የተገደለውን [የትግራይ ተወላጅ የዩንቨርሲቲ አስተማሪ] ማስቀመጥ ይቻላል። እንደ አንድ የአውደ ጥናት ተሳታፊ "ባንዳዎችን" ለይቶ ማንነታቸውንና አድራሻቸውን የሚያጋራ የዩቱዩብ ተጠቃሚ ነበር። የምርመራ ጋዜጠኛ ነኝ የሚለው ይህ ግለሰብ የሰዎቹን ቤት በቪዲዩ በመልቀቅ ተመልካቾቹ ጉዳት እንዲያደርሱ ይቀሰቅስ ነበር። የሲ.አይ.አር ሰራተኞች ይህንን በማጣራት የአውደ ጥናት ተሳታፊውን ሀሳብ አረጋግጠዋል።እነዚህ ተንቀሳቃሽ ምስሎች አሁንም በዩቱዩብ ላይ ይገኛሉ (ምንጮች ለደህንነት ሲባል አልተገለፀም)።

ጥናቱ በተጨማሪ ብሄር ተኮር ጥላቻዎች ከቲክቶክ ይልቅ በዩቱዩብ ላይ የተስፋፉ እንደሆኑ አሳይቷል። ይህም በእያንዳንዱ ማህበራዊ ሚዲያ መድረክ ባለው ልዩነት ምክንያት ሊሆን ይችላል። የዩቱዩብ ረጃጅም ተንቀሳቃሽ ምስሎች ለፖለቲካዊ ይዘት ምቹ መሆናቸው ለብሔር ተኮር ጥቃቶች በር ሲከፍቱ የቲክቶክ አጫጭርና መዝናኛ ላይ ያተኮሩ ተንቀሳቃሽ ምስሎች ይህን አይነት ጥላቻ ንግግር ላያበረታቱ ይችላሉ።

የፖለቲካ እና ብሄር ግንኙነት

*መንግስትን የሚተቹና የሚደግፉ ከፖለቲካዊ አመለካከት ጋር የተያያዙ ፀብ ጫሪ የሆኑ ንግግሮች በመረጃ ስብስብ ውስጥ በሰፊው ታይተዋል። የኢትዮጲያ መንግስት የጥላቻ ንግግር ትርጓሜ "ፖለቲካዊ ማንነትን ወይም አመለካከትን " ጥበቃ እንደሚደረግለት ማንነት ባያካትትም ጥቃቶቹ ብሔርን ወይም ሀይማኖትን ወደ ማጥቃት ሲሻገሩ ሲ.አይ.አር በመረጃ ስብስብ ውስጥ አካቷቸዋል። "አህያ"፣ "ከሀዲ"፣ "ባንዳ" እና "የሚኒሊክ ደጋፊዎች "የሚሉት ቋንቋዎች በዚህ ሁኔታ ውስጥ ጥቅም ላይ ውለው ነበር።*

አንዳንድ የፖለቲካ ሰዎች በፖለቲካ አቋማቸው ብቻ ሳይሆን በብሄራቸውም ጭምር ስድብ ይደርስባቸዋል። እንደዚህ አይነት ጥቃቶች አንዳንድ መሪዎች "ሀገራቸውን የሸጡ"  ወይም ለውጪ ሀገር አሳልፎ የሰጡ እንደሆኑ አድርገው የሚያትቱ ናቸው ። በፖለቲካ ሰዎች ላይ የሚሰነዘሩ የጥላቻ ንግግሮች ወደ አጠቃላይ የብሔር ጥላቻ የሚሻገሩ ናቸው። ለምሳሌ ከዚህ በታች ያለው ፅሁፍ የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን የመንግስት ጠላት ወይም ከሀዲዎች አድርጎ በመሳል የፖለቲካ ጥላቻ እንዴት ወደ ብሔር ጥላቻ ሊሻገር እንደሚችል ያሳያል።

> "
>
> ጌታቸው ረዳና ደብረፂዮን የግብፅ ሰላዮች ናቸው"
>
> "

ከጥላቻ ንግግር ስብስብ የተወሰደ

የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ አማራን ለመጉዳት እየሰሩ ነው በሚል የተለያዩ የፖለቲካ ብሄር ተኮር ጥላቻዎች ሲደርሱባቸው እሱን ለመጉዳትና ከስልጣን የሚወገድበትን መንገዶች የሚጠቁሙ አስተያየቶችም ያሰጣሉ። እንደዚህ አይነት የጥላቻ ንግግሮች በኢትዮጲያ ፖለቲካ መድረክ ውስጥ ፖለቲካና ብሄር ምን ያህል የተቆራኙ እንደሆነ ያሳያሉ። ለምሳሌ ታሪክ ስለ አንዳንድ ጦርነቶች ወይም መሪዎች የተሳሳቱ ሃሳቦችን በማስተላለፍ ዘር ተኮር ለሆኑ የጥላቻ ንግግሮች በር ይከፍታል። አንዳንድ የማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎች ሌሎችን "የሚኒሊክ ደጋፊ" በማለት ዝቅ የሚያደርጉ መልዕክቶችን ይለጥፉ ነበር። በአውደ ጥናቶቹ ወቅት አንድ ተሳታፊ ይህ ንግግር ብሄር ተኮር ስድብ ሳይሆን የፌዴራሊዝም ተቃዋሚ የሆኑ ግለሰቦችን ለመግለፅ የሚውል ንግግር እንደሆነ ተናግረዋል።

*የሃይማኖት ሚና*


በኢትዮጲያ ውስጥ ባሉት የጥላቻ ንግሮች ሀይማኖትን መቀላቀል የተለመደ ነው።  ይህም የበለፀገ ሀይማኖታዊ ታሪክና አሁን ያለው ማህበረሰብ ሀይማኖተኝነት ውጤት ነው። ምንም እንኳ አንድም የሀይማኖት ቡድን ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት የጥቃት ኢላማዎች ውስጥ ያልገባ ቢሆንም ሀይማኖት አንዳንድ ብሄሮችንና የፖለቲካ ቡድኖችን ኢላማ ላደረጉና ከፋፋይ ለሆኑ የጥላቻ ንግግሮችን ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ቀደም ሲል እደተገለጸው "ሴጣን " የሚለው ቃል የተወሰኑ ብሔሮችን ለማጥቃት ጥቅም ላይ ይውላል ይህም በሀይማኖትና ብሄር መሃከል ያለውን ግንኙነት ያሳያል። በተጨማሪም ሰዎችን "ከሀዲ"፣ "እምነት የሌላቸው" ወይም "ሰይጣናውያን "ብሎ

መጥራት በተተረጎመው የጥላቻ ንግግር መረጃ ውስጥ በሰፊው ታይቷል ይህም ሃይማኖታዊ ቋንቋ ከኢላማነት አልፎ በራሱ ሌሎች ፅሁፎች ላይ ጥቅም ላይ እንደሚውል ያሳያል።

> ሃይማኖታዊ ቃላትና ማጣቀሻዎች ኢንተርኔትም ላይ ሆነ ከኢንተርኔት ውጪ የዕለት ተዕለት ንግግሮች ላይ የተለመዱ ናቸው።
>
> የአውደ ጥናት ተሳታፊ፣ እ.ኤ.አ 2025

## 4.6 በተለያዩ የይዘት ዘውጎች ላይ የሚሰነዘሩ የጥላቻ ንግግሮች ንፅፅር በፆታ

ሲ.አይ.አር በተለያዩ የይዘት ዘውጎች ላይ ያሉ የጥላቻ ንግግሮች ካጠና በኋላ ሴትና ወንድ ይዘት ፈጣሪዎች የተለያዩ አይነት ጥቃቶች እንደሚደርስባቸው ተመልክቷል። ሴቶች በማህበራዊ እና አኗኗር ዘይቤ ይዘቶች ላይ በአብዛኛው የስድብና አዋራጅ የጥላቻ ንግግሮች ሲደርስባቸው ወንዶች ደግሞ ከቴክኖሎጂ፣ ከሀይማኖትና ከዘር ጋር በተያያዙ ይዘቶች ጥላቻ ይደርስባቸዋል። ኮሜዲ፣ ሙዚቃና መዝናኛ እና ፖለቲካ በፆታ መሃከል ተመጣጣኝ ስብጥር ያለው የጥላቻ ንግግር ይዘት አሳይተዋል። ይህም የቀንቀሳቃሽ ምስሉ ይዘትና የይዘት ለጣፊው ፆታ በጥላቻ ንግግር ይዘት ላይ ተፅዕኖ እንዳለው ያሳያል።




*ምስል 17፡ ወንድና ሴት ይዘት ፈጣሪዎች የሚደርስባቸውን የጥላቻ ንግግር በተንቀሳቃሽ ምስል ይዘትና ዘውግ ከመቶኛ የሚያነፃፅር ምስል*

### 4.6.1 የተለያዩ ዘውግ ያላቸው ይዘቶችን የሚያዘጋጁ ወንዶችና ሴቶች

እነዚህ ልዩነቶችን የበለጠ ለመዳሰስ ሲ.አይ.አር የተለያዩ ዘውግ ያላቸው ይዘቶችን በሚሰሩ ወንዶችና ሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት አነጻጽሯል። ግኝቶቹም የጥናቱን የቀድሞ ግኝቶች የሚያጠናክሩ ናቸው። የኢንተርኔት ላይ ጥቃትን ለመከላከል የስርዓተ ፀታ ተለዋዋጭነትንና የእያንዳንዱ ይዘት ዘውግ ያማከለ አካሄድ ያስፈልጋል

በሁሉም ዘውጎች ላይ ግኝቶቹ ከዚህ በፊት የተደረሱ መደምደሚያዎችን የሚያጠናክሩ ናቸው። ሴቶች ይዘት ፈጣሪዎች በሚያነሱት ርዕስ ላይ የተመረከዘ ሆን ብሎ የሚደረግ ስላቅ እና ንቀት ሰለባ ይሆናሉ። ከዚህ በታች ያለውን (ምስል 18-21 ይመልከቱ) በወንዶች አዘጋጆች ላይ የሚደርሱት የጥላቻ ንግግሮች በዘውግ የሚለያዩና የህብረተሰቡን አስተሳሰብ የሚያንፀባርቁ ናቸው።

መኪኖች እና ቴክኖሎጂ

- ሴት ይዘት ፈጣሪዎች -መረጃ የለም
- ወንድ ይዘት ፈጣሪዎች ስለ መኪና እና ቴክኖሎጂ ያላቸው ሀሳቦች እና አይታዎች ዝቅ ተደርገው ታይተዋል።

ኮሜዲ ፣ሙዚቃ መዝናኛ

- ሴቶች ይዘት ፈጣሪዎች ከቀጥተኛ ጥቃት ይልቅ በጉዳዩ ላይ ከቁም ነገር አይወስዱም አልፎም ስላቅና ውርደት ይደርስባቸዋል።
- ወንድ ይዘት ፈጣሪዎች ግላዊ ጥቃትና ከአንድ ርዕዮተ ዓለም ጋር የመወገን ውንጀላ ይደርስባቸዋል። ካቀረቡት ይዘት በዘለለ ከማንነታቸውና ማህበራዊ ሚናቸው ጋር የተያያዘ ጥቃት ይደርስባቸዋል።

ምግብ ማብሰል

- በምግብ ማብሰል ይዘት ዘውግ ውስጥ ያሉ ሴቶች ግላዊ ጥቃትና ብቁ እንዳልሆኑ የሚገልፅ ንግግሮች ይደርስባቸዋል። ይህ ከላይ ሲታይ ሴቶች የቤተሰቡ ምግብ አብሳይ እንደሆኑ ከሚያዩ ባህላዊ አመለካከቶች ጋር የሚቃረን ይመስላል። ሲ.አይ.አር ይህንን ለመመርመር ጥቂት ምሳሌዎችን ባበት ወቅት ጥቃቶች በመልካቸው ላይ ያነጣጥሩ መሆኑን ተረድቷል። በእነዚህ አዝማሚያዎች ላይ ተጨማሪ ጥናቶች ያስፈልጋሉ ።
- ወንድ ይዘት ፈጣሪዎች ዙሪያ መረጃ የለም።

ትምህርት

- በዚህ ዘውግ ላይ በሴቶች ይዘት ፈጣሪዎች ላይ የተገኘው ውጤት ሴቶች በትምህርቱ ዘርፍ የሚያጋጥማቸውን ችግር የሚያሳይ ነው። ወንዶችን ከሴቶች በበለጠ በትምህርት የተሸሉ እንደሆኑ የሚያየው ማህበራዊ እይታ በሴቶች ብቃት ዙሪያ እምነት የለውም። የተገኘው ከፍተኛ የፆዝ ንግግር ብዛትም ይህን ያሳያል።
- በተመሳሳይ ወንድ ይዘት ፈጣሪዎች በእውቀታቸውና በተዓማኒነታቸው ላይ ያነጣጠሩ ጥቃቶች ሲደርስባቸው አልፎም ግልፅ የሆኑ ጥላቻ፣ ፆዝና የተሳሳቱ አመለካከቶችን የያዙ የጥላቻ ንግግሮች ይደርስባቸዋል። በተቃራኒው ሴት የይዘት ፈጣሪዎች አነስተኛ ፆዝ፣ ስድብ እና አሳናሽ ንግግሮች ሲደርስባቸው እነሱን ከመጥፎ ባህሪያት ጋር የሚያገናኙ ንግግሮች ግን በብዛት ተሰተውሎባቸዋል።

ፋሽን

- በዚህ ዘውግ ያሉ ሴት የይዘት ፈጣሪዎች በመልካቸው ላይ የተመሰረተ ነቀፌታና በባህላዊ እሴቶች ላይ የተመሰረቱ ጥላቻዎች ይደርስባቸዋል። ሴት ይዘት ፈጣሪዎች ላይ የሚደርሰው አሳነሽ የሆነና ፆዝ የቀላቀለ የጥላቻ ንግግር በፋሽን ላይ ያላቸውን አመለካከት ከቁም ነገር እንዳይወስድ ያደርጋል።

- ወንድ ይዘት ፈጣሪዎች -መረጃ የለም።

ፌሚኒዝምና የሴቶች መብት

- ከዚህ በፊት እንደተብራራው በፌሚዝምና ሴቶች መብት ዙሪያ የሚሰሩ ሴቶች እንደ የግል ጥቅም ማራመድና የምዕራባውያንን አስተሳሰብ ማራመድ ያሉ ድብቅ አላማዎች እንዳላቸው ተደርጎ ይወሰዳሉ። ግኝቶቹም ለስርዓተ ፆታ መታገል ዝቅ መደረግና መገፋትን ያመጣል የሚለውን የጥናቱን ውጤት ያጠናክራል።
- ፌሚነዝምንና የሴቶች መብት የሚደግፉ ወንድ የይዘት ፈጣሪዎች የፆታ እኩልነት በመደገፋቸው ተቃውሞ ገጥሟቸዋል። ይህም ግኝት በአውደ ጥናት ተሳታፊዎች የተነሳውንና ወንዶች ፌሚኒዝምን ሲደግፉ የጥላቻ ንግግር እንደሚደርስባቸው የሚያስረዳውን ሀሳብ ያጠናክራል። ለስርዓተ ፆታ እኩልነት የሚታገሉ ወንዶች ብዙውን ጊዜ በፆታ ላይ የተመሰረቱ አድሎዎችና ዓላማቸውንና ተዓማኒነታቸውን የሚጠራጠሩ ንግግሮች ያስተናግዳሉ።

ፖለቲካና ዜና


- በዚህ ዘውግ ውስጥ ሀሳባቸውን የሚያቀርቡ ሴቶች ከወንድ አቻዎቻቸው አንጻር ስማቸው ጠፍቷል። የሚያነሱት ሀሳብም ተቀባይነቱ ያነሰ ነበር። ከፍተኛ የሆነ አፀያፊና ፀብ ጫሪ የሆኑ ንግግሮች ማስተናገዳቸው በዚህ ዘርፍ ያሉ ሴቶች ምን ያህል ቀጥተኛ ጥቃቶች እንደሚደርሱባቸው ያሳያል።
- ይህ ጥናት በዚህ ዘውግ ውስጥ የሚሳተፉ ወንዶች ቀጥተኛ የሆኑ ስድቦችን ዛቻዎች እነደሚደረሱባችው አሳይቷል። ይህም ወንዶች በእምነታቸው በሚያኒሱት ሀሳብ ጥቃት እንደሚደርስባቸው የሚያሳየውን ቀደምት ግኝት ያጠናክራል።

ሀይማኖት


- በሀይማኖት ዙሪያ ሴት የይዘት ፈጣሪዎች ያለውን ባህላዊ የወንድ የበላይነትን ከመቀየር ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ጥቃት ይደርስባቸዋል። ሴቶች በሀይማኖት ጉዳዮች ላይ ለመወያየት ብቃቱ እንደሌላቸው ተደርጎ ይታያል።
- በዚህ ዘውግ ላይ የሚሳተፉ ወንዶች ተዓማሚነታቸው ጥያቄ ውስጥ ይገባል። አመለካከታቸው ዝቅ ተደርጎ ታይቷል፤ ተቀባይነትም አላገኙም ነበር። ይህም በርዕዮት ዓለም ልዩነትና የሀይማኖት ሀሳቦቻቸውን ካለመቀበል የመጣ ሊሆን ይችላል።

ጉዞ


- ሴት የይዘት ፈጣሪ- መረጃ የለም
- በጉዞ ዘውግ ላይ የሚሰሩ ወንዶች ከተወሰኑ ባህሎችና የፖለቲካ ሀሳቦች ጋር በመወገን ጥላቻ ይደርስባቸዋል።





*ምስል 18፡ ሴት የይዘት ፈጣሪዎች የደረሰባቸውን የጥላቻ ንግግር አይነት በዘውግ የሚያወዳድር ምስል*




*ምስል 19፡ ወንድ የይዘት ፈጣሪዎች የደረሰባቸውን የጥላቻ ንግግር አይነት በዘውግ የሚያወዳድር ምስል*




*ምስል 20: ሴት የይዘት ፈጣሪዎች የደረሰባቸውን የጥላቻ ንግግር አውድ በዘውግ የሚያወዳድር ምስል*




*ምስል 21: ወንድ የይዘት ፈጣሪዎች የደረሰባቸውን የጥላቻ ንግግር አውድ በዘውግ የሚያወዳድር ምስል*

### 4.7 የኢንተርኔት ላይ ጥቃት የሚያደርሱ እና/ወይም የሚደርስባቸው የይዘት ፈጣሪዎች

ሲ.አይ.አር በጥላቻ ንግግር ላይ የተሰማሩ አካውንቶች ራሳቸው የኢንተርኔት ላይ ጥቃት ማስተናገዳቸውን ለማወቅ የቲክቶክ መለያዎችን እና የዩትዩብ ቻናሎችን በጥልቀት አጥንቷል። ሲ.አይ.አካውንቶቹን የጥላቻ ንግግር ላኪ፣ ተቀባይ፣ ላኪ እና ተቀባይ፣ ወይም ላኪም ሆነ ተቀባይ ያልሆኑ (በይዘታቸው ናሙና ትንተና ላይ በመመስረት) በማለት ከፋፍሏቸዋል። የኢንተርኔት ተጠቃሚው ላኪ፣ ተቀባይ፣ ሁለቱንም ቢሆንም ባይሆንም ተመሳሳይ አዝማሚያዎች ታይቷል።

---

# 5. ማጠቃለያ

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ጎጂ፣ የተስፋፉ እና ሥር በሰደደ የሥርዓተ-ፆታ አይታዎች እና የተሳሳቱ አመለካከቶች ውስጥ የተጠላለፉ ናቸው። ሴቶች እና ልጃገረዶች ድምፃቸውን የሚያፍኑ እና በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ የሚገድቡ የስድብ፣ የጭፍን ጥላቻ እና አዋራጅ ንግግሮችን ይጋፈጣሉ።

ከኢትዮጵያውያን ባለድርሻ አካላት የቀረበላቸውን ጥሪ መሰረት በማድረግ ሲ.አይ.አር በቲኪቶክ እና በዩትዩብ ላይ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ላይ ጥናት አድርጓል። በመረጃ ላይ በተመሰረተ ትንተና እና በባለሙያዎች አውደ ጥናት ላይ መሰረት በማድረግ አዳዲስ ግንዛቤዎችን ፈጥሯል። ይህ ዘገባ በኢትዮጵያ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ላይ ያለውን ማስረጃ በማስፋት ውጤታማ የሆነ የፖሊሲ ለውጥ ለማምጣት እና የተሚጋቾችን ጥረቶችን ለማጠናከር ባለድርሻ አካላትን በእውቀት ያስታጥቃል።

> “በቴክኖሎጂ የታገዘ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ችላ ከተባለ ሴቶችን ከማህበራዊ ተሳትፎ ያጠፋል።”
>
> የአውደ ጥናት ተሳታፊ፣ እ.ኤ.አ 2025

ሴቶች እና ልጃገረዶች በቲኪቶክ እና በዩትዩብ ላይ ሰፊ ጥቃት ይደርስባቸዋል። ስድብ፣ አዋራጅ የሆኑ በስርአተ-ፆታ ዙርያ የተሳሳቱ አመለካከቶች እና የበታችነትን የሚጠቁሙ መልእክቶች ይጎላሉ። መሳለቂያዎችም ብዙውን ጊዜ ሴቶች እና ልጃገረዶችን ለማዳከም ጥቅም ላይ ይውላሉ። ዛቻ እና ፀብ ጫሪ ንግግሮች ብዙ ጊዜ ባይሆንም አሁንም ድረስ በኢንተርኔት ላይ እና ከኢንተርኔት ውጭ በሴቶች ደህንነት ላይ ከባድ ስጋቶችን ይፈጥራሉ። ምንም እንኳን የጥላቻ ዓይነቶች በዩትዩብ እና በቲክቶክ ላይ ተመሳሳይነት ያላቸው ቢሆኑም፣ አውዳቸው ግን የተለያየ ነበር። ይህም ለሁለቱም ሰፊ እና የማህበራዊ ሚዲያ ድረ-ገፅ ተኮር መፍትሄዎች አስፈላጊ እንደሆነ ያሳያል። ከሲ.አይ.አር ቀደምት ጥናት ጋር ሲነፃፀርም በፌስቡክ፣ ቴሌግራም፣ ኤክስ፣ ቲክቶክ እና ዩትዩብ መካከል መጠነኛ ልዩነት እንዳለ ያሳያል። የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎችም ይህ በአጠቃቀም እና በይዘት ቁጥጥር ፖሊሲዎች ምክንያት ሊሆን እንደሚችል አስተውለዋል።

ሴቶችንና ልጃገረዶችን ለማግለልና ለማሳፈር ጥቅም ለይ የዋሉ በርካታ ትርክቶች ነበሩ። ሴቶችን በማህበራዊ ሚናቸው እና መልካቸው መተቸት የተለመደ ነበር። በስልጣን ላይ ያሉ፣ ስፖርት ላይ የሚሳተፉና ለሴቶች መብት በመታገል የተለመደውን የአኗኗር ዘዴ የሚቃወሙ ሴቶች ስም መጥፋት፣ ስድብና መገለል ይደርስባቸዋል። ፌሚኒዝም ለባህላዊ አኗኗር ዘይቤ ጠላት እንደሆነና ፌሚኒስቶች ደግሞ ለኢኮኖሚያዊ ጥቅማቸውና ግብረሰዶማዊነትን ለማስፋፋት እንደሚሰሩ ተደርጎ ስማቸው ጠፍቷል። እነዚህ ትርክቶች ከዲጂታል ሙብቶች መጣስ ጋር ሆነው ሴቶችን ዝም የሚያሰኝና ተሳትፎአቸውን የሚገድብ የማህበራዊ ሚዲያ መድረክ እንዲፈጠር አድርጓል።

በተጨማሪ ጥላቻ እንደየፆታው በተለያየ መልኩ ይገለፃል። ለምሳሌ ወንዶች ግትር በሆኑ የፆታዊ ሚናዎች ሲገደቡ የሚደርስባቸው ጥቃቶችም ድክመትና ወንዳወንድ አለመሆን ላይ ያተኮሩና የፆታ እኩልነትን በመደገፍ ምክንያት የሚመጡም ናቸው። ወንድም ሆነ ሴት የፖለቲካ መሪዎች የኢንተርኔት ላይ ጥቃት ቢደርስባቸውም ሴቶች በመልካቸውና ማህበራዊ ሚናቸው ዙሪያ ጥቃት ሲደርስባቸው ወንዶች ግን በፖሊሲ አመለካከታቸው ፣በድርጊታቸውና ከፖለቲካ አመለካከቶቻቸው ጋር በተያያዘ ጥቃት ይደርስባቸዋል።

በአብዛኛው ወንዶችን ኢላማ ያደረጉ ጥቃቶች የሴት ፆታን እንደማሸማቀቂ መሳሪያ ይጠቀማሉ። በመሆኑም ሴቶች በቀጥታ ከሚደርስባቸው ጥቃት በተጨማሪ መገለላቸውን በሚያሰባስብ መልኩ ወንዶችን ለማጥቂያ መሳሪያ ይሆናሉ።

ሆኖም ግን ሴቶችና ልጃገረዶች ኢላማ የሚያደርጉ ጥቃቶች በባዶ የሚፈጠሩ ሳይሆኑ  ተጨማሪ ማንነቶች (ብሔር ፣ሀይማኖት ወ.ዘ.ተ) ላይ ያተኮሩና በእነዚህ ማንነቶች ዙሪያ ተለዋዋጭም ናቸው። የመጀመሪያ ዙር ትንተናዎችና የአውደ ጥናት ውይይቶች ፆታ፣ ዘር፣ ሀይማኖት እና የቆዳ ቀለም በመቀናጀት እንዴት የጥላቻ ንግግርን ሊቀርፁ እንደሚችሉ አሳይተዋል።

የፖለቲካ ሁነቶች የዘር እና የፆታ የጥላቻ ንግግርን ሲያባብሱ ሀይማኖታዊ ትርክቶች ጎጂ ንግግሮች እንዲቀጥሉ ያደርጋሉ። ለምሳሌ በሴቶችና በሄዋን ሀጥያት መካከል ያለው ግንኙነት የወንድን የበላይነት የሚያስቀጥሉ ሀሳቦችን ለማራመድ ጥቅም ላይ ሲውሉ ሙስሊም ሴቶች ደግሞ ሂጃብ ከመልበስ ጋር የተያያዙ ልዩ ጥቃት ይደርስባቸዋል። በተጨማሪም ጥቁር የቆዳ ቀለምን ኢላማ ያደረጉ ጥቃቶች የተስፋፉ ግን በአብዛኛው ያልተጠኑ የጥቃት አይነቶች ናቸው።

ኢትዮጲያ ውስጥ ካለው የበለፀገ የብሔር እና ሀይማኖት ልዩነት አንጻር እያንዳንዱ ቡድን የተለያየ አይነት የጥላቻ ንግግር ቢያጋጥመው የሚገርም አይደለም። ለምሳሌ ሴቶችና ልጃገረዶች ብሔርን ኢላማ ካደረጉ የጥላቻ ንግግሮች አንጻር ያነሱ ግልፅ የሆኑ ማስፈራሪያዎችና ፀብጫሪ ንግግሮች ሲደርሱባቸው በስርዓተፆታ ዙሪያ የተሳሳቱ ሀሳብ የያዙ ንግግሮችና ፌዝ የጥላቻ ንግግር በብዛት ይደርስባቸዋል።

ብሄርና ፖለቲካ ቀስቃሽ ንግግሮችን ሲያባብሱ መሪዎችም ሀገራቸውን በመክዳት እና ከወጪ ሀይሎች ጋር በመስራት በሚል ጥቃት ይደርስባቸዋል። በህወሐትና በመንግስት ሃይሎች መሃከል በተከሰተው ግጭት ወቅት እንደታየው "ባንዳ" እና "ከሀዲ" የሚሉት ቃላት በእውነተኛው አለም ላይ ብጥብጥ በመፍጠር ጥቅም ላይ ውለዋል። በተጨማሪም "ሴጣን "እና "ካፊር" የመሳሰሉት መጥፎ የሀይማኖት ቃላት ክፍፍሎችን ያባብሳሉ። እነዚህ ግኝቶች ኢትዮጲያ ውስጥ ያለውን የጥላቻ ንግግር ውስብስብነትና ባለ ብዙ ገጽታነት ሲያሳዩ የሴቶች የተለያዩ ማንነቶችም ፖለቲካዊ ፣የብሔር እና ሐይማኖታዊ ውጥረቶችን ለማባባስ ጥቅም ላይ ሲውሉ ይታያል።

ሴቶችና ወንዶች የኢንተርኔት ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ከማህበረሰቡ ባህልና ከይዘቱ ዘውግ ጋር የተያያዙና የተለያዩ ጥቃቶች ይደርስባቸዋል። ለምሳሌ በኢንተርኔት ላይ ከትምህርት ጋር የተያያዘ ይዘት የሚያቀርቡ ሴቶች በትምህርት ላይ ያላቸውን ተሳትፎ በሚቀንስ መልኩ የፌዝ የጥላቻ ንግግር ሲደርስባቸው በፖለቲካ ጉዳይ የሚሳተፉት ደግሞ ከፍተኛ የሆነ ፀብ ጫሪ ንግግሮችን ያስተናግዳሉ።

በትምህርትና በሀይማኖት ላይ አትኩረው ኢንተርኔት ላይ ይዘት የሚሰሩ ወንዶች ተዓማኒነታቸው ሲገዳደር ለፆታ እኩልነት የሚታገሉት ደግሞ ከፍተኛ ተቃውሞ ይደርስባቸዋል። በፖለቲካና ሀይማኖት ላይ የሚሰሩ ወንድ የይዘት ፈጣሪዎች ከሚደግፉት አካል ጋር ተያይዞ ጥቃት ይደርስባቸዋል። ይህ ውጤት ችግሩን ለመፍታት ፆታንና የእንዳንዱን ይዘት ዘውግ ያማከሉ መፍትሔዎች አስፈላጊ እንደሆኑ ያሳያል።

ኢንተርኔት ላይ ያሉ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለመከላከል የቴክኖሎጂ መፍትሄና የማህበረሰባዊ ለውጥ እንደሚያስፈልግ የሚያሳዩ የጥላቻ ንግግር አካሄዶች ይታያሉ። ለምሳሌ የቲክቶክ ስሪት ተቃርኖን ሲያስፋፋ የዩቱዩብ ስሪት ደግሞ ከፖለቲካ ጋር የተያያዙ የብሄርና የፆታ ጥላቻ ንግግሮች እንዲባባሱ ያደርጋል።

ይህ ጥናት በይዘት ቁጥጥር ላይ ያለውን ቀውስ ሲያሳይ የኢንተርኔት ላይ ጥቃትን በመከላከል ረገድ ያለውን የእምነት እጦትም ገልጿል። የጥላቻ ንግግርና ሌሎች የፆታዊ ጥቃቶችን ለመከላከል መመሪያዎች ቢኖሩም አፈጻጸማቸው ደካማ ስለሆነ ከማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ጠንከር ያለ እርምጃ ይጠበቃል። የተሻለ የይዘት ቁጥጥር፣ ደንቦችን በአግባቡ ማስፈጸምና የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮችን ተጠያቂነት ማስፈን በተለይም ብዙ ቋንቋ በሚነገርባቸው ሃገራት አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም የኢንተርኔት ላይ ዓለም ከእውነተኛው ዓለም የተለየ ነው የሚለው አስተሳሰብ መለወጥ አለበት። የኢንተርኔት ላይ ዓለምና ከኢንተርኔት ውጪ ያሉት ዓለማት የተያያዙ ናቸው። ከኢንተርኔት ውጪ ያሉ ሁኔታዎች የኢንተርኔት እንቅስቃሴን ሲቀርፁ የኢንተርኔት ላይ ጥቃቶች ከኢንተርኔት አልፈው ከፍተኛና ሰፊ ተፅዕኖ ያሳድራሉ።

አብዛኞቹ ግኝቶች ፆታን መሰረት ያደረገ ጥላቻ የተለመደ ሆኖ የሴቶችን የዲጂታል መድረክ ተሳትፎ እየገደበ እንደሆነ ከሚሳዩት ቀደምት ጥናቶች ጋር ተደጋጋፊ ነው። ሲ.አይ.አር ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ እየተስፋፋ ያለው የስርዓተ ፆታ ጥቃት ላይ ትኩረት በማድረግ ሴቶችና ልጃገረዶች ከመድረኩ ላይ የበለጠ እንዳይገፉ ለማድረግ ያልማል።

---

# 6. ምክረ ሀሳብ

እውነተኛ እና ዘላቂ ለውጥ ለማምጣት በቴክኖሎጂ የታገዙ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለመከላከል የሚደረጉ ማናቸውም ጥረቶች በፆታ ዙሪያ የተሳሳቱ አስተሳሰቦች መቀየር፣ ፆታን መሰረት ያደረጉ መገለልን ማስቀረትና ሴቶችና ልጃገረዶች በማህበራዊ ህይወት ላይ እንዲወከሉ ማድረግን ጨምሮ የችግሩን ስር መሰረት በሚቀርፍ መልኩ መካሄድ አለባቸው። እነዚህን ኢላማ ያደረገ እርምጃ ካልተወሰደ የኢንተርኔት ላይ ጥቃት መደበኛ ሆኖ በኢትዮጲያ ፆታ እኩልነትና ማህበራዊ ተሳትፎ ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ አይቀሬ ነው።

ሲ.አይ.አር ችግሩን ለመፍታት፣ ትምህርት ላይ ማተኮር፣ ህጎችን ማርቀቅና መተግበር፣ የማህበራዊ ሚዲያ መድረክን ተጠያቂነት ማሻሻል፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎችን ማካሄድ፣ ተጋላጭ ቡድኖችን መደገፍና ጥናቶችን ማካሄድ ያካተተ ሁለገብ አካሄድ ይመክራል። እንደ አንድ የዚህ ፕሮጀክት አካል ሲ.አይ.አር ኢትዮጲያ ውስጥ ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በእነዚህ ቁልፍ ሃሳቦች ዙሪያ የሚያጠነጥን [ማህበረሰብ-መር የምክረ-ሃሳቦች ዶክመንት] አሳትሟል (እ.ኤ.አ በግንቦት 2024)። ሲ.አይ.አር ግኝቶቹን የመንግስት ተቋማት ውሳኔ ሰጪነታቸውን በመረጃ ላይ የተመሰረተ ለማድረግ፣ ማህበራዊ ሚዲያ ኩባንያዎች የይዘት ቁጥጥር ብቃታቸውን ለማጎልበት ፣ሲቪል ማህበራት የማንቂያ ስራቸውን ለማጠናከር፣ ህብረተሰቡ ደግሞ ለውጥ እንዲመጣ ድምፁን ለማሰማት ይጠቀሙባቸዋል ብሎ ተስፋ ያደርጋል።

# 7. አባሪ

## 7.1 GLOSSARY

| Term | Definition |
|---|---|
| Hate Speech | Speech that deliberately promotes hatred, discrimination or attacks against a person or a discernible group of identity, based on ethnicity, religion, race, gender, or disability. (Ethiopian Government) |
| Online abuse | Online abuse is a broad term which encompasses many types of harmful behaviours that occur on the internet. The 'Online Harassment Field Manual' published by PEN America, defines online abuse as "pervasive or severe targeting of an individual or group online through harmful behaviour." This includes, and is not limited to, acts such as hatespeech, doxing, and sexual harassment. |
| Gender-based violence | "[H]armful acts directed at any individual or a group of individuals based on their gender. It is rooted in gender inequality, the abuse of power and harmful norms". (UN Women, Africa) |
| Technology-facilitated gender-based violence (TFGBV) | "[A]n act of violence perpetrated by one or more individuals that is committed, assisted, aggravated and amplified in part or fully by the use of information and communication technologies or digital media against a person on the basis of their gender." (UNFPA) |

## 7.2 EXISTING CIR PUBLICATIONS ON TFGBV IN ETHIOPIA:

Research Summary (May, 2024)

- English
- Amharic
- Afaan Oromo
- Tigrigna

Report 1: Silenced, shamed, and threatened (May, 2024)

- English
- Amharic

Report 2: Normalised and Invisible (May, 2024)

- English
- Amharic

Recommendations for combating TFGBV in Ethiopia (May, 2024)

- English
- Amharic

Inflammatory Keyword List (Lexicon)

- CIR Github

Academic Journal article – Journal, *Resources for Annotating Hate Speech in Social Media Platforms Used in Ethiopia: A Novel Lexicon and Labelling Scheme*

- The Resources for African Indigenous Languages Journal

For more information, visit the CIR website.

CONFERENCES:

A conference was held by The Ethiopian Human Rights Defenders Centre, the Ethiopian Women's Human Rights Defenders Network and CIR in Addis Ababa to raise awareness about TFGBV in Ethiopia (May 9, 2024). For more information, see the CIR website.

## 7.3 ANNOTATION PROTOCOL

**The following guide was provided to the data annotation team to ensure that data annotation was consistent between annotators and across languages.**

### THE PROTOCOL

To limit the impact of individual biases during the data annotation process, CIR asks each annotator to follow these annotation protocol, which outline the different variables that should be considered during the labelling of online posts. Please read these guidelines carefully and refer back to them frequently during the study.

If a post contains hate speech (as defined by the Ethiopian Government) three elements need to be labelled using the annotation tool: the target, the type of speech and the sentiment of speech. The categories pertaining to each of these elements are visually depicted in the diagram below.

**TARGET / PROTECTED CHARACTERISTIC (GROUP AND SUBGROUP)**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| GROUP | DISABILITY | ETHNICITY | GENDER | RACE | RELIGION |
| SUB-GROUP | For example:<br>Visually impaired<br>Physically impaired | For example:<br>Amhara<br>Oromo<br>Tigrayan | For example:<br>Women and Girls<br>Men and Boys | For example:<br>Black<br>White<br>Asian | For example:<br>Christian<br>Jewish<br>Muslim |

**TYPE OF HATE SPEECH**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| CATEGORY | INSULT | THREAT | PRESUMED ASSOCIATION | ALLEGED INFERIORITY |
| DEFINITION | Offensive remarks or denigrating expressions. | Intimidation, incitement to hatred, violence, or a violation of rights. | with harmful personality traits, such as laziness or greed. | of social position, cognitive or physical ability. |

**SENTIMENT OF HATE SPEECH**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| CATEGORY | OFFENSIVE | STEREOTYPICAL | MOCKERY | AGGRESSIVE |
| DEFINITION | Offensive remarks, demeaning or denigrating language. Associating the target with harmful or false personal traits, or suggesting the target's inferiority. | Text includes implicit or explicit references to stereotypical beliefs or prejudices about an individual/group with protected characteristics. | Mockery, satire or sarcastic messaging which targets a protected characteristic of the recipient and could be harmful. | Strong language that: physically intimidates, threatens or incites physical violence; or, which requests, suggests or promotes a violation of rights. |

NOTE TO ANNOTATORS:

The views expressed during this research are not those of the investigators and the research team do not condone the opinions expressed. As the dataset contains real messages/posts sent by users on TikTok and YouTube, this research may expose the annotators to offensive and harmful content. Please take steps to protect yourself from the impacts of vicarious trauma. For example, please take regular breaks. Resources on 'Vicarious Trauma' have been shared with you.

## TARGET OF HATE SPEECH

A post that contains hate speech is targeted towards an individual or group with a protected characteristic. To capture this information, the words that convey which individual/group is being targeted should be assigned any of the following labels (in line with the Ethiopian Government's definition of hate speech):

- **Gender:** An individual or group of people of a particular gender. Although not included in the Ethiopian Government's definition, this study includes sexual orientation, e.g., homosexuals in this category. This is because interviewees reported being labelled as homosexual by abusers.
- **Ethnicity:** An individual or group of people who come from a particular place of origin and culture.
- **Religion:** An individual or group of people belonging to a particular religious group.
- **Race:** An individual or group of people possessing distinctive physical traits associated with a particular race.
- **Disability***:* An individual or group of people possessing a particular disability.

**Example A1:** *Stupid women and girls shouldn't talk about political issues. Someone should throw acid at her face, maybe then she will shut up.*

In the above example, the target should be labelled as **Gender** since the words "women and girls", "her" and "she" indicate that women and girls are the target of hate speech.

**Example A2:** *@airline how about donating flights to deport the Invaders back to their homeland. #DeportThem*

In the above example, the target should be labelled as **Ethnicity** since the word "Invaders" indicates that the hate speech is intended for a group of people whose country of origin is different from that of the speaker (even if the specific group is not explicitly mentioned).

## TYPE OF HATE SPEECH

A post that contains hate speech uses language that spreads, incites, promotes, or justifies hatred, discrimination, dehumanisation, intimidation, or violence towards the target (individual/group). To capture this information, the words that convey such language should be assigned any of the following labels.

***2.1 Insult:*** Insults or denigrating expressions against an individual/group due to protected characteristics.

Example B1: *Fucking clueless women and girls should stay in the kitchen and not ruin a good man's name.*

***2.2 Threat:*** Intimidation, threats or incitement to hatred, violence or violation of individuals' rights, due to protected characteristics, such as:

- bodily harm and threats to physical safety (to individual or family members)
- rape threats or sexual harassment
- image-based sexual abuse (also referred to as 'revenge pornography')
- death threats
- arbitrary arrests
- restriction of access to services
- doxing
- online harassment
- creation of videos/memes

Example B2: *I'll fucking kill the RELIGIOUS_GROUP pig.*

***2.3 Presumed Association:*** Presumed association of protected characteristics with any of the following negative connotations:

- propensity to crime or violence
- laziness or other vices such as greed, alcoholism, cleanliness level
- fundamentalism or terrorism
- invasion or conquest of another location
- threat to national security
- threat to welfare/competitors in distribution of resources

Example B3: *Fucking ETHNIC_GROUP always take more than they deserve. Scroungers!*

***2.4 Alleged Inferiority:*** References to the alleged inferiority (or superiority) of individual/group with a protected characteristic, for example, in relation to:

- social position
- credibility (e.g. defamation)
- cognitive ability
- physical ability
- ability to engage in societal activities, e.g. politics

- undesirable or inferior lifestyle/cultural practises
- dehumanisation or association with animals or entities considered inferior

Example B4: *They ETHNIC_GROUP shouldn't be allowed to vote, they don't contribute to our society. They must be silenced.*

SENTIMENT OF HATE SPEECH

The sentiment of hate speech must be labelled as any of:

***3.1 Aggressive:*** This includes strong language that physically intimidates, threatens or incites physical violence against the recipient, or which requests, suggests or promotes a violation of the recipients' rights.

Example C1.a*: I'll fucking kill the RELIGIOUS_GROUP pig.*
Example C1.b: *Stupid women and girls shouldn't talk about political issues. Someone should throw acid at her face, maybe then she will shut up.*

***3.2 Offensive:*** This includes several different forms of speech, from insulting, demeaning or denigrating language, to associating the target (individual or group) with harmful or false personal traits, or suggesting the target's inferiority.

Example C2: *Stupid immigrants… they come and take our resources. They make us weak. They are the enemy.*

***3.3 Mockery:*** This includes jokes, satire or sarcastic messaging which targets a protected characteristic of the recipient and could be harmful. Hateful content is sometimes conveyed using nuances in language, such as sarcasm, mockery, or satire. Previous studies have expressed the importance of not overlooking this form of hate speech.

Example C3: *@xxxxx Ok hoe or whore you choose sweetie?*

***3.4 Stereotypical:*** Text includes implicit or explicit references to stereotypical beliefs or prejudices about an individual/group with protected characteristics.

Example C4: *Fucking clueless women and girls should stay in the kitchen and not ruin a good man's name.*

Please note, the labels are not mutually exclusive. Something can be both offensive and stereotypical.

IMPLEMENTING THE ANNOTATION PROTOCOL: RULES

Dialogue between the annotators and data engineers led to the creation of a series of rules, outlined below, to ensure consistency during annotation.

**Rule 1: Take the text at face value**

Investigators should not infer meaning from the text; the text must be taken at face value. For example, although the following messages from the dataset contained offensive language, the investigators were advised not to annotate the text as they do not make sense.

> *Pitchfork Dirty van bitches with all that his bagpipes again, and, to give a toast is pain Surviving on toast is your skin*
>
> *The highest high, I'm posed to a dyke bitch 'til she wanna Mac go I don't give me scarred I wake*

Similarly, if the target is unclear, investigators were advised not to annotate. The following examples exemplify this challenge.

> *It's just so hard to let you dusty pieces of crap to do the bare minimum when my bitches show out every fucking time....*
>
> In the above example, it is unclear whether the individuals targeted here are being targeted because of a protected characteristic.
>
> *You are not muslim so crime lenesu normal new*
>
> The above example translates roughly to "you are not muslim so crime is normal for them". While 'crime is normal for them' could fall under 'presumed association' of a protected characteristic with crime, it is unclear who the target is. This may have been meant as hate speech, albeit written with a number of grammatical errors, however, no inferences were allowed.
>
> *Yehen aswged ant 666 new*
>
> The above example translates roughly to: 'Terminate/finish this one, it is 666'. While '666' implies Satanism, and it is inciting violence, the target is unclear.

As this investigation relies solely on textual information, context is lost. As a result, the sentiment of the post may not be captured, such as irony. Additionally, abusive terms may have multiple meanings. For example, the term 'public toilet' is used in gendered abuse. According to CIR workshop participants, this term is used against women and girls who people consider sexually promiscuous. Everyone can use a public toilet. Thus, the use of this word against women and girls implies that

anyone can use them and that they are unclean/impure. This is both offensive and derogatory. Without context, however, it is hard to tell if the term 'public toilet' is being used against a woman, or in a different context altogether. As a result, the following example could be gendered abuse, complaining about a woman moaning during intercourse, or it could be talking about a public toilet:

> *They should make a public toilet that isn't so miserably loud when it flushes*

This rule may have resulted in hate speech being excluded from the study. While this could be seen as a limitation, it prevented any personal biases from impacting the annotation process. This ensures that the hate speech dataset that is created is robust and reflects the current definition as set out by the Ethiopian Government.

### Rule 2: The importance of protected characteristics

For a post to be classified as hate speech, it should target a protected characteristic (gender, race, religion, ethnicity or disability) under the current Ethiopian Government definition.

Sometimes the text was highly offensive; however, if no protected characteristics were targeted, then this does not classify as hate speech under the current definition. For example, the following is not hate-speech:

> *@USERNAME graduated from cunt university with honors with a pHd in serving*

The annotation task revealed a lot of hate, threats and incitement to violence directed against President Abiy and his political party, or other political organisations. However, political views and affiliations are not protected characteristics under the Ethiopian Government's definition of hate speech. This only classifies as hate speech when a protected characteristic is mentioned. For example, the following is not hate speech:

> *@USERNAME: #AmharaGenocide by the fascist #AbiyAhmedAli #JusticeForEthiopia*

However, if the above example made reference to Abiy's ethnicity, then this would classify as hate speech. For example:

> *@USERNAME: #AmharaGenocide by the fascist Oromo #AbiyAhmedAli #JusticeForEthiopia #OromoFascism*

Similarly, a Telegram/X (formerly Twitter) user may be targeted for their views. 'Viewpoints' (like political affiliations) are not protected characteristics. This does

not classify as hate speech under the current definition unless a protected characteristic is targeted.

Sometimes posts contained information and misinformation about war crimes and human rights violations inflicted on an ethnic/religious/gender group and/or committed by certain armed/political groups. While this could amount to incitement to hatred against a particular entity, this is not hate speech unless there is also a protected characteristic targeted within the text.

#### Rule 3: Dealing with multiple languages

When posts contained multiple languages, the investigators consulted the wider annotation team which included four hate speech experts spanning four languages: Amharic, Afaan Oromo, Tigrigna, and English. If the text included languages that were not included in this study, the investigators were advised not to annotate the text. If the text included any combination of this investigation's four languages, the team annotated the text together. This ensured that the study remained focussed on the four languages being analysed, however it also means that hate speech may have been excluded from the study. Another implication of this is that text may have been pulled within, for example, the English dataset, but it may have contained Afaan Oromo. When analysing the results of the study it is important to bear this in mind.

#### Rule 4: Copypasta

During the exercise, a number of 'copypasta' texts were identified. Copypasta is a block of text shared on the internet which is literally copy and pasted by multiple users. It often reveals coordination in information sharing. If the copypasta text contained hate speech, as per the guidelines, each instance was annotated. If they didn't conform with the annotation protocol, they were not annotated. Interestingly, this led annotators to identify a number of copypasta websites including Ethiopian Truth.

#### Rule 5: Additional hate speech terms

When terms which could be indicative of hate speech were identified that were not in the study's hate speech lexicon, the investigators were advised to write these down. These will be added to the final hate speech lexicon that is published alongside the report, to ensure that the lexicon is as comprehensive as possible to aid future research. For example, the terms "flour ranger" and "kufr" were identified within the English dataset and added to the lexicon.

## 7.4 BIBLIOGRAPHY

Akshita Jha and R. Mamidi (2017) 'When does a compliment become sexist? Analysis and classification of ambivalent sexism using X (formerly Twitter) data', NLP+CSS@ACL, Available here.

Deborah James (1998) 'Gender-Linked Derogatory Terms and Their Use by Women and girls and Men', American Speech, Vol. 73, No. 4 (Winter, 1998), Duke University Press, pp. 399-420.

Gao, L., Kuppersmith, A., & Huang, R. (2017). Recognizing explicit and implicit hate speech using a weakly supervised two-path bootstrapping approach. arXiv preprint arXiv:1710.07394.

Gashe, S. M. (2022). Hate Speech Detection and Classification System in Amharic Text with Deep Learning. List of Amharic Hate Speech Keywords (Lexicons). Available here.

Mekuanent Degu (2022), "Amharic dataset for hate speech detection", Mendeley Data, V3, doi: 10.17632/fhvsvsbvtg.3

Samuel Minale (2022), "Amharic Social Media Dataset for Hate Speech Detection and Classification in Amharic Text with Deep Learning", Mendeley Data, V1, doi: 10.17632/p74pfhz3yx.1

Surafel Getachew (2020), "Amharic Facebook Dataset for Hate Speech detection", Mendeley Data, V1, doi: 10.17632/ymtmxx385m.1

REPORTS AND WEB ARTICLES USED IN THE LEXICON DEVELOPMENT:

CARD's Bi-weekly Social Media Conversation Sensitivity Report, see here.

David Shariatmadari (2016) 'Eight words that reveal the sexism at the heart of the English language' Available here [last accessed 9 Nov 2023].

Hatebase.org (2023) Available here [last accessed 9 Nov 2023].

Hate Speech Dataset Catalogue, Available here [last accessed 9 Nov 2023].

Peace Tech Lab (n.d.) 'Hateful Speech and Conflict in the Federal Democratic Republic of Ethiopia: Alexicon of hateful of inflammatory words and Phrases' Available here [last accessed 9 Nov 2023].

Thalikir 2016 'Everyday misogyny: 122 subtly sexist words about women and girls (and what to do about them)' Available here [last accessed 9 Nov 2023].

The Wilson Centre (2021) 'Malign Creativity: How Gender, Sex, and Lies are Weaponized Against Women and girls Online' Available here [last accessed 9 Nov 2023].

### 7.5 FUNDING

UK International Development
Partnership | Progress | Prosperity

This material has been funded by UK International Development from the UK government; however, the views expressed do not necessarily reflect the UK government's official policies.